# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## አስረኛ ክፍል


አዘጋጆች:-

ማርታ እሸቱ

ነፃነት ጌትነት

አርታኢ:-

የኋላሸት ደሳለኝ

ገምጋሚዎች:-

መኮንን አስማማው

ተስፋዬ ወ/ሚካኤል

ወርቁ አድማስ



AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትብ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም
ISBN 978-99944-2-255-5

የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት
የፖ.ሳ.ቁጥር 5613
ዱባይ፣
የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት

ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
የፖ.ሳ.ቁጥር 100767
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# ማውጫ

**ይዘት** | **ገጽ**


**መግቢያ** ...................................................... i

**ምዕራፍ አንድ፡-** ቋንቋና ህብረተሰብ ...............................፩

**ምዕራፍ ሁለት፡-** ባሕላዊ ጋብቻ......................................፲፯

**ምዕራፍ ሦስት፡-** ልቦለድ ........................................... ፴፫

**ምዕራፍ አራት፡-** ማሕበረሰብና ጤና ..............................፶

**ምዕራፍ አምስት፡-** ቀና አመለካከት ............................... ፷፯

**ምዕራፍ ስድስት፡-** ግጥም............................................. ፹፯

**ምዕራፍ ሰባት፡-** የአረጋውያን ሚና............................... ፺፩

**ምዕራፍ ሰምንት፡-** ሴቶች በባህል ውስጥ ...........................፻፮

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡-** ሱስ ............................................ ፻፲፱

**ምዕራፍ አስር፡-** ሥራና ምርት..................................... ፻፴

ሙዳየ ቃላት...................................................፻፵፫

ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው ................................ ፻፵፮

ዋቢ መጻሕፍት ..................................................፻፵፯

# መግቢያ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማጐልበትና የሥነጽሑፍና የሥነልሳን እውቀትን ማዳበር ናቸው፡፡ እነዚህ ዓላማዎችም በመርሀ-ትምህርቱ ላይ በግልጽ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች በየጊዜው ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡ አንደኛው የመርሐ ትምህርቱን አላማዎች በማስፈፀም ረገድ የመፅሐፉን አቅም ለማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መርሀ ትምህርቱ ላይ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሲደረግ ነው፡፡

ይህ የ፲ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሆነበት ምክንያትም በ፳፻፩ ዓ.ም. መርሀ ትምህርቱ እንዲሻሻል በመደረጉ ነው፡፡ መጽሐፉ መርሀ ትምህርቱ ትኩረት የሰጠባቸውን ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ እንዲያካትት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹ ማብራሪያዎቹና መልመጃዎቹ መርሀ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በክሂልና በእውቀት ዘርፍ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ፣ ግልፅና ሳቢ፣ መልመጃዎቹ ደግሞ አሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ በየምእራፉ ማብቂያ ዐበይት ነጥቦች በማጠቃለያ መልክ ከመቅረባቸውም በላይ፣ ተማሪዎች የየምዕራፉን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘጋጅተዋል፡፡ ተማሪዎች በነዚህ ነጥቦች እየተመሩ የትምህርቱን ዓላማዎች በመፈፀም ረገድ በራሳቸው ያሉበትን ደረጃ መገምገምና ጉድለቶቻቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም መጽሐፉ ትምህርቱን በሚፈለገው መንገድ ለመከታተልና የትምህርቱን ዓላማዎች ለመጨበጥ ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

በመጨረሻም ለመጽሐፉ ዝግጅት ጽሑፎቻቸውን ያዋሱንን ሁሉ እያመሰገንን፣ ስለመጽሐፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀርቡ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# ቋንቋና ህብረተሰብ

**የምዕራፉ ዐበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ ስለ ቋንቋ አጀማመርና ባህሪያቱ ትናገራላችሁ።
- ✓ ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ።
- ✓ ቃላትን በምእላዶች ተንትናችሁ ትጽፋላችሁ።
- ✓ በልዩ ልዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ስርአትን ጠብቃችሁ ውይይት ታካሂዳላችሁ።
- ✓ በልዩ ልዩ ርእሶች ዙሪያ የሚቀርቡ ሀሳቦችን በጥሞና በማዳመጥ መልእክታቸውን ታስረዳላችሁ።
- ✓ ቃላትን ነፃና ጥገኛ እያላችሁ በመለየት ትመድባላችሁ።
- ✓ የአንድን ሀሳብ እውነታና የግል አስተያየት ለይታችሁ ትናገራላችሁ።
- ✓ የመረጃ ማግኛ የአነባበብ ዘዴን ተጠቅማችሁ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ ሰብስባችሁ ታቀርባላችሁ።
- ✓ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ማስታወሻ ትይዛላችሁ።

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በታች "የቋንቋ አጀማመር" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት በየግላችሁ ስለ ሰው ልጅ የቋንቋ አጀማመር በእርግጠኝነት የምታውቁትንና ከምንባቡ ማወቅ የምትፈልጉትን እንድትዘረዝሩ ተከታዩ ሰንጠረዥ ቀርቦላችኋል፡፡ ሰንጠረዡን ደብተራችሁ ላይ በማስፈር በየረድፉ ነጥቦችን በአጫጭር ሐረጋት ጻፉ፡፡ ከምንባቡ በኋላ ደግሞ ምን እንደተማራችሁ በአጭሩ አስፍሩ፡፡

| ስለቋንቋ አጀማመር | | |
|---|---|---|
| ከዚህ በፊት የማውቀው | ማወቅ የምፈልገው | ከምንባቡ የተረዳሁት አዲስ ነገር |
| | | |

2. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት “የቋንቋ አጀማመር” በሚለው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ስለፍቻቸው የምታውቁትን በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. መለኮት ለ. አዝጋሚ ለውጥ ሐ. ዕደ-ጥበብ

## የቋንቋ አጀማመር

ቋንቋ አንደበታዊና ስርአታዊ የሆነ የሰው ልጅ መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የሰው ልጅ ይህን መሳሪያ መቼና እንዴት እንደጀመረው ለማወቅ በየዘመናቱ ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ የስነሰብ ተመራማሪዎች “የቋንቋ ጥንተ አመጣጥን ሊያስረዱ ይችላሉ” ያሏቸውን ቅሪቶች ማለትም የዋሻ ውስጥ ስእሎች፣ በድንጋይና በሸክላ ላይ የሰፈሩ ጽሑፎችን ቢያጠኑም ከቋንቋ ጥንታዊነት አንጻር ሲታዩ የቅርብ ጊዜ በመሆናቸው ስለቋንቋ

አመጣጥ በቂ ምላሽ አላስገኙም፡፡ በመሆኑም በየዘመኑ የተነሱ ሊቃውንት የተለያዩ መላምቶችን ሲሰነዝሩ ኖረዋል፡፡

መላምቶቹ በርካታ ቢሆኑም፣ ጠቅለል አድርጎ በሁለት በመክፈል መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የሐሳባውያን የቋንቋ የትመጣነት መላምት ሲሆን፣ ሁለተኛው የቁስአካላውያን የቋንቋ የትመጣነት መላምት ነው፡፡

ሐሳባውያን "ቋንቋ ከየት መጣ?" ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ "ቋንቋ ከመለኮት ለሰው ልጅ የተሰጠ ፀጋ ነው" የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ መለኮታዊው ኃይል ቋንቋን ለሰው ልጅ ሰጠ ብለው በሚገልጹበት መንገድ ልዩነት አላቸው፡፡

አዳም ከእግዚአብሔር በተሰጠው ስልጣንና እውቀት መሠረት ስም ማውጣቱን፣ ያወጣውም ስም መጽናቱን፤ ከዚያ ጊዜ አንስቶም ቋንቋ መፈጠሩን ያስረዳሉ፡፡ "በእርግጥ ይህ ከሆነና አንድ ቋንቋ ብቻ የነበረ ከሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ከ፯ሺ በላይ ቋንቋዎች እንዴት ሊኖሩ ቻሉ?" ተብለው ሲጠየቁ፤ "የአዳም ልጆች በነበራቸው አንድ ቋንቋ እየተግባቡ ለስማቸው ማስጠሪያ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ሲገነቡ እግዚአብሔር ወርዶ ቋንቋቸውን እንዳለያየባቸውና በምድር ላይ እንደበተናቸው" ይገልጻሉ፡፡ በአጠቃላይ ሁሉም ሐሳባውያን የቋንቋ ምንጭ መለኮታዊ ኃይል መሆኑን በመቀበል በኩል ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡

**ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ? የቁስ አካላውያን መላምት ምን ይሆናል ብላችሁ ትገምታላችሁ?**

ሁለተኛው የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ መላምት ቁስአካላውያን የሰጡት፣ "ቋንቋ የአዝጋሚ ለውጥ ውጤት ነው" የሚል ሲሆን ለሐሳባቸው መሠረት የሚያደርጉትም "ሰውን ሰው ያሰኘው ዕደጥበብ(ሥራ) ነው" የሚለውን እምነት ነው፡፡ "ሰው ለአሁኑ ማንነቱ የበቃው ተፈጥሮ ያቀረበችለትን በቀጥታ ከመጠቀም አልፎ ይሁነኝ ብሎ የሥራ መሣሪያ

መሥራቱና ማምረት መጀመሩ ነው፡፡ በዚህም አዝጋሚ የለውጥ ሂደት የሰው ዘር በአራት እግሩ መሄዱን አቁሞ ሁለት እጆቹን ለሥራ ነፃ ከማድረግ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ ተግባር እጅን፣ እጅ ደግሞ ተግባርን እያሻሻለ ሲሄድ ተግባር (ሥራ) የሰው ልጅ ማህበራዊነትን እየጠየቀ መጣ፡፡ ማህበራዊነት በተራው ደግሞ እርስ በእርስ የመግባባት ፍላጎትን ፈጠረ፤ ይህ የመግባባት ፍላጎትም በአንደበት ክፍሎች ላይ ለውጥ አስከተለ፤ ቀስ በቀስም ቋንቋ እውን ሆነ፡፡” በማለት የሰው ልጅ ባላወቀውና ባልተገነዘበው መንገድ ቋንቋን እንዳገኘ ያስረዳሉ፡፡

በርካታ የስነ ሰብ ባለሙያዎችም ይህን መላምት ይጋራሉ፡፡ ሳይንሳዊ ትንታኔ ሲሰጡም፣ የመጀመሪያው የሰው ልጅ መግባቢያ ዝግ (ድምጽ አልባ) አካላዊ እንቅስቃሴና ምልክት እንደነበረ፣ የሰው ልጅ ባህል (ሥራ) እየተወሳሰበ በመሄዱ በነበረው ዝግ መግባቢያ ሀሣብን ለመግለጽ እንደተሳነው፣ ስለዚህም በዝግመተ ለውጥ አእምሮው የንግግር ቋንቋን እንደለመደ ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ቁስአካላውያንና የስነሰብ ተመራማሪዎች የሰጡት የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ መላምት፣ በዚህ ዘመን ባሉ አብዛኞቹ የስነልሳን ባለሙያዎች ዘንድ ከሌሎች መላምቶች በተሻለ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ተቀባይነት ለማግኘቱ ሦስት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ የመጀመሪያው መላምቱ በሳይንሳዊ ግኝቶችና አመለካከቶች ላይ መሠረት አድርጎ መሰንዘሩ ሲሆን፣ ሁለተኛው የቋንቋን አመጣጥ ከተግባርና ከማህበራዊ መግባባት ፍላጎት ጋር ማያያዙ ነው፡፡ ስለ ቋንቋ አፈጣጠር ውስጣዊና ውጫዊ ግፊት ማሳየቱም ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን፣ ይህ መላምት የመጀመሪያው የሰው ልጅ ቋንቋ የቱ እንደሆነ አለማመልከቱና፤ የቋንቋ አፈጣጠርን በጊዜና በቦታ ወስኖ ማሳየት አለመቻሉ የተዋጣለት እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

*የመነሻ ሀሳብ፡- (ትምህርት ሚኒስቴር፣ ፕሮጄክት 17000፣ የስነልሳን መግቢያ፣ Amh. 123 ሞጁዩል)*

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት “እውነት” ወይም “ሐሰት” በማለት መልስ ስጡ::**

1. የሰው ልጅ የሚጠቀምበት መግባቢያ ከአንደበቱ በሚያፈልቀው ቋንቋ ብቻ ነው::
2. የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ እውቀት በመላምት ደረጃ ያለና ትክክለኛው ገና ያልተደረሰበት ነው::
3. ጥንታዊ ስእሎች፣ በድንጋይና በሸክላ ላይ ተጽፈው በቁፋሮ የተገኙ ጽሑፎች ስለ ቋንቋ ጥንተ አመጣጥ በቂ መረጃን አስገኝተዋል::
4. በስነልሳን ተመራመሪዎች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው የቁስአካላውያን የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ መላምት ነው::
5. ቁስአካላውያን ለቋንቋ መገኘት ምክንያቱ የሰው ልጅ ይሁነኝ ብሎ ሥራን መሥራቱ ነው ብለው ያምናሉ::

**፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ::**

1. ከሚከተሉት አንዱ ከአንደበት የሚወጣ ድምጽ ሁሉ ቋንቋ እንደማይሆን ማሳያ ነው::
   - ሀ. አንደበት ለንግግር ድምጾች የሰላ ከመሆኑ የተነሳ፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ድምጾችን ማውጣት መቻሉ፤
   - ለ. የንግግር ድምጾች የተለዩና በቁጥርም የተወሰኑ ሆነው፣ ፍች ለማስገኘት የሚቀናጁበት ሥርዓት ያላቸው መሆኑ፤
   - ሐ. የሰው ልጅ ሲያዝን፣ ሲደሰትና ሲበሳጭ የሚያወጣቸው የለቅሶ፣ የጩኸትና የሳቅ ድምጾች በቋንቋነት መቆጠራቸው፤
   - መ. የሰው ልጅ በአንደበቱ ማፍለቅ የሚችለው የንግግር ድምጾችን በመሆኑና ለሌሎች ድምጾች የሰላ አለመሆኑ::

2. በቁፋሮ የተገኙ የድንጋይና የሸክላ ላይ ጽሑፎች ስለቋንቋ ጥንተ አመጣጥ በቂ ምላሽ ያላስገኙበት ምክንያት፡-
   ሀ. ፍቻቸው ባለመታወቁ ነው፤
   ለ. የተጻፉበት ዘመን ሩቅ በመሆኑ ነው፤
   ሐ. ከቋንቋ ጥንታዊነት አንጻር ሲታዩ የቅርብ ጊዜ በመሆናቸው ነው፡፡
   መ. ስለቋንቋ ምንም የያዙት መረጃ ባለመኖሩ ነው፡፡

3. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መካከል ቁስአካላውያን ስለቋንቋ አመጣጥ የሚቀበሉት ____________አስተሳሰብ ነው፡፡
   ሀ. የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ውጤት
   ለ. ከሰማያዊ ኃይል የተሰጠ ፀጋ
   ሐ. ከዘር በውርስ የተገኘ
   መ. ከብልህ ሰዎች የምርምር ውጤት የተገኘ

4. ከሚከተሉት አንዱ የቁስአካላውያን መላምት የተዋጣለት እንዳልሆነ ማሳያ ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
   ሀ. በለውጥ የተቃኘ መላምት መሆኑ፣
   ለ. ቋንቋ ከሰማያዊ ኃይል ለሰው የተሰጠ መሆኑን አለመቀበሉ፤
   ሐ. በሳይንስ ግኝቶች ላይ አለመመስረቱ፤
   መ. የቋንቋ አፈጣጠርን በጊዜና በቦታ ወስኖ አለማሳየቱ፤

5. ስለቋንቋ አጀማመር ቁስአካላዊያን ከሚሰጡት ገለጻ አንጻር ተገቢውን ቅደም ተከተል የያዘው የትኛው ነው?
   ሀ. እደ-ጥበብ፤ የመግባባት ፍላጎት፣ ዝግ መግባቢያ፣ ጥሪ መሰል መግባቢያ፣ አንደበታዊ መግባቢያ(ቋንቋ)
   ለ. የመግባባት ፍላጎት፣ እደ-ጥበብ፣ ዝግ መግባቢያ፣ ጥሪ መሰል መግባቢያ፣ አንደበታዊ መግባቢያ(ቋንቋ)
   ሐ. እደ-ጥበብ፣ የመግባባት ፍላጎት፣ ጥሪ መሰል መግባቢያ፣ ዝግ መግባቢያ፣ አንደበታዊ መግባቢያ (ቋንቋ)
   መ. የመግባባት ፍላጎት፣ ጥሪ መሰል መግባቢያ፣ እደ-ጥበብ፣ ዝግ መግባቢያ፣ አንደበታዊ መግባቢያ (ቋንቋ)፣

፫. ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላት መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. መላምት | 6. አማልክት |
| 2. ፀጋ | 7. ገሀድ |
| 3. ፍንጭ | 8. ስነ-ሰብ |
| 4. መጽናት | 9. መጣጣም |
| 5. ጎራ | 10. ስልጣን |

፬. ከላይ በተራ ቁጥር ፫ በተሰጡት ቃላት ፍቻቸውን ግልጽ የሚያደርጉ ዓረፍተ ነገሮች ሥሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

ቡድን መስርታችሁ "የንግግር ቋንቋ አጀማመር" በሚለው ርዕስ ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

1. የቡድን መሪዎች በየቡድናቸው ያነሷቸውን ዋና ዋና ነጥቦች፣ በመጨረሻ የተስማሙበትን እንዲሁም ድምዳሜና ስምምነት ላይ ያልደረሱባቸውን ጉዳዮች ከነምክንያቱ ሲያብራሩ የቀራችሁት ነጥቦቹን በደብተራችሁ በማስታወሻ መልክ መዝግቡ፡፡
2. በጥንድ በመሆን የያዛችሁትን ማስታወሻ ተናባችሁ የተዘለለ ካለ አሟሉ፡፡
3. “በንግግር ቋንቋ አጀማመር ላይ የተነሱ ፍሬ ሐሳቦች” በሚል ርዕስ የየቡድኑን ሀሳብ አዳምጣችሁ የጻፋችሁትን ማስታወሻ ለክፍሉ በንግግር መልክ አቅርቡ፡፡

### የቡድን ውይይት

የቡድን ውይይት ሲደረግ ከቡድኑ አባላት ሰብሳቢ፣ ጸሐፊ፣ ዘጋቢ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የውይይቱን ሂደት የሚታዘብ ወገን ሊኖር ይችላል። በቡድን ሆናችሁ ስትወያዩ የሚከተሉትን ጉዳዮች ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅባችኋል።

- የቡድኑ አባላት የሚያቀርቡትን ሀሳብ በጥሞና ማዳመጥ፣
- የሌሎች ቡድኖችን የውይይት ሂደት አለማወክ፣
- በሚቀርበው ሀሳብ ላይ እንጂ፣ በግለሰቦች ላይ አለማተኮር፣
- በቡድን አባላት የሚሰጥ የሥራ ድርሻን መወጣት፣
- በቡድን ውይይቱ የላቀ ተሳትፎ ማድረግ፤
- የቡድናችሁ ድምዳሜ ሲቀርብ እንደአስፈላጊነቱ ማብራሪያ በመስጠት መሳተፍ ናቸው።

## ክፍል ሦስት- መጻፍ

፩. ቀጥሎ በቀረበላችሁ ሰንጠረዥ ውስጥ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የቁስ አካላውያንንና የሐሳባውያንን መላምት ጥንካሬና ድክመት ስይታችሁ ጻፉ።

| | የቁስአካላውያን መላምት | |
|---|---|---|
| | ጥንካሬ | ድክመት |
| ምሳሌ | 1. በሳይንሳዊ አመለካከቶች ላይ መቆሙ፣ | 1. የሰው ልጅ የመጀመሪያ ቋንቋ የቱ እንደሆነ አለማመልከቱ፣ |
| | 2. | 2. |
| | 3. | 3. |
| | **የሐሳባውያን መላምት** | |
| ምሳሌ | ጥንካሬ | ድክመት |
| | ሰብአዊ መግባቢያ መሆኑን መግለጽ | መለኮታዊ ስጦታ ነው የሚለው ሀሳብ በአለም ላይ አንድ ቋንቋ ብቻ ይኖር ነበር ወደሚል ድምዳሜ መውሰድ። |
| | 1. | 1. |
| | 2. | 2. |

**፪. ከዚህ በታች በቋንቋ አጀማመርና ባህርይ ላይ ያተኮሩ እውነታዎችና የግል አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ በጥሞና አንብባችሁ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት "በእውነታ ላይ የተመሰረተ" ወይም "የግል አስተያየት" በማለት ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

ሀቅ የሆኑ አስተያየቶች እውነት ላይ የተመሰረቱና በማስረጃ ሊረጋገጡ የሚችሉ ሲሆኑ፣ በአንጻሩ የግል አስተያየት የምንላቸው በግለሰቦች የሚሰነዘሩ አስተያየቶች ሆነው እውነት ይሁኑ ወይም ሐሰት ለማረጋገጥ የሚያስቸግሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ “የትምህርት ቤታችሁ መምህራን ብዛት ፴፬ ነው ቢባል”፣ አባባሉ እውነት ወይም ሐሰት መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

**ምሳሌ፣** ሀ. ለቋንቋ መፈጠር የሰው ልጅ በተፈጥሮ የሚያወጣቸው ማቃሰትን፣ ሳቅንና ለቅሶን የመሳሰሉ ድምጾች አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ማሰብ ይቻላል፡፡ ***የግል አስተያየት***

ለ. ቋንቋ በተናጋሪው ማህበረሰብ ባህልና አስተሳሰብ ላይ ለውጥ በተከሰተ ጊዜ፣ አዲሱን ባህልና አስተሳሰብ ለመግለጽ ሲል ይለወጣል፡፡ ***እውነታ***

1. ቋንቋ የዘፈቀዳዊነት ባህርይ አለው፤ በስያሜውና በተሰያሚው ነገር መካከል ያለው ግንኙነት አጋጣሚያዊ እንጂ ተፈጥሮአዊ አይደለም፡፡
2. እያንዳንዱ የንግግር ድምፅ ከሌላው የሚለይበት የራሱ ባህሪ አለው፡፡
3. የሰው ልጅ በሥራ አማካኝነት በራሱና በአካባቢው ላይ ለውጥ መፍጠሩ የቋንቋ ባለቤት እንዲሆን እንዳገዘው መገመት ይቻላል፡፡
4. ባለንበት ዘመን ስለቋንቋ አጀማመር በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ንድፈ ሀሳብ ቁስ አካላውያን የሰነዘሩት መላምት ሳይሆን አይቀርም፡፡
5. ሰዎች በየትኛውም ቋንቋ ውስጥ ያሉ ቃላትን በመጠቀም ሰምተዋቸውና ተጠቅመውባቸው የማያውቋቸውን አዳዲስ ዓረፍተ ነገሮች በማፍለቅ መግባባት እንደሚችሉ ይታሰባል፡፡

6. በዓለም ላይ ከሌላ ቋንቋ ድምጾች ቃላትንና አገላለጽን ያልተዋሰ "ንጹህ" የሚባል ቋንቋ የለም፡፡
7. ሁሉም ቋንቋዎች የተናጋሪዎቻቸውን ባህል በመግለጽ እኩል ናቸው፡፡
8. የሰው ልጅ ስለቋንቋ አጀማመር ያለው እውቀት በመላምት ደረጃ ያለ ቢሆንም የሀሳባውያን ንድፈ ሀሳብ ከሌሎች የተሻለና ምሉዕ ይመስላል፡፡

## የቋንቋ ባህርያት

በዓለማችን ላይ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ከሌሎች መግባቢያዎች በተለየ አኳኋን አንድ የሚያደርጓቸው ብዛት ያላቸው የጋራ ባህርያት አሏቸው፡፡ ከባህርያቱ መካከል ስምንቱ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

**1. ምሉዕነት፣**

ሁሉም የሰው ልጅ ቋንቋዎች የተናጋሪያቸውን ወግ ልማድ ወይም ባህል በተሟላ አኳኋን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ሁሉም ቋንቋዎች ባህላቸውን በመግለጽ እኩል ናቸው፡፡ ትንሽ ቋንቋ ወይም ትልቅ ቋንቋ የሚባል የለም፡፡ ስለዚህም ቋንቋዎች ሁሉ ለራሳቸው ባህል ምሉዕ በመሆን አንድ አይነት ባህርይን ይጋራሉ፡፡

**2. ሰብአዊነት፣**

የቋንቋ ሰብአዊ ባህሪ የሚገለጸው፣ የመግባቢያነት አገልግሎቱ ለሰብአዊ ፍጡር ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ከሰው ልጅ በስተቀር ቋንቋ ያለው ሌላ ፍጡር የለም፡፡ በዚህ የተነሳ ቋንቋ ሰብአዊ ባህርይ አለው ይባላል፡፡

**3. ዘፈቀዳዊነት፣**

ቋንቋዎች የዘፈቀዳዊነት ባህርይ አላቸው የምንለው የሰው ልጅ መጀመሪያ ቋንቋን መናገር ሲጀምር ከአንደበቱ የሚወጡ ድምጾችን አቀናጅቶ ለአንድ ነገር ወይም ሀሣብ ወኪል እንዲሆኑ ሲያደርግ ባጋጣሚ የተስማማበትን እንጂ፣ ቃላቱ በውክልና ከቆሙለት ነገር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ተመስርቶ አይደለም፡፡ ስለዚህም በስያሜና በተሰያሚው ነገር መካከል ምንም አይነት ተፈጥሮአዊ ግንኙነት የለም፡፡ የተፈጠረው ግንኙነትም በአጋጣሚ የሆነ ነው፡፡

## 4. ተዋዋሽነት፣

አንድ ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር በሚኖረው ንክኪ ሳቢያ ድምጽ፣ ቃል፣ አገላለጽ፣ ወዘተ. ሊዋስ ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳ በአለማችን ላይ ካሉ ቋንቋዎች ያልተዋሰ “ንፁህ” የሚባል ቋንቋ የለም፡፡ ቋንቋዎች፣ ተናጋሪዎቻቸው በሚጋሯቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አንጻር ንክኪ ይኖራቸዋል፡፡ ለምሣሌ፣ አማርኛ ቋንቋ በሐይማኖት ሳቢያ እንደ /ጵ/፣/ፅ/ ያሉ ድምጾችንና እንደ ጳጳስ ያሉ ስሞችን ተውሷል፡፡ ውሰት  የሁለም ቋንቋዎች የጋራ ባህሪ ነው፡፡

## 5. ስርዓታዊነት፣

አንድ ቋንቋ በውስጡ ሁለት አይነት ስርዓቶች ይኖሩታል፡፡ አንደኛው የመዋቅር ስርዓት ሲሆን፤ ድምጾች በስርዓት ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላትም እንዲሁ ተቀናጅተው ሐረግና ዓረፍተ ነገርን የሚያስገኙበት ነው። ሁለተኛው ከቅንጅቱ የሚፈልቀው የፍች ስርዓት ነው፡፡ በቋንቋ መልእክት መተላለፍ የሚችለው ሁለቱ ስርዓቶች የቋንቋ ተናጋሪዎቹ በሚስማሙበትና በሚግባቡበት መንገድ ተጣምረውና ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡

**ምሳሌ፣** በቃል ደረጃ፣ “ገበረ” ለማለት “ረገበ” ብንል ቃሉን የመሰረቱት ድምጾች አንድ ቢሆኑም፣ አደራደራቸው በመቀየሩ “ግብር የመክፈል” ፍችን አላስገኙም፡፡ ከዚህ ይልቅ መላላትን፣ አለመወጠርን የሚያመለክት ፍችን ይዘዋል፡፡ የፍችው መለወጥ በቋንቋው ውስጥ የፍች ስርዓት መኖሩን የሚያሳየን ነው፡፡

## 6. ረቂቅነት፣

አንድ ሰው አንድን ቃል ከወካዩ ግዑዝ ነገር፣ ሁኔታ ነጥሎ ጽንሰ ሀሳቡን ብቻ በመቅረጽ ነገሩ ወይም ሁኔታው ከነበረበት የቦታና የጊዜ ክልል ውጭ ሊናገረው ይችላል፡፡ ለራሱ ሲነገረውም አድምጦ መረዳት አይቸገርም፡፡ ይህም መልዕክትን በተለየና በላቀ ደረጃ የማስተላለፍ ባህሪው ቋንቋ ረቂቅ ነው ያሰኘዋል፡፡

## 7. በመልመድ በትምህርት መገኘት፣

አንድ ህፃን ሲወለድ ይዞት የሚወለደው ቋንቋን ሳይሆን ቋንቋ ለመልመድ የሚያበቃውን ሰብዓዊ ችሎታ ነው፡፡ በሚያድግበት አካባቢ ካለው ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው መስተጋብር በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በማዳመጥ በምላሹም ለመናገር በመሞከር ቋንቋን

ይለምዳል። ከዚህ ባለፈም ት/ቤት በመግባትና፣ ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ ሊማር ይችላል። ቋንቋ ሰዎች ከተወለዱ በኋላ የሚለምዱት ወይም የሚማሩት እንጂ በተፈጥሮ የሚያገኙት አይደለም።

### 8. መወለድ፣ ማደግ፣ መሞት፣

የአንድ ቋንቋ ዘዬዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ከመሆን ደረጃ ሲደርሱ ቋንቋ ተወለደ ይባላል። እንዲሁም አንድ ህብረተሰብ፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ በባህልና በአኗኗር ሲያድግ ቋንቋውም አዳዲስ ቃላት በመፍጠር ያሉትንም ቃላት ትርጉም በማስፋትና ከሌሎችም ቋንቋዎች በመዋስ አብሮ እየተሻሻለና እየበለጸገ ሲመጣ ቋንቋ አደገ ይባላል።

አንድ ቋንቋ ቀስ በቀስ ወደሌላ ቋንቋ ሲለወጥ፣ በሌላ ቋንቋ ሲዋጥና ተናጋሪ ሲያጣ ቋንቋው ሞተ ይባላል።

**፫. በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ቋንቋዎች ይነገራሉ። አማርኛ ቋንቋ ከነዚህ አገርኛ ቋንቋዎች በቃል ደረጃ ውሰት አካሂዷል። በተሰጣችሁ ምሳሌ መነሻነት በጥንድ ሆናችሁ አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች የተዋሳቸውን ቢያንስ አምስት ቃላትን ዘርዝሩ።**

ምሳሌ

| ተ.ቁ | በውሰት ወደ አማርኛ የገባ ቃል | አዋሽ ቋንቋ |
|---|---|---|
| - ሀ | ሰንጋ | ኦሮምኛ |
| - ለ | እንሰት | ጉራጌኛ |
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

፱. በተለያዩ ቡድኖች ሆናችሁ በትምህርት ቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ወደሚገኙ የህዝብ ቤተመጻሕፍት በመሄድ ቀጥሎ የሚቀርብላችሁን የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያን ተከትላችሁ ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች ላይ ስለ ቋንቋ ባህሪያት አጫጭር ማስታወሻዎችን በመያዝ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ አቀናብራችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

### የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያ

ቤተመጻሕፍት በልዩ ልዩ የእውቀት መስኮች ላይ የተጻፉ መጻሕፍት ሲፈለጉ በቀላሉ ሊወጡ በሚችሉበት አኳኋን ተከማችተው የሚገኙበት የእውቀት ማህደር ነው፡፡ በቤተመጻሕፍት ውስጥ መጻሕፍት ብቻ ሳይሆኑ፣ የጥናትና ምርምር ጽሑፎች፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ ልዩ ልዩ መረጃዎችን የያዙ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ይገኛሉ፡፡ የምንፈልገውን መረጃ ከቤተመጻሕፍት ለማግኘት የቤተመጻሕፍት ስነስርዓትንና የመጻሕፍት አፈላለግ ስልትን መገንዘብ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

1. **በቤተመጻሕፍት የምንከተላቸው ዋና ዋና ደንብና ስርዓቶች፣**
   1.1. ፀጥታን መጠበቅ፣
   1.2. የግል መጻሕፍትን ወደ ቤተመጻሕፍት ይዞ አለመግባት፣
   1.3. መጻሕፍትን በተገቢው መልክ መገልገል፤ ማለትም አለማበላሸትና በጥንቃቄ መጠቀም፣
2. **መጻሕፍት በቀላሉ ለማውጣት እንዲያመች ተለይተው የተቀመጡበትን መንገድ ማወቅና መጠቀም፤**
3. **በማንኛውም ጊዜ መጻሕፍቱን በመፈለግ በኩል ችግር ሲያጋጥመን የቤተመጻሕፍት ሠራተኛውን/ዋን እርዳታ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡**

## ክፍል አራት:- ማዳመጥ

፩. ቀጥሎ መምህራችሁ የሚያነብቡላችሁን አጭር ምንባብ እያዳመጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ማስታወሻ ያዙ፡፡

፫. የያዛችሁትን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ እና አቀናብራችሁ በመጻፍ የምንባቡን ዋና መልዕክት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

*ሀ) ጥገኝነት የሚያጠቃው የትኛውን ወገን ነው?*

*ለ) በጥናት እንደተረጋገጠው ጥገኛውና አስጠጊው ያላቸው ብቃት ምን ያህል ነው?*

*ሐ) ጥገኛውና አስጠጊው ያላቸው የዜግነት መደብ ስንተኛ ነው?*

*መ) ጥገኛውና አስጠጊው እርስ በርስ ምን ምን ተግባራትን ይለዋወጣሉ?*

*ሠ) የአዕምሮ ብልሹ ልማድ የተባለው ምንድነው?*

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

**በሚከተለው ሠንጠረዥ በቀረቡት ቃላት ውስጥ ያሉትን ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች በመለየት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

| ተራ ቁጥር | ቃል | ነፃ ምእሳድ | ጥገኛ ምዕሳድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | መለኮታዊነቱን | መለኮት | -ኣዊ | -ነት | -ኡ | -ን |
| 2 | ተማሪዎቹን | | | | | |
| 3 | መምህራኑን | | | | | |
| 4 | ደስታችንን | | | | | |
| 5 | ልጅነታችን | | | | | |
| 6 | አንደበታቸውን | | | | | |
| 7 | አለማችን | | | | | |
| 8 | ስልጣኑን | | | | | |
| 9 | መረመሩት | | | | | |
| 10 | ተፈጥሮአዊ | | | | | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ከተለያዩ የፍልስፍና አተያዮች በመነሳት የተለያዩ ምሁራን የሰጡትን አመለካከት ተመልክተናል:: በቡድን ተወያይተንም ስለ ጽንሰ ሃሣቦቹ ያለንን ዕውቀት አዳብረናል:: ስለ ቋንቋ ባህሪያትም ከቤተመጻሕፍት በማንበብ ያገኘነውን እውቀት ወደ ክፍል በማምጣት ተነጋግረንበታል:: የቃላት መዝገብ ቃላዊ ፍችዎች ካየን በኋላ በአውድ በማስገባት ዓረፍተ ነገሮችን ሠርተንባቸዋል:: በተጨማሪም ቃላትን ነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ በማለት በተለያዩ ክፍሎች መድበን ለማየት ሞክረናል:: የውውይት መመሪያን ተንተርሰን ውይይት አድርገናል:: ከዚህም ባሻገር አንድን ሀሳብ "እውነታ" ወይም "የግል አስተያየት" በማለት ፈርጀን አስቀምጠናል:: የመረጃ ማግኛ ንባብ ዘዴን በመጠቀም ስለቋንቋ አጀማመር ከተለያዩ ምንጮች መረጃን በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማከፋፈል በመረጃው ላይ ውይይት አድርገናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በቡድን ሆናችሁ ሀሳባውያን የሚሰጡትን የቋንቋ አመጣጥ ገለጻ ካብራራችሁ በኋላ በእናንተ አመለካከት ከሐሳባውያንና ከቁሳካሳውያን የተሻለ ገለጻ የሰጠውን ወገን በምክንያት አስደግፋችሁ አሳዩ::
2. በሀሳባዊያን መላምቶች ላይ የተነሱ ጥያቄዎችን ዘርዝራችሁ ምላሽ የሰጡባቸውንና ምላሽ ያልሰጡባቸውን በመለየት አሳዩ::
3. የቋንቋ አመጣጥ ጥያቄ በቁስአካላውያን መላምት ላይ ተመስርቶ ምላሽ ያገኘ ይመስላችኋል? ለምን?
4. በቤተ-መጻሕፍት ውስጥ የምንከተላቸውን ዋና ዋና ደንብና ስርዓቶች ተናገሩ::
5. <u>እቃውን</u> ለመሸጥ እያስማማ ነው:: የተሰመረበትን ቃል ነፃና ጥገኛ ምዕላድ ለይታችሁ ተናገሩ::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለቋንቋ አጀማመር ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት መግለጽ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3. | ለተለያዩ ቃላት ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ቃላትን በምዕላድ በመከፋፈል አጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ውይይት በስርዓት አካሂዳለሁ፡፡ | | | |
| 6. | እውነታና የግል አስተያየት የሆኑትን እለያለሁ፡፡ | | | |
| 7. | ከመረጃ ምንጮች መረጃ መውሰድ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8. | ማስታወሻ መውሰድ ችያለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስከተረዳችሁ ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊ ጋብቻ

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች:-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ✓ በቃል ክፍሎች ሐረጋትን መስርታችሁ ዓይነታቸውን ትጽፋላችሁ።
- ✓ በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር የሚያመጣውን የትርጉም ልዩነት ለይታችሁ ታሳያላችሁ።
- ✓ ለሚቀርቡላችሁ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ።
- ✓ አንድን ሀሳብ በራሳችሁ አባባል ትገልጻላችሁ።
- ✓ የጽሑፍ ንግግር ታደርጋላችሁ።
- ✓ የቃላዊ ግጥም ይዘትን ትተነትናላችሁ።
- ✓ በንግግራችሁ ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋሮችን በማስገባት ትጠቀማላችሁ።
- ✓ ለምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ።
- ✓ ጭውውት ታደርጋላችሁ።

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለ ዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ግምታችሁን በደብተራችሁ አስፍሩ። ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ግምታችሁ ትክክል እንደነበርና እንዳልነበር አረጋግጡ።
2. የጋብቻ ማህበራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
3. የጋብቻ ዓይነቶች ስንት ይመስሏችኋል? ስማቸውን ጥቀሱ።

## የዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ

የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ በተለያዩ የህይወት ዑደቶች ውስጥ ያልፋል። የመጀመሪያዎቹ የህይወቱ ዘመናት የመሸጋገሪያ ስነስርዓት የሚያካሂድባቸው ሲሆኑ፣ ቀጥሎ የሚመጣው የመቀላቀያ **ስነ ስርዓት** የሚያካሂድበት ነው። በመጨረሻም ይህችን ዓለም ሲሰናበት የመለያያ ስነስርዓት የሚደረግለት ይሆናል። ከዚህ አንፃር ልደት፣ እድገት፣ ጋብቻና ሞት ጊዜውን ጠብቆ የሚያልፍባቸው ዑደቶች ናቸው። ከነዚህ መካከል ጋብቻን ነጥለን ብንመለከት፥ ከአፈጻጸሙ አንጻር ብሔራዊ ጋብቻ፣ ባህላዊ ጋብቻና ሀይማኖታዊ ጋብቻ በመባል በሦስት ይከፈላል። በዚህ ጽሑፍ የዘይሴ ብሔረሰብ የባህላዊ ጋብቻ ስርዓትን በማሳያነት እንቃኛለን።

የዘይሴ ብሔረሰብ የሚገኘው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጋሞጎፋ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ውስጥ ዘይሴ በተባለ አካባቢ ነው። ስፍራው የጫሞ ሐይቅ ዳርቻን ይዞ የሚገኝ ለም አካባቢ ነው። በዘይሴ ብሔረሰብ አራት የባህላዊ ጋብቻ አይነቶች ይገኛሉ። እነሱም መደበኛው ባህላዊ ጋብቻ፣ ቦንቃ (ጠለፋ)፣ ዳሎ (የውርስ ጋብቻ) እና ወዶ-ገብ ጋብቻ ናቸው።

ተማሪዎች ምንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ያገኛችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ሀ. መደበኛ ባህላዊ ጋብቻ፡-** በሁለቱ ተጋቢዎች ወላጆችና ጎሳዎች ብቻ ወይም ልጁ ልጅቷን አይቷት ካፈቀራት ወላጆቹን አሳውቆ፣ የልጅቷ ወላጆች በሀገር ሽማግሌዎች ተጠይቀው ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ ድግስ ተደግሶ የሚፈጸም ጋብቻ ነው፡፡ ባህላዊ ጋብቻ የሁለቱም ወላጆች ተሳትፎ እንጂ፣ እምብዛም የልጁንና የልጅቷን ተሳትፎ አይጠይቅም፡፡ የትዳር ጓደኛ መረጣው በሚደረግበት ጊዜ ሁለቱ ወጣቶች የአንድ ጎሳ አባላት አለመሆናቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ ምክንያቱም የአንድ ጎሳ አባል ወንዶችና ሴቶች እንደ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ስለሚቆጠሩ እርስ በርሳቸው ሊጋቡ አይችሉም፡፡

**ለ. ቦንቃ (ጠለፋ)፡-** አግቢው ልጅ ጉልበቱንና ሀብቱን በመተማመን ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ልጅቷን ይዟት ሲኮበልል የሚከሰት ጋብቻ ነው፡፡ በባህሉ መሠረት ቦንቃ ሕገወጥ ጋብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም ጠለፋው ያለ ልጅቷ፣ ያለወላጆቿ፣ ወይም ያለጎሳዎቿ ፈቃድ የሚከናወን በመሆኑ ነው፡፡ ልጅቷ እንደተጠለፈች፣ ልጁ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ወደ አሳቻ ቦታ ይወስዳታል፡፡ በዚህን ጊዜ የልጁ ወላጆች የሀገር ሽማግሌዎችን ወደ ልጅቷ አባት ቤት ይልካሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም ወደ ልጅቷ አባት ቤት ሄደው ደጃፍ ላይ በጉልበታቸውና በግንባራቸው በመተኛት፤ "ሐላቱኒን፣ ባላቱኒን፣ (ተሳስተናል፣ አጥፍተናል) "ኑና ሚያይት ዶስ ሚያይት" (እንቀጣለን፣ እንክሳለን) በማለት አፈር በአፋቸው ውስጥ በመጨመር ይለምናሉ፡፡ የልጅቷ አባት የሚስማሙ ከሆኑ "ተነሱ ከቤተዘመድና ከጎረቤት ጋር ተማክሬ መልሱን እነግራችኋለሁ" በማለት በቀጠሮ ይሸኟቸዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ተማክረው ልጁ የሚመጥናቸው ከሆነ በልጅቷ እህት ወይም በጓደኞቿ ልጅቱ እንድትጠየቅ ያደርጋሉ፡፡ የአዎንታ መልስ ከሰጠች የልጅቷ ወላጆች የካሣና የጥሎሽ ጥያቄያቸው ይሟላና ልጁና ልጅቷ በሰርግ ወይም ያለሰርግ ለጋብቻቸው ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው አብረው ይኖራሉ፡፡ ወላጆቿ ካልፈቀዱ ተጠላፊዋ ከወላጆቿ ፈቃድ አትወጣም፡፡

**ሐ. ዳሎ (የውርስ ጋብቻ)፡-** ይህ ጋብቻ ዕድሜው በጣም አጭር ነው ይባላል፡፡ ስለሆነም በብሔረሰቡ ዘንድ አልተስፋፋም፡፡ ሆኖም ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ ታላቅ ወንድም ሲሞት ታናሽ የታላቁን፤ ታናሽ ወንድም ሲሞት ደግሞ ታላቅ የታናሹን ሚስት ማግባት የውርስ ጋብቻ ይባላል፡፡ ይህ የውርስ ጋብቻ በብሔረሰቡ አጠራር **ዳሎ** ይባላል፡፡ **የዳሎ** ጋብቻ ዓላማው የሟቹን ልጆች በእንክብካቤ ለማሳደግና ንብረቱን ለሚያድጉ ልጆች ለማቆየት ነው፡፡

**መ. ወዶ-ገብ ጋብቻ፡-** ልጁ (ግለሰቡ) ሣያፈቅራትና ሳይጠይቃት በልጅቷ ፍቃድ ብቻ የሚከሰት ጋብቻ ነው፡፡ መንስኤውም የባህል ተጽእኖ እንደሆነ ይታመናል፡፡ አንዲት ልጃገረድ በተለያዩ ባህላዊ ተጽእኖዎች ምክንያት ሳታገባ ብዙ ጊዜ ልትቆይ ትችላለች፡፡ በዚህ ጊዜ ያለው አማራጭ "ቆማ ቀረች" እንዳትባል ብቻ በገዛ ፍቃዷ "ባል ይሆነኛል" ብላ ወደምትገምተው ግለሰብ ቤት ቀጥ ብላ ሄዳ መቀመጥ የግድ ይሆናል፡፡ በባህሉ መሠረት ወዳ የመጣች ልጃገረድ "እግረ እርጥብ" እንደሆነችና በረከት ይዛ እንደምትመጣ ስለሚታመን አትጠላም፡፡ ግለሰቡ ያገባ ወይም ያላገባ ሊሆን ይችላል፡፡ ወዶ-ገብ ጋብቻ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር በብሔረሰቡ ዘንድ አይዘወተርም፡፡

ለማጠቃለል ያህል የህይወት ዑደት አካል ከሆኑት በአንዱ ውስጥ እኚህ አራቱ የጋብቻ ዓይነቶች በዘይሴ ብሔረሰብ ሲስተናገዱ ኖረዋል፤ እየተስተናገዱም ይቀጥላሉ፡፡

*(አባይነህ ኡናሾ፣ የዘይሴ ብሔረሰብ ባህል፣ 1999፤ 23-29፣ በመጠኑ ተሻሽሎ የቀረበ)*


## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የዘይሴ ብሄረሰብ በየትኛው የኢትዮጵያ ክልልና ወረዳ ይገኛል?
2. በዘይሴ ብሔረሰብ መደበኛ ባህላዊ ጋብቻ ስርዓት ውስጥ የጋብቻ ምርጫ የማድረግ ሀላፊነት የማን ነው?
3. በዘይሴዎች ቦንቃ (ጠለፋ) ህገወጥ የሚሆነው ለምንድን ነው?

4. በዘይሴ ብሔረሰብ ውስጥ የዳሎ ጋብቻ ዓላማው ምንድን ነው?
5. በዘይሴ ባህል በተመሳሳይ ጎሳ አባላት መካከል ጋብቻ መፈጸም የማይቻለው ለምንድን ነው?

**፪. ከዚህ በታች የሰው ልጅ በተለያዩ ስነስርዓቶች የሚያልፍባቸውን የህይወት ዑደቶች የምታመለክቱበት ምስል ቀርቧል፡፡ በምንባቡ መሰረት ዑደቶቹን በቅደም ተከተል በስተቀኝ በኩል በቁጥሮቹ ትይዩ በመሙላት ግለጹ፡፡**




አንድ ______________

ሁለት ______________

ሦስት ______________

አራት ______________

**፫. ቀጥሎ ከምንባቡ በወጡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍች ፈልጉላቸው፡፡**

ሀ. መደበኛ ባህላዊ ጋብቻ በብሔረሰቡ <u>ወግ</u> እና ደንብ ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም ነው፡፡

ለ. ከቤተ-ዘመድና ከጎረቤት ጋር ተማክሬ መልሱን እነግራችኋለሁ በማለት <u>ይሸኟቸዋል</u>፡፡

ሐ. ጠለፋ ልጁ ልጅቷን ይዟት <u>ሲኮበልል</u> የሚከሰት ነው፡፡

መ. አንዲት ልጃገረድ በተለያዩ ባህላዊ <u>ተጽዕኖዎች</u> ምክንያት ሳታገባ ብዙ ጊዜ ልትቆይ ትችላለች፡፡

ሠ. ወዳ የመጣች ልጃገረድ <u>እግረ እርጥብ</u> ስለሆነች በረከት ይዛ ትመጣለች ተብሎ ይታመናል፡፡

፱. ከዚህ በታች በሳጥኑ ውስጥ የተዘረዘሩትን ቃላት በተከታዩ ጽሑፍ ውስጥ በተስማሚው ቦታ በማስገባት አንቀጹን አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሽርክና | አሀድ | እውቅና |
| ዘላቂነት | ማስታወቂያ | ተጽዕኖ |

## ጋብቻ

ጋብቻ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ስነምግባራዊ መሠረት ያለው የግለሰቦች ጥምረት ነው፡፡ ዋነኛ ግቡም የህብረተሰብ መዋቅር መሠረታዊ __ሀ__ የሆነውን ቤተሰብን መመስረትና የማህበረሰቡን ህልውና __ለ__ ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተጋቢዎች አንድ ህጋዊና ማህበራዊ ተቋም ለመመስረት የሚያስችላቸውን __ሐ__ ሲመሰርቱ አባል ለሆኑበት ማህበረሰብ ይፋዊ __መ__ ይሆን ዘንድ ልዩ የጋብቻ ስነስርአትን ያዘጋጃሉ፤ ያከብራሉ፡፡ ማህበረሰቡም ለዚህ ሽርክና __ሠ__ ይሰጣል፡፡ ባቋቋማቸው የፍትህ አካላት አማካኝነትም ህጋዊ ጥበቃ ያደርግለታል፡፡

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፲. በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ባለ አንድ ባህላዊ ጋብቻ ላይ ጭውውት ታደርጋላችሁ፡፡ ለዚህ እንዲረዳችሁ፡-

1. በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶች፣ ከጋዜጦች፣ ከሬዲዮና ከቴሌቪዥን ማስታወሻ ውሰዱ፡፡ የአካባቢውን ባህል የሚያውቁ ሰዎችን ወይም የአካባቢውን የባህል መስሪያ ቤት ባለሙያዎች እየጠየቃችሁ ማስታወሻ ያዙ፡፡
   - ሀ. በባህሉ መሰረት የጋብቻ ምርጫ በማን ይካሄዳል?
   - ለ. የምርጫው መስፈርት ምንድን ነው?
   - ሐ. የሚያጨው አካል የትኛው ነው?
   - መ. "ልጃችሁን ለልጃችን" የሚለው ጥያቄ የሚቀርብበት ስነስርአት ምን ይመስላል?

ሠ. ጥያቄው በልጅቷ ቤተሰቦችና ቤተዘመዶች እንዴት ይስተናገዳል?
ረ. በምን ያህል ጊዜ ጥያቄው ምላሽ ያገኛል?
ሰ. የቃል ማሰሪያ ስነስርአቱ ጊዜ በማንና እንዴት ይቆረጣል?
ሸ. የሰርጉ ጊዜ መቼና እንዴት ይወሰናል?

2. የያዛችሁትን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ፣ የጋብቻ ጥያቄ አቀራረብና የሴቷ ቤተዘመድ በጥያቄው ላይ የሚያደርጉትን የሀሳብ ልውውጥ የሚያሳይ አንድ ጭውውት አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ። (በጭውውታችሁ ለአውዱ ተስማሚ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ተጠቀሙ)

**የማስታወሻ አወሳሰድ፣**

(አንድን ንግግር አዳምጣችሁ ማስታወሻ ስትይዙ የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውሉ)

- ማስታወሻ ለመውሰድ ባሰብን ጊዜ ሁሉ የማስታወሻ ደብተር (ወረቀት) እና ብዕር ማዘጋጀታችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል።
- እንደማስታወስ ችሎታችንና እንደሚኖረን ማስታወሻ የመያዣ ጊዜ ዋና ዋና ነጥቦችን:-
  - ✓ በቃላት ደረጃ
  - ✓ በሐረጋት ደረጃና
  - ✓ በዓረፍተ ነገር ደረጃ እንዳመቺነቱ ጽፈን መያዝ አስፈላጊ ነው።

**፪. የሚከተሉት ሁለት የጋብቻ አይነቶች ምን እንደሆኑ ሰዎችን በመጠየቅ በአካባቢያችሁ ያሉ የፍትሕና የማህበራዊ ጉዳይ መሥሪያ ቤቶችን በማነጋገር፣ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን በማንበብ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በማዳመጥ ማስታወሻ ይዛችሁ፣ የአስር ደቂቃ ማብራሪያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።**

1. ብሔራዊ ጋብቻ
2. ሐይማኖታዊ ጋብቻ

፫. ከዚህ በታች የቀረበላችሁን የንግግር መመሪያ መሰረት አድርጋችሁ፣ በአካባቢያችሁ ባለ ባሕላዊ ጋብቻ ላይ ያተኮረ አንድ የአስር ደቂቃ የጽሑፍ ንግግር በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። (በንግግራችሁ ሀሳባችሁ ጎልቶና ደምቆ እንዲሰማ ለአውዱ ተስማሚ ምሳሌያዊ ንግግሮች መጠቀምን አትዘንጉ)

## የንግግር መመሪያ

ንግግር በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ የሚችልና ሐሳብ አፍልቀን ለሌሎች የምናስተላልፍበት ክሂል ሲሆን፣ ከዝግጅት እስከ አቀራረብ ጥንቃቄን ይሻል።

**ሀ. ዝግጅት**

- የአድማጮችሁን እድሜውን፣ ጾታውን፣ የእውቀት ደረጃውን፣ ግላዊ አቋሙን፣ ወዘተ. ማወቅ፤
- የርእሱን ጥልቀት መወሰን፤
- መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች ማሰባሰብ፣
- ካሰባሰባችኋቸው መረጃዎች ውስጥ ለንግግራችሁ ርእስ ይመጥናሉ የምትሏቸውን መርጣችሁ መያዝ፤
- ንግግራችሁን መልክ ማስያዝ፤
- በጊዜና በቦታ ቅደም ተከተል ማደራጀት፣
- ፍሬ ሀሳቦችን በሚያነጻጽር መልክ ማደራጀት፣
- ፍሬ ሀሳቦችን በአሃዝ ከፋፍሎ ለማየት በሚያስችል መልክ ማደራጀት፣

**ለ. አቀራረብ**

- የንግግሩን አላማ ባጭሩ ማስተዋወቅ
- ርዕሱን ማስተዋወቅ
- የድምፅ ቃናና አወራረድ፣ ፍጥነት፣ ሐይል፣ መጠን እንዲሁም የአካል እንቅስቃሴ አድማጭን የሚማርክ እንዲሆን መጣር
- የተደራሲያንን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ
- ተደራሲያንን በዐይን መቃኘት
- ንግግሩ የሚያሳስብ የሚያመራምርና የሚያወያይ እንዲሆን መጣር
- ለቃላት ምርጫ ልዩ ትኩረት መስጠት
- በመጨረሻም ከአድማጭ አስተያየት መቀበል

## ክፍል ሦስት፣ ማዳመጥ

**ቀጥሎ የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ጽሑፍ እያዳመጣችሁ የምትመልሷቸው ናቸው:: ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት ጥያቄዎቹን በሚገባ ለመረዳት እንድትችሉ ደጋግማችሁ ከነአማራጮቻቸው አንብቧቸው:: ጽሑፉን ሁለት ጊዜ ስለምታዳምጡ በመጀመሪያው ዙር ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፤ ያመለጧችሁ መልሶች ካሉም በሁለተኛው ዙር አሟሉታችሁ መልሱ::**

1. የወንዱ አባት የልጅቱን ጥሩነት ካጣራ በኋላ፣ የልጅቷን አባት “ልጅህን ለልጄ ስጠኝ” ብሎ የሚጠይቀው ከማን ጋር በመሆን ነው?
   ሀ. ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ለ. ከቃዲዎች፣
   ሐ. ከወንድሞቹ ወይም ከቤተሰቡ አባላት፣ መ. ብቻውን
2. የልጅቷ አባት በዕለቱ የቀረበለትን ጥያቄ ከወደደውና የሚስማማው ከመሰለው ይህንኑ የሚገልጸው ምን በማድረግ ነው?
   ሀ. እሺ! በማለት፣
   ለ. ምግብና ቡና በመጋበዝ፣
   ሐ. ከሳምንት በኋላ ተመለስ በማለት፣
   መ. ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ተመለስ በማለት::
3. ከሚከተሉት በሴቷ ልጅ አባት በኩል ስለጋብቻው የተስማሚነት ምክር የማይጠየቁት የትኞቹ ናቸው?
   ሀ. የሚስቱ እናትና አባት፣
   ለ. እህቶቹና ወንድሞቹ፣
   ሐ. ጓደኞቹና የሀገር ሽማግሌዎች፣
   መ. የራሱ እናትና አባት
4. በፍጥምጥሙ እለት የልጁ አባት፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ቃዲና ቤተሰብ ሆነው በሴት ልጅ አባት ቤት ደጃፍ በመቆም ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ ጥያቄያቸውን ምን በማለት ያቀርባሉ?
   ሀ. “አላህ የሰጣችሁን ልጃችሁን አላህ ለሰጠን ልጃችን ስጡልን ብለን መጥተናል”
   ለ. “አላህ የሰጣችሁን ልጃችሁን ለልጃችን ስጡልን ብለን መጥተናል”

ሐ. "ልጃችሁን አሳህ ለሰጠን ልጃችን ስጡልን ብለን መጥተናል"
መ. "አሳህ የሰጣችሁን ልጅን ልጃችን ስጡልን"

5. የሰማኒያው ውል ምን ተብሎ ይጠራል?
ሀ. ፊቂሃ ለ. ኒካ ሐ. ዝየራ መ. ጃዊ

## ክፍል አራት፣ ሰዋስው

፩. ከዚህ በታች በተሰጡት መሪ ቃላት ተጠቅማችሁ በምሳሌዎቹ መሰረት የተሰደየ ሐረጎችን በመመስረት ዓይነታቸውን ግለጹ።

**ምሳሌ፣**

| ተራ ቁ. | መሪ ቃል | የቃል ክፍል | ሐረግ | የሐረግ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | ተማሪ | ስም | ሰነፍ ተማሪ | ስማዊ ሐረግ |
| ለ | ደፋር | ቅጽል | በጣም ደፋር | ቅጽላዊ ሐረግ |
| ሐ | አለፈ | ግስ | የመግቢያ ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አለፈ | ግሳዊ ሐረግ |
| መ | ወደ | መስተዋድድ | ወደ መማሪያ ክፍል | መስተዋድዳዊ ሀረግ |
| ሠ | ገና | ተውሳከ ግስ | በጣም ገና | ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ |
| 1 | ነቀፈ | ______ | ______ | ______ |
| 2 | ገበሬ | ______ | ______ | ______ |
| 3 | ቀራፒ | ______ | ______ | ______ |
| 4 | ክፉኛ | ______ | ______ | ______ |
| 5 | ስለ | ______ | ______ | ______ |

**፪. በተራ ቁ.፩ በመሰረታችኋቸው ሐረጎች ተጠቅማችሁ አምስት ዓረፍተ-ነገሮችን ጻፉ።**

### ሐረግ

ሐረግ ከቃል የሰፋ ከዓረፍተ-ነገር ያነሰ መዋቅር ነው። እያንዳንዱ የቃል ክፍል ከሌሎች ክፍሎች ጋር እየተቀናጀ ሐረግ ይመሰርታል። ሐረግ በዓይነቱ ስማዊ ሐረግ፣ ግሳዊ ሐረግ፣ ቅጽላዊ ሐረግ፣ ተውሳከ ግሳዊ ሐረግና መስተዋድዳዊ ሐረግ በመባል ተለይቶ ይታወቃል። የሐረግ ዓይነት የሚወሰነው በሐረጉ መሪ ቃል፣ የቃል ክፍል ነው። መሪው ስም ከሆነ ስማዊ፣ ግስ ከሆነ ግሳዊ፣ ቅጽል ከሆነ ቅጽላዊ፣ ተውሳከ ግስ ከሆነ ተውሳከ ግሳዊና መስተዋድድ ከሆነ መስተዋድዳዊ ሐረግ ይባላል።

**፫. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሐረጎች መሪ ቃልና የሐረጎቹን ዓይነት በምሳሌው መሰረት ጽፋችሁ አመልክቱ።**

**ምሳሌ**፣ አንሻ አክስቷን ለመጠየቅ ወደ አዳማ ሄዳለች።

የሐረጉ መሪ ቃል = ሄዳለች

የሐረጉ ዓይነት = ግሳዊ ሐረግ

1. ትናንት የታመመው ተማሪ ወደሆስፒታል ተወሰደ።
2. ወይኒቱ እንደወንድሟ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት።
3. እህቱ ስለመጣች ደስ አለው።
4. ጫልቱ እንደ እህቷ ቶሎ ትከፋለች።
5. አያና የእግር ኳስ ጨዋታ ለመመልከት ስቴዲየም ገባ።
6. የትምህርት ቤታችን የስፖርት መምህር የአትሌቲክስ ውድድር እንደሚያዘጋጁ ነገሩን።
7. ሁሉም ሰው እንደንብ ታታሪ ሠራተኛ መሆን አለበት።
8. ሁሉን በሆዱ የሚይዝ ሰው እራሱን ይጎዳል።
9. በቃጠሎው በጣም የተጎዱ ቤቶች ፈርሰው በአዲስ መልክ እንደገና ተሰሩ።
10. ትናንት ገበያ ውስጥ ያየነው እብድ ተይዞ ወደ አእምሮ ሆስፒታል ተወሰደ።

## ክፍል አምስት፣ ስነጽሑፍ

**፩. የሚከተሉት ቃላዊ ግጥሞች በያዟቸው ቃላት ውስጥ ባሉ ድምጾች መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር፣ እንዲሁም ባንድ ላይ መነበብ ወይም ተነጣጥለው መነበብ የተነሳ የሚመጣውን የፍች ልዩነት በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት ጽፋችሁ አሳዩ።**

**ምሳሌ**፣ እረኛ ነህ አሉ አንተሰው ለዚያ ሰው፣
ባልመጣ በቀረ ብታገኝ መልሰው።

የፍች ለውጥ ያመጣው ቃል፡- **ባልመጣ**

ተነጣጥሎ ሲነበብ፡- **ባል መጣ** (ባለቤቴ መጣ)

መልእክት- 1. ባለቤቴ ስለመጣ ንገረውና ይቅር፤ አይምጣ።
(ተነጣጥሎ በመነበቡ የተገኘ)
2. በዓል ስለመጣ ይቅር። (እዚያው ያክብር)

**ላልቶ ሲነበብ፡-** ባልመጣ (እኔ ብቀር)

**መልእክት፡-** እኔ መምጣቴ በቀረ፤ እሱንም ብታገኘው መልሰው።

1. አውራ ዶሮ ጭሮ እህልሽን ሲያፈሰው፣
   እሽ አለማለትሽ የሚገርም እኮ ነው።
2. ጠላቴ ነህ እንጂ መች ወዳጄ ነህ፣
   አትድረስ ከደጄ አንተን አልይህ።
3. እኔስ ይገርመኛል የዚህ አብነቱ፣
   ባላልቦ ወለደች ልጃገረዲቱ።
4. እመጣለሁ ብሎ ሰው እንዴት ይዋሻል፣
   ማበል እንኳን አንቺን ምድር ያበላሻል።

**፪. ባህላዊ ጋብቻን፣ ሥራንና ፍቅርን የተመለከቱ ሦስት ሦስት በድምሩ ዘጠኝ ቃላዊ ግጥሞችን ከሰዎች፣ ከመገናኛ ብዙኃንና ከመጻሕፍት በመሰብሰብ መልእክታቸውን ተንትናችሁ በጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።**

፫. ከዚህ በታች በባህላዊ ጋብቻ ላይ ያተኮሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ቀርበዋል:: በቡድን ሆናችሁ በይዘታቸውና በሚነገሩበት አውድ ላይ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

1. በሴት የከበረ፣ ከእግዚአብሄር የተማከረ::
2. የሙሽራ እድሜ ቢያጥር፣ የሰርጉ ድግስ ሆነ ለተዝካር::
3. የሙት ቀናተኛ ሚስቴን አደራ ይላል::
4. ያልገደለ ዘማች ያልወለደ አማች::
5. የተቀመጠ ማርና ልጃገረድ የሚሆኑት አያጡም::

፬. ከዚህ በታች በ"ሀ" ስር የሐረሪ ብሔረሰብ ምሳሌያዊ ንግግሮች የአማርኛ ፍችም ቀርቧል:: በ"ለ" ስር ከቀረቡትና በይዘት ከሚመስሏቸው የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ከልጅ ጋር የዋለን ሽማግሌ ሞቶ አገኙት:: | ሀ. ከቁንጫ ሌጦ ያወጣል:: |
| 2. ሙሽራ በጓዳ ወሬዋ ግን በሜዳ:: | ለ. በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል:: |
| 3. ከእባብ አምልጦ ወደ እፉኝት ሩጦ:: | ሐ. ከልጅ አትጫወት ይወጋሀል በእንጨት:: |
| 4. ለመልኳ ያገቧትን ሚስት ላመሏ ፈቷት:: | መ. እናቴን ላህል ዘጠኝ ወር ቀረኝ አለች:: |
| 5. የጠገበች አህያ ጋራ ላይ ትንከባለል:: | ሠ. የሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ:: |
| 6. ከድንጋይ ልጣጭ መፈለግ:: | ረ. ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው:: |
| 7. እናት እያለች ዋጋዋን አያውቁም:: | ሸ. አህያ ቢሰባ ምን ረባ:: |
| | ቀ. የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም:: |
| | በ. አልሸሹም ዘወር አሉ:: |

፭. ምሳሌያዊ ንግግሮች የሌሉት ቋንቋ ይኖራልን? ለምን? መልሳችሁን በማስረጃ በማስደገፍ በጽሑፍ ግለጹ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ “ባህላዊ ጋብቻ” በሚል ርእስ የዘይሴ ብሔረሰብን ባህላዊ ጋብቻ ተመልክተናል፡፡ ጋብቻ ከሚፈጸምበት መንገድ አንጻር ብሔራዊ፣ ሀይማኖታዊና ባህላዊ በመባል በሦስት ተከፍሎ እንደሚታይና ሰዎች ከነዚህ መንገዶች በአንዱ የሚፈጽሙት ጋብቻም ህጋዊ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል መሪ ቃላት ዘር ሆነው እንዴት ራሳቸውን እያሳደጉ ሐረግ እንደሚመሰርቱ ተመልክተናል፤ በመሪ ቃላት ተጠቅመን ሐረጎችን በየዓይነታቸው በመለየት መስርተናል፡፡ ከልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮች እንዴት መረጃ እንደምንወስድ ባየንበት ክፍል የማስታወሻ አወሳሰድ መመሪያን ተከትለን እያዳመጥን፣ እያነበብን ወይም እየጎበኘን ማስታወሻ በመያዝ ለምንፈልገው ዓላማ ማዋልን ተለማምደናል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ የጽሑፍ አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን ተከትለን የጽሑፍ ንግግር አዘጋጅተን አቅርበናል፡፡ በልዩ ልዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች የሚዜሙ የቃል ግጥሞች ይዘትን ተንትነናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብና ይዘታቸውንና የሚነገሩበትን ማህበራዊ አጋጣሚ በመመርመር እንዴት መልእክትን አጉልቶ ለማሳየት እንደሚያገለግሉ አይተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የ "ውርስ ጋብቻ" ያለውን ደካማና ጠንካራ ጎን በክፍል ውስጥ ተነጋገሩበት፡፡
2. በምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ ላይ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡
3. ቀጥሎ የቀረቡትን የተጓደሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች አሟሉ፡፡
   - ሀ. መቼ መጣሽ ሙሽራ ________________________________፡፡
   - ለ. ________________________________ዳቦ ይልሳል፡፡
   - ሐ. ሞኝና ወረቀት ____________________________፡፡
   - መ. __________________________እምብርት የለውም፡፡

4. ለሚከተሉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች ተመሣሣይ ፍች የያዙ ምሣሌያዊ አገጋገሮችን እየፈለጋችሁ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡
   - ሀ. ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ፡፡

     ________________________________________________
   - ለ. ጅብ በማያውቀው ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል፡፡

     ________________________________________________
   - ሐ. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሠንበሌጥ፡፡

     ______________________________________________________
   - መ. አጥብቆ ያሠረ ዘቅዝቆ ይሸከማል፡፡

     ______________________________________________________

5. ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት መጥበቅና መላላት ትርጉማቸው የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡
   - ሀ. ገና
   - ለ. ይመራል
   - ሐ. ይበላል
   - መ. ዋና

## የግንዛቤ ማመሣከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል። በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የቀረበልኝን ምንባብ አንብቤ ተረድቻለሁ | | | |
| 2. | ከምንባቡ ስወጡ ቃላት አውዳዊ ፍች ሰጥቻለሁ። | | | |
| 3. | የድምጽ መጥበቅ፣ መላላት፣ … የሚስከትለው የፍች ልዩነት ተረድቻለሁ። | | | |
| 4. | በመሪ ቃላት በመጠቀም ሐረጋትን መስርቻለሁ። | | | |
| 5. | የተለያዩ ሐሳቦችን በራሴ አባባል ገልጫለሁ። | | | |
| 6. | ከመረጃ ምንጮች ማስታወሻ መያዝ ችያለሁ። | | | |
| 7. | የቃላዊ ግጥሞችን መልእክት መግለጽ ችያለሁ። | | | |
| 8. | ባህላዊ ጋብቻን የሚመለከቱ ቃላዊ ግጥሞችን ሰብስቤ ተንትኛለሁ። | | | |
| 9. | ከባህለዊ ጋብቻ ጋር የተያያዙ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይዘት መግለጽ ችያለሁ። | | | |
| 10. | የጽሑፍ ንግግር በባህላዊ ጋብቻ ዙሪያ በማዘጋጀት ማቅረብ ችያለሁ። | | | |
| 11. | ጭውውት በባህላዊ ጋብቻ ዙሪያ ማድረግ ችያለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ሦስት

# ልቦለድ

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ የረጅም ልቦለድን ምንነትና ባህሪያት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ከምታነቡት ረጅም ልቦለድ መካከል መቼትንና ጭብጥን እየለያችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታቀርባላችሁ፡፡
- ✓ ተራና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ከምታነቡት ረጅም ልቦለድ ውስጥ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን እንዲሁም ሐረጋትን ለይታታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ✓ የአንቀጽ ቅርጾች በኃይለ ቃልና በአረፍተነገሮች አቀማመጥ መሠረት እንደሆነ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ የተሰጣችሁን መመሪያ በመከተል መልመጃዎችን ትሠራላችሁ፡፡

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

**ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ከመምህራችሁ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሠረት በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ የ‹‹ሀ›› እና የ ‹‹ለ›› አምድን አሟሉ፡፡ ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ደግሞ የ‹‹ሐ›› አምድን ሙሉ፡፡**

ምሣሌ

| ‹‹ሀ›› ስለረጅም ልቦለድ ምን አውቃለሁ? | ‹‹ለ›› ከምንባቡ ምን ማወቅ እፈልጋለሁ? | ‹‹ሐ›› ምን አዲስ ነገር ተማርሁ? አውቃለሁ ያልኩትስ ትክክል ነበር? |
|---|---|---|
| ሀ) የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ነው<br>✓ … | ✓ ስለረጅም ልቦለድ ባህሪያት<br>✓ … | |
| ✓ … | ✓ … | |
| 1. … | | |
| 2. … | | |

## ረጅም ልቦለድ

ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረጽ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነጥበብ ሥራ ነው። ልቦለድ በቁሙ እውነት አይደለም ሲባል የተተረከው የገጸ-ባህሪያት ህይወት በእውኑ ዓለም በእርግጥ የተፈጸመ አይደለም ማለት ነው፡፡

ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ ተብሎ በሁለት ዓበይት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡፡ አጭር ልቦለድና ረጅም ልቦለድ በፈጠራ ጽሑፍነታቸው ተመሳሳይነት ሲኖራቸው በመጠን ግን ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡

ረጅም ልቦለድ ስሙ እንደሚያመለክተው ረዘም ያለና በስድ ጽሑፍ የሚቀርብ የፈጠራ ድርሰት ቅርጽ ነው። ረጅም በመሆኑ በሚቀርበው ታሪክ ውስጥ በርካታ ገጸ-ባህሪያትን ማሳተፍ ከመቻሉም በላይ የእነዚህን ገፀ ባህሪያት ህይወት ከልደት እስከ ሞት በስፋትና በጥልቀት ለማሣየት በቂ ቦታና ጊዜ አለው። በዚህ ዓይነቱ የፈጠራ ድርሰት ውስጥ በእውናዊው ዓለም ያሉ ሰዎች የሚገጥሟቸው ደስታና ሃዘን፤ ፍቅርና ጥላቻ፤ ማግኘትና ማጣት፤ ምኞትና ተስፋ፤ ባጠቃላይ የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎችና ልዩ ልዩ አመለካከቶች ለዛ ባለው መንገድ ሰፋ ባለ ሁኔታ እውን መስለው ይቀርባሉ። አንባቢም በታሪኩ የተሳተፈ እየመሰለው ህይወትን እንዲታዘብ፣ የራሱንም ማንነት እንዲያጤንና እንዲመራመር እድል ይሰጣል። አጭር ልቦለድ የራሱ ቅርጽና ይዘት ያለው የፈጠራ ድርሰት ነው። ከረጅም ልቦለድ የሚለይባቸውም ሶስት መሰረታዊ ባህሪያት አሉ። እነሱም ጥድፊያ፣ ነጠላ ውጤትና ቁጥብነት ናቸው። አጭር ልቦለድ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ ወደ ፊት ሲገሠግስ ረጅም ልብወለድ ጊዜ ስላለው አይጣደፍም። አጭር ልቦለድ አንድን ጉዳይ ብቻ መርጦ በትኩረት ሲያይ ረጅም ልብወለድ ግን ብዙ ጉዳዮችን ይዳስሳል። አጭር ልቦለድ ዝርዝር ነገሮችን ከማንሳት ተቆጥቦ በአጭሩ ሲያቀርብ ረጅም ልብወለድ ግን ዘርዝር ባለ ሁኔታ ነገሮችን ለማብራራት ስለሚጓዝ ቁጥብነት አይታይበትም።

*(ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ፣ ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ ለ 11ኛና ለ 12ኛ ክፍል፣ 1999 እና ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፣1992)*

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. በአንድ ልቦለድ ውስጥ የግለሰብ አልያም የማህበረሰብ የህይወት ገጠመኝ ፈጠራዊ በሆነ መንገድ ሊቀርብ ይችላል።

2. በልቦለድ ዓለም የሚሳሉ ገጸባህሪያት በገሃዱ ዓለም ላይ ሲኖሩ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
3. ረጅም ልቦለድ በባህሪው መጠነ ሰፊ በመሆኑ ደራሲው ከአንድ በላይ ጭብጥ የማሳየት እድል ይኖረዋል፡፡
4. የአንድ ልቦለድ ታሪክ በገሃዱ ዓለም ላይ ለመከሰቱ በማስረጃ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡
5. ልቦለድ ሰዎች ካነበቡት ታሪክ ማንነታቸውን እንዲፈትሹ እንዲሁም የህይወትን ገጽታዎች ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱ ንቃተ ህሊናቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛል፡፡

**፪. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ(አቻ) የሆኑትን በ"ለ" ክፍል ከቀረቡት በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ምናብ | ሀ. ገሀድ |
| 2. እውን | ለ. ዝርው |
| 3. ነጠላ | ሐ. ዋና |
| 4. አጤነ | መ. አንድ |
| 5. ዓብይ | ሠ. ሀሳብ |
| | ረ. አገናዘበ |

**፫. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ስለልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ልቦለድ ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት ያለው ሰው በሙሉ ሊጽፈው የሚችለው ጥበብ ነው፡፡
   ለ. የልቦለድ ታሪክ በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡
   ሐ. ልቦለድ በሰው የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴንና ገጠመኝን መሠረት አድርጎ የሚጻፍ የፈጠራ ድርሰት ነው፡፡
   መ. በልቦለድ የማስዋብ ወይም የማጋነን ሁኔታ አይፈቀድም፡፡

2. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል የረጅም ልቦለድ ባህሪይ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ጠባብ መቼት
   ለ. በርካታ ገፀባህሪያት
   ሐ. ከአንድ በላይ ጭብጥ
   መ. ሰፊ የገፀባህሪያት ገለፃ

3. አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ከሚለይባቸው ባህሪያት አንዱ "ቁጥብ" መሆኑ ነው፡፡ የዚህን ዐረፍተ ነገር ሐሳብ የሚያጠናክረው ከቀረቡት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
   ሀ. ነገሮችን ግራ ቀኝ እየመዘነ እና እየገመገመ ታሪኩን ሰፋ አድርጎ ያቀርባል
   ለ. ልቦለድ በሚያነሳው ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮር ይገባዋል፡፡
   ሐ. የገፀባህሪያትን አካላዊና ህሊናዊ ሁኔታ ባልተቆጠበ መንገድ ያቀርባል፡፡
   መ. ታሪኩ ሰፋ ያለ ጊዜና ቦታን ይጠይቃል፡፡

4. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች መካከል ስለ አጭር ልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የአጭር ልቦለድ ገፀባህሪይ በታሪኩ ውስጥ በርካታ ግጭቶች ይገጥሙታል፡፡
   ለ. አጭር ልቦለድ ደራሲው የራሱን ፍልስፍና ዘርዘር አድርጎ እንዲያቀርብ ያስችለዋል፡፡
   ሐ. አጭር ልቦለድ የረጅም ልቦለድ አንድ ምዕራፍ ሊሆን ይችላል፡፡
   መ. የአጭር ልቦለድ ጭብጥ ነጠላ /አንድ/ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ጭውውት

"በእውኑ ዓለም በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የሐሳብ ወይም የንግግር መለዋወጥ አለ፡፡ ሁለት ሰዎች ባላቸው ግንኙነት መሠረት በየአጋጣሚው የሆነ ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩና ሐሳብ ለሐሳብ ሲለዋወጡ እንሰማለን፡፡ እንዲህ ያለው የሐሳብ መለዋወጥ በልብወለድ ገፀ ባህርያትም ይደረጋል፡፡ ይህም የሐሳብ መለዋወጥ ምልልስ /ጭውውት/ በመባል የሚታወቀው ነው፡፡"

*ምንጭ (ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሑፍ መሠረታውያን፣ (2000)፡፡*

፩. መምህራችሁ በሚጠቁሟችሁ አንድ ረጅም ልብወለድ ውስጥ በምልልስ (ጭውውት) መልክ የቀረበውን አንድ ክፍል በአንድ ገጽ ላይ ቀንጭባችሁ በጽሑፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

፪. በምልልስ የቀረበ የአንድ ልቦለድ ታሪክ መርጣችሁ አንብቡና በቡድን ሆናችሁ በመለማመድ ክፍል ውስጥ በጭውውት መልክ አቅርቡ።

፫. በምዕራፍ አንድ ላይ በተማራችሁት መሠረት የሚከተሉትን ሀቅ አዘል ዓረፍተ ነገሮች ወደ ግል አስተያየት ለውጣችሁ ተናገሩ።

1. ብዙዎቹ ጋዜጠኞች ሙያዊ ስልጠና ወስደዋል።
2. ጋዜጣ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የመገናኛ ብዙኃን ዘርፎች ናቸው።
3. በሬዲዮ ከሚቀርበው ዜና ይልቅ በቴሌቪዥን የሚቀርበው የተሻለ መረጃ ይሰጣል።
4. ህዝባዊ ድጋፍ የሌላቸው መገናኛ ብዙኃን ዓላማቸውን ማሳካት ይሳናቸዋል።
5. ማንኛውም ሰው መረጃ የመስጠትና የመቀበል መብት አለው።

## ክፍል ሦስት፡- መጻፍ

### ከመጻሕፍት መረጃ ማግኘትና ማስታወሻ መውሰድ

ከልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮች ሃሣቦችን ማግኘት ይቻላል። ከነዚህ ውስጥ ከመጽሐፍ የምናገኘው መረጃ አንዱና ዋነኛው ነው። ቤተ መጽሐፍት ውስጥ በመሄድ የካርድ ካታሎግ አፈላለግ ሥርዓትን ከኃላፊው/ዋ ጠይቆ በመጠቀም የምንፈልገውን መረጃ ማግኘት እንችላለን። በዚህም ወቅት በማስታወሻችን በአጭር በአጭሩ ፍሬ ሃሣቡን፡-

ሀ. በሐረግ ደረጃ፣

ለ. በዓረፍተ ነገር ደረጃ መያዝ ይኖርብናል።

ይህ ተግባር ከጋዜጣ፣ ከመጽሔቶች፣ ከንግግር አድራጊዎች፣ ወዘተ ማስታወሻ በምንወስድበት ጊዜም ይጠቅመናል። ይህን የወሠድነውን ማስታወሻ ደጋግመን በማንበብና በስርዓት በማጠናቀር ለፈለግነው ጉዳይ በመረጃነት ልንጠቀምበት እንችላለን።

*(በደበበ ኃ/ጊዮርጊስ እንግዳ ፣ ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ፣ (1999)።*

**፩. ቀጥሎ የቀረበው አንቀጽ ሲያስተላልፈው የፈለገውን መልዕክት ከሁለት ዓረፍተ ነገሮች ባልበለጠ አሳጥራችሁ ጻፉና ተወያዩበት፡፡**

በባህሮችና በተራራዎች ላይ ባሉት ከተሞችና ሜዳዎች የሚታየው ነገር ሁሉ ያስጎመጃል፡፡ ሲያዩት ከቶ አይሰለችም፡፡ ተክሎችና አበባዎች፣ ዛፎች፣ ፍሬዎች፣ ስዕሎችና ቅርጾች፣ በብዙ ዓይነት ቋንቋ የተጻፉ ጋዜጣዎችና ልዩ ልዩ የሆኑ መጻሕፍት፣ ፋብሪካዎችና ማዕድኖች፣ መንገዶች፣ በየሱቁ የሚታዩት እቃዎችና የውበት መደብሮች ሁሉ ሲያዩዋቸው የሰው እጅ ያልዳሰሳቸው ይመስላሉ፡፡


## የአንቀጽ ቅርጾች

በጥሩ ሁኔታ የተጻፉ አንቀጾች ሁሉ ኃይለቃል አላቸው፡፡ ኃይለቃል የአንቀጽን ማእከላዊ ሃሳብ የያዘና አብዛኛውን ጊዜ በአንቀጹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ዓረፍተነገር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን እንደ ጸሐፊዎች ምርጫ ኃይለቃሉ በአንቀጹ መሃል ወይም መጨረሻ ላይም ሊመጣ ይችላል፡፡ ኃይለቃል፣ ርዕሳዊ ዓረፍተነገር፣ መሪ ዓረፍተነገር፣ መንደርደሪያ ዓረፍተነገር የሚሉ ስያሜዎች አሉት፡፡


አልፎ አልፎ የአንቀጹን ርዝማኔ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ኃይለቃሉን በአንቀጽ ውስጥ ሁለት ጊዜ ማቅረብ የማቻልበትም መንገድ አለ፡፡ ሆኖም ሁለቱ ኃይለቃሎች በተለያየ መልክ /አባባል/ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

የአንቀጽ ቅርጾችም በኃይለቃሉ መገኛ ቦታ ይወሰናሉ፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕላዊ መግለጫዎች ለአብነት እንመልከት፡፡


ሀ. <u>ኃይለ-ቃል</u> በስተመነሻ





ለ. <u>ኃይለ-ቃል</u> በስተመድረሻ




ሐ. <u>ኃይለ-ቃል</u> በስተመነሻና በስተመድረሻ




መ. <u>ኃይለ-ቃል</u> በመሃል




**፪. ቀጥለው የቀረቡላችሁን ምንባቦች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በተማራችሁት መሠረት የአንቀፅ ቅርፃችን አመልክቱ፡፡**

ምንባብ 1

እስክንድር ራሱን አከከ፡፡ ሰው ሰራሽ ጥርሱንም ወደ ውስጥ ገፋ አደረገ፡፡ ከሲራክ ባሻገር መስኮቱን ዘልቆ ሩቅ ተመለከተ፡፡ ዐይኑ፣ ከአድማስ ጋር

ተጋጨ። የነበረው ተሰጥዖ ከጉም ጋር በንኖ ሲጠፋ ታየው። አንድ ወር፣ ግፋ ቢል ሁለት ወር… ስሙን የያዘው መጽሐፍ ታትሞ… ሰው እጅ ገብቶ ሲነበብ ለማየት የነበረው ተስፋ፣ ይታየው የነበረው ጣፋጭ ሕልም… በሲራክ ክፋት ምክንያት… ድንገት መጥፎ ቅዠት ሆኖ ሲቀር… ደብዛው ሲጠፋ…ሲጨልም… የጋራ ስሜቱ ከስሎ አመድ ሲሆን ታየው። ሕይወት መራራ ሆነችበት፣ ሲራክን ከልቡ ጠላው። ልቡን በጦር ቢወጋውም ምንኛ ደስ ባለው ነበር።

## ምንባብ 2

"ነፍጠኞች ለምዳቸውን እየደረቡ በጢስ የበለዘ ጋሻና ጦር ይዘዋል። ጎልማሶች የክትክታ ቆመጥና የወይራ ዱላ ይዘዋል። መቆነን የሚያበዙት እነዚያ የጐንደር ደብተሮች እንደመልካም ክፍክፍ ጥምጥማቸውን ቀሽረው ጭራቸውን እያወዛወዙ እርስ በርሳቸው በማንጎራጎር በጓድ በጓድ ይከማቻሉ። ወዲያውኑ ከፋሲል ግንብ አንስቶ እስከ ጉፋያ መስጫ ድረስ ሕዝብ ጥቅጥቅ ብሎ መላ ጥቁር ቆብ፣ ቢጫ ቆብ፣ ክምር ጥምጥም፣ የሚያንፀባርቅ በራ፣ በቅቤ ወዝ የሚጭረቀረቅ ቁንዳላ፣ ከቆብ አስጥሉ ላይ ሆኖ ለተመለከተ የሚታየው የሰው ጭንቅላት ብቻ ነበር። አንዳንዱ የባሰበት በመዳፉ ጮራዋን ሲጋርድ ሁሉም አንጋጦ የፋሲልን ግንብ ሰገነት ይጠባበቃል። ጎንደር ተሞሽራ ሙሽራዋን ትጠብቃለች። ከሕዝቡ ብዛት ጋር ሲመዛዘን ብዙ ድምጽ አልነበረም። ነጋሪቱ ብቻ "ገብር፣ገብር" እያለ ያስተጋባል። ድንገት ቀጥ አለ አካባቢውን ፀጥታ ዋጠው። ሰው ከተረከዙ ወደጣቱ፣ ከአንድ እግሩ ወደሌላው በመንቆራጠጥ በያለበት ይቁነጠነጥ ጀመር። ወደላይ አንጋጦ የሚጠባበቀው ሕዝብ ስሜት በገሀድ የሚታይ ቢሆን ኖሮ ክንፍ አውጥቶ የሚበር በመሰለ ነበር። ከዚያም ያደገደገ ጥቁር ጎፈሬ በጥቂት ሰዎች ታጅቦ ወጣና የተጠቀለለውን ብራና ገልጦ አነበበ።

## ምንባብ 3

ሶፍያና ጽጌ መንታዎች ናቸው። እናታቸው ብርሃነ በተወለደች በአሥራ ሦስት ዓመቷ አግብታ በአሥራ ስድስት ዓመቷ እነሱን ወለደች። መንትዮቹ ከተወለዱ በኋላ አራት ቀን ብቻ ቆይታ ሞተች። አባታቸውም

ተድላ የሚስቱ ሬሳ ሲወጣ አብሮ እንደወጣ የደረሰበት አልታወቀም። ስለዚህ ሶፍያን ደብረሊባኖስ ገዳም መንኩሰው የሚኖሩ እማሆይ ጥሩነሽ የሚባሉ የእናቷ ታላቅ እህት ወስደው ያሳድጓት ጀመር። ተዋበችም በኃይሉ ደበበ የሚባል የአባቷ ታላቅ ወንድም በእድሜው ከእሷ ምንም ያህል ከማይበልጥ ዮናታን ከሚባል ልጁ ጋር አብሮ ያሳድጋት ጀመር።

## ምንባብ 4

ዮፍታሔ ለሁለተኛ ጊዜ ኤልያስን ላይመለስበት ጥሎ የወጣው በእናቱ ምክንያት በተፈጠረው ሐሜት ነበር። ቄሰ ገበዝ ንጉሴና ወይዘሮ ማዘንጊያ የተጋቡት ሥርዓተ-ተክሊል ደርሶላቸው ሥጋ-ወደሙ ተቀብለው ነበር። ሞት ቢለያቸውም ሕጋቸው እንደፀና ይኖራል እንጂ መፍረስ አልነበረበትም ሕጋዊ ባላቸው በሞት ሲለዩዋቸው መንኩሰው፣ እማሆይ ተብለው ባይመነኩሱም ሕጋቸውን አክብረው፣ አጽንተው ጊዜ ሞታቸውን መጠበቅ ነበረባቸው። እሳቸው ግን ይህን አላደረጉም። ከባላቸው አንፃር ገና ወጣት የሚባሉ፣ የደም ገንቦ የሆኑ ወይዘሮ፣ በዚህም ላይ ደግሞ ሙቀት ልምላሜ ያልጠፋባቸው ቀበጥ ሴት ስለነበሩ ህጋዊ ባላቸው እንደሞቱ በመመንኮስ ወይም አድበው፣ ጨምተው በመቀመጥ ፈንታ እንደሚባለውም ብዙ ሳይቆዩ ሕጋቸውን አፈረሱ። የቄሰ ገበዝ ንጉሴ ቤተሰብ ተበጠበጠ፣ ተከፋፈለ። የኤልያስም ሕዝብ፣ በተለይ የደብተራው ወገን ደህና አድርጎ ዘፈነበት። ይህም አሳዛኝ ሁኔታ ሥሱ በሆነው በዮፍታሔ ስሜት ውስጥ የኀዘንና የብስጭት ማዕበል ፈጥሮ ሕሊናውን እንደመታው መንፈሱን እንዳቃጠለው፣ ነፍሱን እንዳዋከባት ማስተዋል አያዳግትም። ደብተራውና የቅኔ ባልንጀሮቹ የዘፈኑበት በተራ ግጥም አይደለም። በለዘበ፣ በረቀቀ፣ ሲያቃጥል፣ ጠቅ ሲያደርግ፣ በሚያንገበግብ፣ ቅስም በሚሰብር፣ ውቃቢ በሚገፍ ቅኔ ሳይሆን አልቀረም። በቅኔ መሰደብ ቀላል ነገር አይደለም። በተለይም በጥበቡ፣ በኪኑ ታሽቶ ላደገው ብሩህ ለሆነው ለዮፍታሔ የማይዋጥ ነገር ሆነ። በእናት ምክንያት የተጀመረው ሐሜት በልጅ ስደት ተፈጸመ።

## ክፍል አራት:- ሰዋስው

### አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት

አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ቃላትን ከቃላት፣ ሐረጋትን ከሐረጋት፣ ዓረፍተ ነገሮችን ከዓረፍተ ነገሮች ወዘተ. የሚያያይዙ ወይም የሚያሸጋግሩ ቃላት ማለት እንደሆኑ ብዙ ጸሐፍት ጽፈዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ባየ ይማም በ2002 ካሳተሙት "አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው" ውስጥ የሚከተለው ይገኛል፡፡

- አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት (ሐረጋት) የሚጠቁሙት ነገርን፣ ድርጊትን፣ ባህሪን ወዘተ አይደለም፡፡ በመሆኑም በራሳቸው ትርጉም የላቸውም ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ተግባር አላቸው፡፡ ተግባራቸው ከስም በፊት ወይም በኋላ መገኘትና ስሙን ከሌላ ነገር ጋር ማዋደድ ወይም ማያያዝ ነው፡፡ እንዳገባባቸው ዓይነት፣ ከስም በፊት ወይም በኋላ የሚገቡ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ከስም በፊት የሚገቡት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| አያያዥ ቃል | ምሣሌ |
|---|---|
| ስለ | ስለ ገንዘብ |
| እንደ | እንደ ሰው |
| ወደ | ወደ ጎጃም |
| እስከ | እስከ መርካቶ |

- ከስም በፊትና በኋላ የሚገቡት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

| አያያዥ ሃረግ | ምሣሌ |
|---|---|
| ከ ___ አጠገብ | ከ ተማሪ አጠገብ |
| ከ ___ ማዶ | ከ ወንዝ ማዶ |
| ከ ___ ወዲህ | ከ አጥሩ ወዲህ |
| እስከ___ ድረስ | እስከ ጐጃም ድረስ |

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ፡፡**

1. *መምህራችሁ በሚያዟችሁ አንድ ረጅም ልብወለድ ከሚገኝ አንድ ምዕራፍ በተከታታይ ሁለት ገጾች ውስጥ የሚገኙትን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡*
2. *ያገኛችኋቸውን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ከላይ ባያችኋቸው ምድቦች ውስጥ በመከፋፈል ዘርዝራችሁ አሳዩ፡፡*

## የዓረፍተ ነገር ዓይነቶች

ዓረፍተ ነገር ማለት በሥርዐት ተቀነባብሮ ሙሉ ስሜትን ሊሰጥ የሚችል የቃላት ወይም የሐረጋት ስብስብ ነው፡፡ ዓረፍተ ነገሮች ተራ ወይም ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. **ተራ ዓረፍተ ነገር፡-** ከአንድ ስማዊ ሀረግና ከአንድ ግሣዊ ሐረግ ብቻ ይዋቀራል፡፡

   **ምሳሌ፡-** ታፈሰ    ሣር አጨደ፡፡
   ስሐ    ግሐ

2. **ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፡-** ይህ ዓረፍተ ነገር ከአንድ በላይ ማሰሪያ አንቀጽ የያዘ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ዋናው መለያው በውስጡ የያዘው የግስ መጠን ነው፡፡ ይህን ለመረዳት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡
   ሀ. ልጁ ምሳውን በላ፡፡
   ለ. ልጁ ወደ ት/ቤት ሄደ፡፡

እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች በተለያየ መልክ በማጣመር ወደ ውስብስብ ዐረፍተ ነገር መለወጥ ይቻላል፡፡

ስ.ሐ    ግ.ሐ

**ምሳሌ ፡-** 1. ልጁ ምሣውን በልቶ ወደ ት/ቤት ሄደ፡፡
2. ልጁ ምሣውን እንደበላ ወደ ት/ቤት ሔደ፡፡

**፪. ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች "ተራ" ወይም "ውስብስብ" በማለት መልሱ፡፡**

*ሀ. ያ ልጅ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡ ____________________*
*ለ. አስቴር አባቷ ስለመጡ ተቀበለቻቸው፡፡____________________*

ሐ. ከበደ ከመቀመጫው ፈጥኖና በርግጎ ተነሳ፡፡ ___________

መ. ወንድሙ ወደውጭ ሀገር ስለሄደ ቶሎሳ አዘነ፡፡ ___________

ሠ. ህጻን ልጅ ወተት በጣም ይወዳል፡፡ ___________

## የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንጻር ስንመረምራቸው ሁለት ጠባዮች ይታይባቸዋል፡፡ ከእነዚህም አንዱ የመዝገበ ቃላት ወይም ቀጥተኛ ፍች የመያዛቸው ጠባይ ሲሆን ይህም እማሬያዊ ፍች ይባላል፡፡ ሁለተኛው ቃላት ከቀጥተኛ ፍቻቸው በተጨማሪ በተደራቢነት የሚይዙት ምስጢራዊ ወይም ስውር ፍች ሲሆን ይህም ፍካሬያዊ ፍች ይባላል፡፡

**ምሳሌ**

| ተ.ቁ | ቃል | እማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1 | መሬት | ምድር፣ ዓለም | ቻይ |
| 2 | ዶማ | መሬት መቆፈሪያ የእጅ መሳሪያ | የማይገባው |
| 3 | መሰላል | መወጣጫ | ረጅም/ቀውላላ |
| 4 | መብረቅ | ብልጭታ ነጎድጓድ | ኃይለኛ አስደንጋጭ |

፬. ከላይ የቀረበውን ማብራሪያና ምሳሌ መሠረት በማድረግ በሰንጠረዡ ውስጥ ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ሙሉ፡፡

| ተ.ቁ | ቃል | ዕማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1 | እርግብ | | |
| 2 | አመድ | | |
| 3 | እባብ | | |
| 4 | እሾህ | | |
| 5 | እሳት | | |
| 6 | ቆቅ | | |
| 7 | ምላጭ | | |

# ክፍል አምስት:- ሥነጽሑፍ

## የልቦለድ አላባውያን

የልቦለድ አላባውያን የሚባሉት ታሪክ፣ ትልም፣ ገጸባህሪይ፣ ግጭት፣ መቼት ጭብጥ እንዲሁም አንጻር የተሰኙት ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ መቼት እና ጭብጥን እንመለከታለን፡፡

**መቼት**:- ‹‹መቼት›› የሁለት ቃል ጥምረት ነው፡፡ ቃላቱም ‹‹ መቼ?›› እና ‹‹የት?›› የሚባሉት ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት፣ የልቦለድ መቼት ሲባል ታሪኩ የተፈጸመበት ዘመንና ቦታ ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ:-** ሰፈራችን እንደሸረሪት ድር ተወሳስበው የቂርቆስን ቤተክርስቲያን ከከበቡት ቤቶች የበስተ ምስራቁን አቅጣጫ ይዛ ተመስርታለች፡፡ … ዓሳ ይመስል ከተንሿጠጠች ቤቴ ወጣሁ:: ቀኑ ጨፍግጎታል፡፡ የቂርቆስ ቤተክርስቲያን ጥንጁት እንደሚታጠን ጋን ጉም ያንዣብብ በታል፡፡ ዞር ብዬ ቤቴን አየኋት፡፡ …

*/አለማየሁ ገላጋይ፣ ቅበላ 2001፣3::/*

ከላይ ባየነው ምሳሌ የታሪኩ አካባቢ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ይኸውም የገጸ ባህሪው የመኖሪያ አካባቢ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ እንደሆነ በትረካው ተነግሮናል፡፡ የጊዜው ጨፍጋጋነትም ተጠቁሟል፡፡

**ጭብጥ**:- ደራሲው በህብረተሠቡ ውስጥ ያየውን፣ የታዘበውን፣ የተገነዘበውን ማህበራዊ ጉዳይ በማንሳት አመለካከቱን እውቀቱን መሠረት አድርጎ በልቦለዱ አንድ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ ይህ ደራሲው እንዲተላለፍ የፈለገው ፍሬ ነገር ጭብጥ ይባላል፡፡

ጭብጥን ለይቶ ለማውጣትና ለመገንዘብ ከባድ ነው፡፡ በአንድ ቦታ ወይም አንቀጽ ላይ ቁልጭ ብሎ አናገኘውም፡፡ አንባቢ ታሪኩን አንብቦ ሲጨርስ በታሪኩ ከቀረቡ የተለያዩ የገጸ ባህሪያት ንግግሮችና አስተያየቶች መነሻነት ጭብጡን ፈልቅቆ ሊያወጣና ሊገነዘብ ይችላል፡፡

፩. መምህራችሁ የሚጠቁሟችሁን አንድ ረጅም ልቦለድ አንብባችሁ የልቦለዱን መቼት እና ጭብጥ በመለየት ክፍል ውስጥ አቅርቡ።

፪. ቀጥሎ የቀረቡትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ግለጹ።

| | |
|---|---|
| ሀ. አሳሩን በላ። | ረ. እጀ-ሰባራ፣ |
| ለ. ፀጉር ስንጠቃ፣ | ሰ. ክንዱን ተንተራሰ። |
| ሐ. ፊቱን ነጨ። | ሸ. አራስ ነብር፣ |
| መ. ሰው ሆነ። | ቀ. ሱሪ ባንገት፣ |
| ሠ. እንባ ጠባቂ፣ | በ. ነፈሰበት። |

፫. ከተለያዩ ጽሑፎች ፈሊጣዊ አባባሎችን ከነፍቻቸው በመፈለግ ሰብስባችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ፈሊጣዊ አነጋገር

ፈሊጣዊ አነጋገር ማለት አንድ ሐሳብ ከመደበኛው/ከቀጥታ/ አገላለጥ በተለየ መልኩ ክብደትና ውበትን ተጎናጽፎ ለአድማጭ እንዲደርስ የሚያደርግ የአነጋገር ስልት ነው። ፈሊጦች የተናጋሪውን ቋንቋ ውበትና ለዛ በማላበስ የአድማጭን ስሜት የሚኮረኩሩ ቅመሞች ናቸው።

**ምሣሌ፡-** ተናደደ ለማለት ደሙ ፈላ፣ ፊቱ ቀላ፣ አበደ፣ የሚሉትን ፈሊጦች እንጠቀማለን።

ፈሊጥ አንድ ቃል ብቻውን ወይም ቃልና ቃል የሚመሰርቱት ሊሆን ይችላል።

**ምሳሌ፡-** ፊት ነሣኝ /አገለለኝ፣ አራቀኝ/
ለዋሳ /ልፍስፍስ/
ሰማይ ቅርቡ /ወሬኛ፣ የተግባር ሰው ያልሆነ/
ቀኝ እጅ /መከታ፣ አለኝታ/

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር የረጅም ልብወለድ ምንነትና ከአጭር ልብወለድ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በንጽጽር ለማየት ችለናል፡፡ በልብወለድ ውስጥ መቼትንና ጭብጥን ለይተን የማውጣት ልምምድ ሰርተናል፡፡ የተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ምንነት፣ ከተሰጠ ጽሑፍ ውስጥ ደግሞ ተራና ውስብስብ በማለት ዓረፍተ ነገሮችን ለይተን አስቀምጠናል፡፡ የቃላት እማሬያዊ ፍች ማለት ጥሬ ፣ የዘወትር ወይም ግልጽ ትርጉም ማለት እንደሆነ ፤ ፍካሬያዊ ፍች ማለት ደግሞ ቃላት ካላቸው እማሬያዊ ትርጉም በተጨማሪ ይዘውት የሚመጡ ተጨማሪ ትርጉም እንደሆነ ለማየት ችለናል፡፡ መሸጋገሪያ ቃላትንም ሆነ አያያዥ ቃላትንና ሐረጋትን ከጽሑፍ ውስጥ ለይተን ማውጣት ተለማምደናል፡፡ የአንቀጽ ቅርጽንም ትርጉም ተረድተን የተሰጡ አንቀጾችንም አንብበን በስዕላዊ መግለጫ ማስቀመጥም ችለናል፡፡ በመጨረሻም ፈሊጣዊ ንግግሮች እንዴት እንደሚመሰረቱና ፍቻቸው ምን እንደሆነ እየተረጐምን መለማመዳችን ይታወሳል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ያነበባችኋቸውን ልቦለዶች ረጅምና አጭር ልብወለድ በሚሉ አምዶች ሥር ዘርዝራችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡
2. ካነበባችሁት ረጅም ልብ ወለድ ወይም በሬድዮ ከተከታተላችሁት የረጅም ልብወለድ ትረካ ውስጥ የአንዱን ጭብጥና መቼት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡
3. ተራ ዓረፍተነገር ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ በመስጠት አስረዱ፡፡
4. ውስብስብ ዓረፍተነገር ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ ስጡ፡፡
5. የሦስት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በንጽጽር ዓረፍተነገር በመሥራት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡
6. በሚከተሉት አያያዡና የመሸጋገሪያ ቃላት /ሐረጋት/ ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡
   ሀ. እንጂ ለ. ከዚያም በኋላ ሐ. ቢሆንም
7. የሚከተሉትን ፈሊጣዊ ንግግሮች ትርጊሜ በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸው፡፡
   ሀ. የትየለሌ ለ. አጉራ ዘለል ሐ. ኩታ ገጠም
   መ. አውራ ሴሊት ሠ. ሥጋ ለስጋ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል። በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለልቦለድ ምንነት የሚያስረዳውን ምንባብ ሀሳብ ተረድቻለሁ። | | | |
| 2. | የረጅም ልቦለድንና የአጭር ልቦለድ ምንነትና ልዩነት ተገንዝቤአለሁ። | | | |
| 3. | የመቼትንና የጭብን ምንነት ለይቻለሁ። | | | |
| 4. | ተራና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መለየትና መጻፍ ችያለሁ። | | | |
| 5. | ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እሰጣለሁ። | | | |
| 6. | አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን ለይቻለሁ። | | | |
| 7. | እውነታና የግል አስተያየት የሆኑትን ለይቻለሁ። | | | |
| 8. | የተለያዩ የአንቀጽ ቅርፃች መኖራቸውን አውቄአለሁ። | | | |
| 9. | በኃይለ ቃልና በዝርዝር ዓረፍተነገሮች መካከል ልዩነት እንዳለ ተረድቻለሁ። | | | |
| 10. | ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች እሰጣለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ አራት

## ማሕበረሰብና ጤና

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ ለቃላት ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ::
- ✓ ዓረፍተ ነገሮችን በየስልታቸው ትጽፋላችሁ::
- ✓ ከግስ የተለያዩ ስሞችንና ቅጽሎችን ትመሠርታላችሁ::
- ✓ ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅሶችን በተገቢ ቦታቸው ትጠቀማላችሁ::
- ✓ ቃለ ጉባኤ ትጽፋላችሁ::
- ✓ መመሪያ ተከትላችሁ ውይይትና ጭውውት ታካሂዳላችሁ::
- ✓ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ታዘጋጃላችሁ::
- ✓ መመሪያዎችን ተከትላችሁ የተለያዩ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ::

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ለአንድ ማህበረሰብ ጤና መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ? ሀሳባችሁን ዘርዝር አድርጋችሁ ተናገሩ፡፡
2. የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ምን ምን ጉዳዮችን የሚዳስስ ይመስላችኋል?
3. የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለማሕበረሰባችን በተለይ ለወጣቱ መሠጠቱ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ወጣቱና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት

የስነ ተዋልዶ ጤናን በሚመለከት ማንኛውም ሰው መረጃና ትምህርት የማግኘት መብት አለው፡፡ መረጃዎቹ በትምህርት ቤቶች፣ በመገናኛ ብዙኃንና በየአካባቢያችን ባሉ የጤና ድርጅቶች አማካኝነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተቋሞች ኃላፊነት ቢኖርባቸውም መረጃና ትምህርቱን ተከታታይነት ባለው መንገድ በተገቢው መጠን አድርሰዋል ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ለዚህ ደግሞ ዛሬም ድረስ በቤተሰብ ውስጥ ስለ ጾታዊ ግንኙነት በግልጽ የመወያየት ባህል አለመኖሩ እንደ ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ስነ-ተዋልዶ ጤና ማለት ከማንኛውም ስነ-ወሲባዊና ከሰው ልጅ መራቢያ አካላት ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የጤና ዘርፍ ሲሆን ሰዎች በአካልና በአእምሮ መጎልመስ በሚጀምሩበት ወቅት በተፈጥሮና በአካባቢያዊ ሁኔታዎች መገፋፋት በሚፈጽሙት ድርጊት አማካይነት በመራቢያ አካላት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችንም ይዳስሳል፡፡ ስነ-ተዋልዶ ጤና ከጤና ባሻገር የአንድ ማህበረሰብ አደረጃጀት፣ ዝንባሌ፣ ባህሪይ በግለሰብ በቤተሰብና በህብረተሰብ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ማጤን የምንችልበት የጤና ዘርፍ ነው፡፡

**ተማሪዎች አስቀድማችሁ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ምን ነጥቦችን አገኛችሁ? የስነ ተዋልዶ ጤና በቀጥታ ከወጣቶች ጋር የሚያያዘው ለምን ይመስላችኋል?**

የወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና ትርጉም ከወጣቶች አካላዊ እንዲሁም አእምሮአዊ እድገትና ብስለት፣ በወጣቶችና በቤተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ጨምሮ ከጾታ እኩልነት፤ ከቤተሰብ አመሰራረትና እንዲሁም በፍቅር ጓደኛሞች መካከል ከሚኖረው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የስነ ተዋልዶ ጤና መረጃ ለወጣቶች አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ወጣትነት የህይወት ምዕራፍ የሚጀመርበት ወሳኝ ጊዜ እንደ መሆኑ ፈታኝ ባህሪዎች የሚገጥሙበት፤ የስሜት ተለዋዋጭነት፣ ችኩልነት እና የአቻ ግፊት የሚበረታበት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ከላይ በተዘረዘሩት ጫናዎች ህይወታቸው እንዳይሰናከልና መንገድ እንዳይቀሩ ኑሯቸውን በትክክለኛና በስኬታማ መንገድ ለመምራት ይችሉ ዘንድ በጉዳዩ ዙሪያ ሰፊና ጥልቅ የሆነ መረጃ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ መልሶቻቸውን በቃል ተናገሩ፡፡**

1. የስነ-ተዋልዶ መረጃ በተለይ ለወጣቱ የሚያስፈልግበት ምክንያት ምንድንነው?
2. የስነ-ተዋልዶን መረጃ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው እነማን ናቸው?
3. የስነ-ተዋልዶ መረጃ ትምህርት በተገቢው መንገድ ተዳርሷል ለማለት የማያስችለን ጉዳይ ምንድንነው?
4. ወጣቶች የስነ ተዋልዶ ጤና መረጃን በበቂ ሁኔታ ባለማግኘታቸው ለምን ዓይነት ማህበራዊ ቀውስ ይጋለጣሉ?

**፪. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በ ‘ሀ‘ ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በ ‘ለ‘ ክፍል ከተዘረዘሩት በፍች የሚስማማቸውን መርጣችሁ አዛምዱ::**

| ‘ሀ‘ | ‘ለ‘ |
|---|---|
| 1. ፈታኝ | ሀ. እኩያ |
| 2. ዝንባሌ | ለ. ክፍል |
| 3. ዘርፍ | ሐ. ፍላጎት |
| 4. ግፊት | መ. ህቡዕ |
| 5. አቻ | ሠ. ጫና |
| | ረ. አስቸጋሪ |

**፫.ቀጥሎ የሚቀርቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በ ‘ሀ‘ ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በፍች ተቃራኒ የሆኑትን ከ ‘ለ‘ ክፍል በመምረጥ አዛምዱ::**

| ‘ሀ‘ | ‘ለ‘ |
|---|---|
| 1. መብት | ሀ. ቋሚ |
| 2. ብዙሀን | ለ. ደከመ |
| 3. በረታ | ሐ. ጥቂት |
| 4. ተለዋዋጭ | መ. ግዴታ |
| 5. ግልጽ | ሠ. ስውር |
| | ረ. ዳበረ |

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

**፩. የሚከተሉትን መልመጃዎች በመመሪያው መሠረት ሥሩ::**

ሀ. በጭውውት፣ በውይይት ወይም በትምህርታዊ ጉባኤዎች ላይ በመገኘት ማስታወሻ ይዛችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ::

ለ. ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያነብቡላችሁን መመሪያዎች አዳምጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ አስፉሩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

**ሐ. ማህበረሰብና ጤናን በተመለከተ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር በጽሑፍ አዘጋጁና በክፍል ውስጥ በንባብ አቅርቡ።**

### የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር

የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ሰዎችን ወደአንድ ወደተፈለገ ጉዳይ ለመሳብ፣ ለማግባባት እንዲሁ/ ለማነሳሳት ታልሞ የሚደረግ የንግግር ዓይነት ነው።

የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር በፖለቲካ ተቋማት፣ በእምነት ተቋማት፣ በተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ በግለሰቦች... ሊደረግ ይችላል። ተቋማቱ ወይም ግለሰቦቹ አድማጮቻቸው በማነቃቂያ ንግግራቸው ተማርከው ወደ እነሱ እንዲቀርቡ የዓላማቸው ደጋፊ፣ ተከተይ ወይም ደንበኞቻቸው እንዲሆኑ ይሰብካሉ፤ ይቀሰቅሳሉ።

የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ሲቀርብ የንግግሩ ትኩረት በቀጥታ በሚነሳው ጉዳይ ላይ ሰዎችን ለመቀስቀስና የማነቃቃት በመሆኑ የሰዎችን ስሜት በሚነካ በቀላሉ ሊረሳ በማይችል በተዋበና በተመረጠ ቋንቋ በአጭሩ መቅረብ ይኖርበታል።

**፪. ቀጥሎ አጠር ያለ ጽሑፍ ይቀርብላችኋል። ከቀረበው ጽሑፍ ውስጥ እውነታ እና የግል አስተያየት የሆኑትን ለይታችሁ በጽሑፍ አሳዩ።**

የሰው ልጅ በምድር መኖር ከጀመረበት ጊዜ እስከ አሁን ጤንነቱን የሚፈታተኑ ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ሲያስተናግድ ኖሯል። እነዚህን የጤና ሰንኮፎችን ለመንቀል ሰው እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። በተለያየ መንገድ የተለያዩ የበሽታ መከላከያና ማከሚያ መድሃኒቶችን ሲያዘጋጅና ሲጠቀም ዘመናትን አስቆጥሯል። እነዚህ የሰው ልጅ በአካባቢው ከሚያገኛቸው ጥሬ ነገሮች በቤቱ ውስጥ በባህላዊ መንገድ የሚያዘጋጃቸው መድሃኒቶች “ባህላዊ መድሃኒቶች” ይባላሉ።

ባህላዊ መድሃኒቶችን አሁን ባለንበት ዘመንም የሚጠቀሙ ሰዎች አሉ። አንዳንድ ግለሰቦች ግን ባህላዊ መድሃኒት የጎንዮሽ ችግር ያመጣል በማለት መጠቀም አይፈልጉም ይባላል። የባህል መድሃኒት በሳይንሳዊ

መንገድ ያልተዘጋጀ ስለሆነ ምናልባትም የግለሰቦቹ ስጋት ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡

ባህላዊ መድሃኒቶች ተበጥብጠው የሚጠጡ፣ በጭስ መልክ የሚታጠኑ፣ በሰውነት ላይ የሚቀቡ…ሲሆኑ ከእፅዋት፣ ከእንስሳት ተዋፅኦ እንዲሁም ከተለያዩ ንጥረ ነገሮች ይዘጋጃሉ፡፡ ማህበረሰቡም እንደባህሉና እንደእምነቱ ጥቅም ላይ ያውላቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በተለያየ አካባቢ ግራዋ የተባለውን ዛፍ ቅጠል ጨቅጭቆና ጭማቂውን በውሃ በጥብጦ መጠጣት ሆድ ውስጥ ያሉ ተዋህስያንን ለማስወገድ ጥሩ ነው ይባላል፡፡ ቀበርቾ የተባለውን እንጨት ጢስ መታጠን ደግሞ እርኩስ መንፈስ ለመከላከል ይረዳል ብለው የሚያምኑም አሉ ይባላል፡፡

ለማጠቃለል ባህላዊ መድሃኒቶች በተጠና መልኩ ቢዘጋጁና በጥቅም ላይ ቢውሉ የራሳቸው ጥቅም እንደሚኖራቸው ዘመናዊ ህክምና በማስረገጥ ይናገራል፡፡

**፫. የማህበረሰቡን የጤና ሁኔታ በተመለከተ በቡድን እየተወያያችሁ የውይይታችሁን ቃለ ጉባዔ ከታች በተሰጠው መመሪያ መሠረት አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡ የቃለጉባዔ አጻጻፍ መመሪያውንም ተግባራዊ አድርጉ፡፡**

**የቃለ ጉባዔ አጻጻፍ መመሪያ**

ሀ. የስብሰባውን ርዕስ ወይም መጠሪያ መጻፍ

ለ. ቦታና ጊዜ መጻፍ

ሐ. በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላትን መጻፍ ወይም ወረቀት አያዞሩ ስማቸውን እንዲጽፉና እንዲፈርሙ ማድረግ፡፡

መ. በስብሰባው ላይ ያልተገኙ አባላትን መጻፍ

ሠ. አጀንዳውን መጻፍ

ረ. የተደረገውን ውይይት መጻፍ

ሰ. የውሣኔ ሃሳብን ማስፈር፡፡

ሸ. በውሳኔ ሃሣቡ ግርጌ ፊርማቸውን አባላት እንዲያስቀምጡ ማድረግ (እያዞሩ ማስፈረም)፡፡

በዚህም መሠረት የሚከተለውን የቃለ ጉባዔ ቅጽ (ፎርማት) ለአብነት ተመልከቱ፡፡

## በድሳችን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የአስረኛ ክፍል የቡድን “ጁ” ተማሪዎች ቃለ ጉባዔ

- የስብሰባ ቦታ፡- ድላችን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት
- የስብሰባ ሰዓት፡- ከ3:00
- በስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት፡-
    1. ተማሪ ዳዊት ዳግማዊ (ሰብሳቢ)
    2. ተማሪ ሳምራዊት ቢረዳው (አባል)
    3. ተማሪ ምህረት ብርሃኔ (አባል)
    4. ተማሪ አረጋዊ ረጋሣ (አባል)
    5. ተማሪ ቶሎሣ መርጊያ (አባል)
    6. ተማሪ ዳንኤል መላክ (ጸሐፊ)

### 5. ያልተገኙ አባላት፡- 
1) ተማሪ ኪዳኔ ምህረት (በህመም ምክንያት)
2) ተማሪ አሰፋ አያሌው (በእክል)

### 6. የመወያያ አጀንዳዎች፡-

ሀ. በትምህርት ቤታችን ግቢ ውስጥ የጤና ችግር መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?

ለ. አንድ ተማሪ በምን ያህል ክበብ መሳተፍ ይኖርበታል?

ሐ. የመማሪያ መጻሕፍትና ከቤተ መጻሕፍት የምንዋሳቸው መጻሕፍት አያያዝ፡፡

### 7. ውይይትና የውሣኔ ሐሳብ

7.1 ውይይት

7.2 ውሣኔ (የመፍትሔ ሐሳብ)

የተሰብሳቢ አባላት ፊርማ

________________

## መረጃ ማግኛ ንባብ

**መረጃ ለማግኘት የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን እንጠቀማለን፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡**

**ሀ) ምርምራዊ ንባብ**

ይህ የንባብ ዓይነት ከሌሎች የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች የንባብ ዓይነቶች ይልቅ ጠለቅ ያለና ትኩረት የሚሻ ንባብ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ንባብ ጥልቅ ንባብ ነው፡፡ በጥልቅ አንብበንና ተመራምረን በነበረን ዕውቀት ላይ ተመስርተን አንድ በዓይነቱ አዲስ ከሆነ የምርምር ወይም የፈጠራ ሥራ ላይ ፍሬ ሃሳቦችን ማጤን ማለት ነው፡፡

**ለ) የገረፍ ገረፍ ንባብ፡-** ይህ የንባብ ዓይነት የምንፈልገውን ነገር ብቻ ብድግ ብድግ በማድረግ የምናነብበት ዘዴ ነው፡፡

**ለምሣሌ፡-** መጽሐፍት ቤት ሄደን የምንፈልገውን መጽሐፍ ካወጣን በኋላ የምንፈልገውን ርዕስ የምንመርጥበት የአነባበብ ዓይነት ነው፡፡

**፬. የምርምራዊ የንባብ ዓይነት በመጠቀም ማህበረሰብና ጤናን የተመለከቱ ጽሑፎችን በሚገባ አንብባችሁ ጠቃሚ ሐሳሣቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አቅርቡ፡፡**

**፭. በምዕራፍ ሦስት ላይ የቀረበውን የማስታወሻ አወሳሰድ ዘዴ በመጠቀም ቀጥሎ የቀረበውን ጽሑፍ ዋናውን መረጃ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡**

ተማሪዎች የቤት ሥራቸውንም ሆነ ጥናታቸውን ሲያከናውኑ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ የሚጠቁሟቸው መምህራንም ሆኑ ሌሎች ደጋፊዎች መኖራቸውን ከተረዱ ትምህርታቸውን በሙሉ ልብ ለመከታተል ይተጋሉ፡፡ ትምህርት በመቀበልም ሆነ በአንዳንድ ግላዊ ችግሮች ምክንያት መሰናክል የሚያጋጥማቸው ተማሪዎች ለትምህርታቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በመጠቀምም ሆነ በማቅረብ እገዛ የሚገያኙበትን መንገድ ማፈላለግ ቢቻል የበለጠ ውጤት ሊገኝ

ይችላል፡፡ ተማሪዎችም የሚያስፈልጋቸውንና የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ እንዲገልፁ ቢበረታቱ የወደፊት ህይወታቸው የተቃና እንዲሆን መደገፍ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ እንዲህ ያለ ዕድል መኖሩን ካወቁና ካመኑ የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ልዩ ችግሮች በማሳወቅ አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኙ ይጣጣራሉ፡፡

*(ደረጀ ገብሬ፣ በተማሪዎች የቤት ሥራ የመምህራንና የወላጆች ሚና፣ ገፅ 51፡፡)*

**፯. የሚከተለውን ምንባብ ጥንድ ሆናችሁ በሚገባ ካነበባችሁና በውስጡ የተካተቱትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ለይታችሁ ካወጣችሁ በኋላ ፍቻቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርቱ፡፡**

## አያ ጥበቡ

አቶ ጥበቡ የሚባሉ አንድ አዛውንት ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ እርሻቸው ደፋ ቀና እያሉ ሲሄዱ አንዲት መልከ መልካም ሴት ከመንገድ ዳር ቁጭ ብላ ስታለቅስ ያገኛሉ፡፡ “ምነው ልጄ ፣አንችን የመሰለች ቆንጆ ይስቃል፣ ይጫወታል እንጂ ፣እንዴት ሆደ ባሻ ይመስል ዝምብሎ መንገድ ላይ ያለቅሣል?” ሲሉ ይጠይቋታል፡፡ እሷም “ አባቴ የማለቅሰው ዝም ብዬ ሳይሆን፣ ‘እግረ ቀጭን እንደሰሳ፣ልበሙሉ እንደ አንበሳ’ እያለ፣ጧት ማታ ራሱን የሚያሞካሽ እኔን ሲሻው ‹አቅመቢስ!› ሲሻው ‹ቀልበቢስ!› እያለ የሚያናንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ባል አጋጥሞኝ ሆድ ቢብሰኝ ነው”ትላቸዋለች፡፡ እሳቸውም “ወቼው ጉድ! እግሩ ቢቀጥን ፣ልቡ ቢደነድን፣ከሰሳና ከአንበሳ የተወለደ መሰለው? ከሴት ማህጸን አይደለም የወጣው? ወይ አለማወቅ ደፋር! ተይው!እያደር ልብ ሲገዛ ይተወዋል፡፡ እስከዚያው ትንሽ ሆደ ሰፊ መሆን ጥሩ ነው ልጄ!” አሏት፡፡ እስዋም እንባዋን ጥርግ ጥርግ አድርጋ ተነሳችና ቀስ እያለች ወደ ቤቷ ታዘግም ጀመር፡፡

*(ባዬ ይማም፣ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፣ (2002)፡፡)*

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

- *ቀጥለው መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ "ኤድስ" በሚል ርዕስ ስር አንድ ምንባብ ያንብቡላችኋል፡፡ እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ያዙ፡፡ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በያዛችሁት ማስታወሻ ዙሪያ ተወያዩ፡፡*

### የማዳመጥ ክህሎትን ማዳበር

ብስሉን ከጥሬ፣ ዋና ዋና ሐሳቦችን ከዝርዝሮች ለይቶና አበጥሮ ማዳመጥ ዕውቀትን ለመቅሰም ዓይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡ ማዳመጥን በተመለከተ የሚከተሉት ነጥቦች ጠቃሚዎች ናቸው፡፡

1. ማዳመጥ መልዕክት መቀበያ መሆኑን መገንዘብ፡፡
2. የሰዎችን ንግግር ስታዳምጡ አለማቋረጥ ለማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንኳ በስርዓት ይቅርታ በመጠየቅ ያቋረጣችሁበትን ምክንያት መግለጽ፡፡
3. ማንኛውም መልዕክት በቃል ሲነገራችሁ ወይም ሲነበብላችሁ በጥሞና ማዳመጥ ለሰዎች ንግግር ተገቢውን ግምት መስጠት እንጂ በንቀት መንፈስ ለማንኳሰስና ለማጥላላት አለመሞከር፡፡
4. ስታዳምጡ ጆሮአችሁን ብቻ ሰጥታችሁ ቁጭ አለማለት
5. ከምታዳምጡት ንግግር ውስጥ ዋና ዋና ሐሳቦችን ለመለየት ጥረት ማድረግ፡፡
6. ያዳመጣችሁትን ፍሬ ሐሳብ አስፈላጊ ሆኖ ስታገኙት ሳታዛቡ ለሌሎችም አስተላልፉ (ማስተላለፍ)፡፡
7. ካዳመጣችሁት ሐሳብ ውስጥ ስህተት የሆነ ነገር ተሰንዝሮ ከሆነ ፊት ለፊት "ልክ አይደለም" "ስህተት ነው" ከማለት ይልቅ በሥርዓት ስህተቱን ማሳየት፡፡

*(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ እንግዳ፣ ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ (1999)፡፡)*

# ክፍል አራት:- ሰዋስው:-

## ከግስ ስምንና ቅጽልን መመስረት

**ከግስ የሚመሰረቱ ስሞች:-**

✓ ከአንድ ግስ እስከ አምስት የሚደርሱ ስሞችን መመስረት ይቻላል፡፡

| ግስ | ጥሬዘራዊ ስም | ሳቢ ዘራዊ ስም | አርዕስታዊ ስም | ግልጋሎታዊ ስም | ውጤታዊ ስም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. መረጠ | ምርጫ | አመራረጥ | መምረጥ | መምረጫ | ምርጥ |
| 2. ሞተ | ሞት | አሟሟት | መሞት | መሞቻ | ሙት |
| 3. ሾመ | ሹመት | አሿሿም | መሾም | መሾሚያ | ሹም |

**፩. ከላይ በተመለከታችሁት ምሳሌ መሠረት ከሚከተሉት ግሶች ውልድ ስሞችን መስርታችሁ አሳዩ፡፡**

| ተ.ቁ | ግስ | ጥሬ ዘራዊ ስም | ሳቢ ዘራዊ ስም | አርዕስታዊ ስም | ግልጋሎታዊ ስም | ውጤታዊ ስም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለመነ | | | | | |
| 2 | ቀረበ | | | | | |
| 3 | ገደለ | | | | | |
| 4 | ሔደ | | | | | |
| 5 | ለበሰ | | | | | |

## ከግስ ቅፅል መመስረት

✓ ከግስ የሚመሰረቱ ቅጽሎች በርካታ ሲሆኑ የእርባታ መልካቸውም ይለያያል፡፡

**ምሳሌ:-**

| ግስ | ውልድ ቅፅል |
|---|---|
| 1. ሰነፈ | ሰነፍ |
| 2. አጠረ | አጭር |
| 3. ከበረ | ክቡር |

✓ **ማስታወሻ:-** በአማርኛ ቋንቋ አንዳንድ ግሶች ቅጽላዊ እርባታ የላቸውም፡፡

**ምሳሌ:-** "ተኛ"

**፪. ከላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመመልከት ቀጥሎ የተሰጡትን ግሶች ወደ ቅፅል ቀይራችሁ አሳዩ::**

| | ግስ | | ቅፅል |
|---|---|---|---|
| 1. | ጎተተ | ⟶ | |
| 2. | ባከነ | ⟶ | |
| 3. | ደነደነ | ⟶ | |
| 4. | አሸገ | ⟶ | |
| 5. | ተለቀ | ⟶ | |
| 6. | ወረረ | ⟶ | |
| 7. | በዛ | ⟶ | |

## የዓረፍተ ነገር ስልቶች

የዓረፍተ ነገር ስልት ማለት አንድ ዓረፍተ ነገር ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር በዓይነት የሚመደብበት ስልት ነው:: በዚህም መሠረት በባየይማም (2002) "አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው" ውስጥ እንደሚከተለው ተሰይመው እናገኛቸዋለን::

1. **ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር፡-** በአዎንታዊና በአሉታዊ መልክ የሚካተት ዓረፍተ ነገር ነው::

**ምሣሌ፡-** ሀ. ሔርሜላ የአንደኛ ክፍል ተማሪ ነች:: (አዎንታዊ የሐተታ ዓረፍተ ነገር)
ለ. እኔ ዛሬ ምሳ አልበላም:: (አሉታዊ ዓረፍተ ነገር)

2. **ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር፡-** በትዕዛዝ መልክ የሚቀርብ የዓረፍተ ነገር ስልት ነው::

**ምሣሌ፡-** ከአልጋው ላይ ተነስ!

3. **ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር፡-** በጥያቄ መልክ የሚቀርብ የዓረፍተ ነገር ስልት ነው::

**ምሳሌ፡-** ወዴት እየሄድክ ነው?

4. **አጋናኝ ዓረፍተነገር፡-** ይህ ስልት መደነቅ፣ መደሰትን፣ መጥላት ወይም መውደድን…ለመግለጽ የሚያገለግል የዓረፍተነገር ስልት ነው::

**ምሳሌ፡-** እፎይ! ገና አሁን ትንሽ ሻል አለኝ::

*(ናንተ ጥበብ ዘሥነፅሁፍ፣ በተክለማርያም ፈንታዬ (ገፅ 67) ውስጥ የተጣቀሠ)*

**፫. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ በተሰጡት ቃላት ሀተታዊ፣ አሉታዊ፣ ጥያቄያዊ ወይም ትዕዛዛዊ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

*ሀ. ወደቀ (ሐተታዊ)*
*ለ. ተመቸ (አሉታዊ)*
*ሐ. ፈጣን (ጥያቄያዊ)*
*መ. ተጠርተህ (ጥያቄያዊ)*
*ሠ. ቆራጥ (ትዕዛዛዊ)*
*ረ. አልተፈቀደም (ሐተታዊ)*
*ሰ. ተገነባ (አጋናኝ)*

## ስርዓተ-ነጥብ

- ስርዓተነጥቦች በወረቀት ላይ የሠፈረ ሐሳብ መልዕክቱ ግልጽ ሆኖ እንዲተላለፍ የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም መልዕክታችንን በሚገባ ለማስተላለፍ አጠቃቀማቸውን በሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡
- በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎች ውስጥ የሚያገለግሉ ሥርዓተ ነጥቦች በርካታ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ሀ. አንድ ነጥብ (.)
ለ. ሁለት ነጥብ (፡)
ሐ. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (፡-)
መ. ነጠላ ሰረዝ (፣)
ሠ. ድርብ ሰረዝ፤
ረ. ሦስት ነጥብ (…)
ሰ. ትዕምርተ - ጥቅስ (« »)
ሸ. ትዕምርተ - አንክሮ (!)
ቀ. ትዕምርተ - ስላቅ (¡)
በ. ትዕምርተ-ጥያቄ (?)
ተ. እዝባር (/)
ቸ. ቅንፍ (())
ነ. ሰረዝ (-)
ኘ. ዕሩይ (=)
አ. እመጫት (∧) እና
ከ. አራት ነጥብ (፡፡) ናቸው፡፡

- **ከዚህ በታች የምናያቸው ድርብ ትዕምርተ ጥቅስንና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስን ብቻ ይሆናል፡፡**

**ሀ. ድርብ ትዕምርተ-ጥቅስ ‹‹ ›› (ሙሉ የጥቅስ ምልክት)**

1. ጸሃፊው ሃሳቡ ከራሱ የፈለቀ አለመሆኑን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

**ምሣሌ፡-** “ድርጅታችን ጨው፣ ስኳር፣ ጥራጥሬ፣ ዱቄት፣ ዘይት ያከፋፍላል” በማለት ሥራአስኪያጁ አስረዱ፡፡

2. አንዳንድ የተውሶ ቃላት በቋንቋው ውስጥ ሲጻፉ ባዕድነታቸውን ለማሳየት ያገልግላል፡፡

**ምሣሌ፡-** የእግሩ ህመም መንስኤ የ “ነርቭ” መሸማቀቅ ነው፡፡

3. ጸሐፊው በትርጉማቸው የማያምንባቸውን አባባሎች ለመለየት ይገለገልበታል፡፡

**ምሣሌ፡-** እኔን አልሰማ ካልከኝ አክስትህ እንደመከረችህ “የጨዋ ልጅ” ፈልገህ አግባ፡፡

4. የሁለት ሰዎችን ምልልሳዊ ንግግር ለየብቻ በደንብ ለማሳየት ይረዳል።

**ምሣሌ:-** "ዛሬ ት/ቤት ሄደሃል?"
"አዎና! ግን ለምን ጠየቅኸኝ?"
"የትራንስፖርት ችግር ስለነበረ ነዋ!"

**ሰ. ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ (' '):-** ይህ ምልክት ጸሐፊው በጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ሌላ ጥቅስ (የሌላ ሦስተኛ ሰው ሃሳብ) ካጋጠመው ለብቻው ቀንብቦ ለማቅረብ የሚጠቀምበት ምልክት ነው።

**ምሳሌ:-** "በርትተን ለመማርና ጥሩ ውጤት ለማምጣት 'ሁልጊዜ ትጉ' የሚለውን የመምህራችንን ምክር እናስታውስ" በማለት የክፍል አለቃው ጓደኞቹን መከረ።

**፬. በሚከተሉት ጽሑፎች ውስጥ ተገቢ ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ አስገቡ።**

1. ሌላው የምመክርህ ነገር አሉ አቶ ማንደፍሮ እንዴት እንደ ሚቀበሉዋቸው ስላላወቁ እያመነቱ ሌላው የምመክርህ ነገር ሥራ እንደያዝህ የምትስማማህንና በመጠኑም ቢሆን ትምህርት ያላት ልጅ ፈልገህ አግብተህ ትዳር እንድትይዝ ነው ትዳር መልካም ነው ልጄ ትዳር ይሰበስባል ይቀጣል የትዳርን ያህል አባት እናት አይቀጡም ይባላል ወዲያውም ያስከብራል አሉት።

*(ሃዲስ ዓለማየሁ፣ የልምዣት፣ 1980)*

2. ማለፊያ አሉ ፊታውራሪ ማለፊያ ገንዘቡ ባደራ እኔ ዘንድ ይቀመጥልሃል ካደራ የበለጠ ክቡርና ከባድ ነገር የለም መተማመን ከሌለ አደራ ሰጭም አደራ ተቀባይም አይኖርም ይል ነበር መክብብ።

*(በዓሉ ግርማ፣ የህሊና ደወል፣ 1967)*

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሳይ ተማሪዎች በአብዛኛው የተሳተፋችሁበትና የመናገርና የመጻፍ ክህሎቶቻችሁን ያሳደጋችሁበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍችዎችን ከመስጠት አንስቶ ዓረፍተ.ነገሮችን በስልታቸው እየመረጥን እንደጻፍን ከመልመጃዎቹ መረዳት ይቻላልና፡፡ ከዚህም ባሻገር ትዕምርተ ጥቅሶቹን ማለትም ድርብ ትዕምርተ ጥቅስና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ በመጠቀም አንቀጾችን በሚገባ አሟልተን ጽፈናል፡፡ እውነታንና የግል አስተያየትን እንዴት መለየት እንደምንችልም በተግባራዊ ልምምድ አይተናል፡፡ በተጨማሪም የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ዝግጅቶችን አድርገን ንግግርም ለማቅረብ ሞክረናል፡፡

በሌላም በኩል ከግሶች ስሞችና ቅጽሎች እንደሚመሰረቱ ተረድተን መስርተናል፡፡ የተለያዩ መልመጃዎችንም መመሪያዎችን በመከተል ሠርተናል፡፡ ውይይትና ጭውውትም በመመሪያዎች መሠረት አድርገናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፈልጉላቸው፡፡

| ተ.ቁ | ቃል | ተመሳሳይ | ተቃራኒ |
|---|---|---|---|
| 1.1 | ፀዳል | | |
| 1.2 | ፍስሐ | | |
| 1.3 | ገሃድ | | |
| 1.4 | አመክንዮታዊ | | |
| 1.5 | ቁስ አካላዊ | | |
| 1.6 | ግርታ | | |

2. የሚከተሉትን ተደባልቀው የተቀመጡ ቃላት ግስ ፣ ስም ወይም ቅጽል በማለት አመልክቱ፡፡

ሀ. ማቀቀ ________

ለ. አዋቂ ________

ሐ. ብልሃት ________

መ. ሰው ________

ሠ. ሰውነት________

ረ. አስገበረ ________

ሰ. አዟሪ________

ሸ. ካሠ ________

ቀ. አታች ________

በ. ጉታች ________

3. ቀጥለው የሚሠጧችሁን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ሀ. ቃር አያውቅሽ

ለ. ዝቅ ቀና

ሐ. ልጓም አጥባቂ

መ. ስም አበር

4. አራቱን የዓረፍተነገር ስልቶች በምሳሌ አስደግፋችሁ ግለጹ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወጣቶችና ስነተዋልዶ ጤና የሚለውን ምንባብ አንብቤ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳያቸውንና ተቃራኒያቸውን በመፈለግ ሠርቻለሁ፡፡ | | | |
| 3. | ከግስ ስምንና ቅጽልን መስርቻለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የዓረፍተ ነገርን ስልቶች ተረድቼ ምሣሌ መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5. | የድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስን አገልግሎት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 6. | በተለያዩ የንግግር መድረኮች የሚተላለፉ መልእክቶችን በማዳመጥ ማስታወሻ መያዝ የሚጠቅም መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 7. | እውነታን ከግል አስተያየት መለየት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 8. | የቃለ ጉባዔ አያያዝ ምን መልክ እንደሚኖረው ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 9. | ለተለያዩ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ቀና አመለካከት

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ ስለ ቀና አመለካከት ጠቀሜታ ተገንዝባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ሐረጋትን በዓይነታቸው ለይታችሁ ትመድባላችሁ፡፡
- ✓ ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ✓ ከተለያዩ ምንጮች የምታገኟቸውን መረጃዎች በሚመለከት ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ✓ አመዛዛኝ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ለምሣሌያዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ መልእክት ያላቸውን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ እንቶኔን፣ ምፀትንና ግነት ዘይቤን በጽሑፋችሁና በንግግራችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች አንድ ሰው ቀና አመለካከት አለው ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. ቀና አመለካከት ያላቸው ሰዎች በህይወታቸው ምን ጠቀሜታ የሚያገኙ ይመስላችኋል? የሌላቸውስ?
3. በሰዎች ዘንድ ቀና አመለካከት መኖር ሀገራዊ ፋይዳው ምንድን ነው?

## "ምንም የማይቻል ነገር የለም!"

“ምንም የማይቻል ነገር የለም!”
“ይተው እንጂ፣ ዶክተር!” ትሉ ይሆናል፡፡ “እርስዎ የተማሩ ሰው ነዎት፡፡ እንዴት ‘ምንም የማይቻል ነገር የለም!’ ይላሉ? አእምሮዎን ስተዋል እንዴ?!” ልትሉም ትችላላችሁ፡፡

“አይቻልም!” የሚለውን ቃል ከአእምሮዬ ውስጥ ካስወጣሁት ከረምኩ፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ በብዙ ምክንያቶች ከቃሉ ጋር የነበረኝን ቁርኝት አቋርጫለሁ፡፡

“አይቻልም” የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ በጥቅም ላይ የሚውለው ደንታ ቢስ በሆነ፣ በተስፋ መቁረጥና ፍሬ በሌለው ሁኔታ ነው፡፡ እና በፍጹም አእምሮዬን አልሳትኩም፡፡ እጄን ለእነዚህ ከንቱ ስሜቶች አልሰጥም፡፡ ስለዚህም “አይቻልም” የሚለውን ቃል ከእስር አውጥቼ ፈታሁት!

በምድር ላይ እጅግ አደገኛው አስተሳሰብ የጨለምተኛነት አስተሳሰብ ነው፡፡ ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያለው ሰው ከዚህ ቀደም ተሞክሮ ያልተሳካ አንድ ተግባር የሚያውቅ ከሆነ ያ ተግባር ያልተሳካው መጀመሪያውኑ “የማይቻል ስለሆነ ነው” ብሎ አምኖ እናንተንም ያሳምናችኋል፡፡ ዓለም በሙሉ እውነተኛ ያልሆነች፣ ያልተጨበጠች፣ አስቸጋሪ፣ የማትታሰብ እና የማትቻል እንደሆነች ይሰብካችኋል፡፡ እናም ይህ ዓይነቱ ሰው እድገትን ይገድባል፤ ልማትን ያጨናግፋል፣ ፈጠራን ያቀጭጫል፤ ጠልቆ ማሰብን ይገታል፡፡

**ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ በማድረግ ከላይ ባነበባችኋቸው አንቀጾች ውስጥ ያገኛችኋቸውን ነጥቦች ለመምህራችሁ ተናገሩ፤ በሚቀጥሉት የምንባቡ አንቀጾች ውስጥ ሲነሱ ይችላሉ የምትሏቸውን ሐሳቦችም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡**

ከዚህ በተቃራኒ ቀናው አስተሳሰብ የ“ይቻላል” አስተሳሰብ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ሰው አዲስ ሀሳብ ሲያጋጥመው የአሸናፊነት ስሜት በውስጡ ስለሚሰማው በገጠመው እድል የሚደሰት ነው፡፡ ለአሮጌ ችግሮች የአዲሱን ትውልድ መፍትሔዎች በመጠቀም አዲስ ታሪክ ለመሥራት ባገኘው አጋጣሚ ይነቃቃል፡፡ የማይታለፉ የሚመስሉ እንቅፋቶች የሚፈቱበት አንድ መንገድ አለ ብሎ ስለሚያምንም በልበ ሙሉነት ወደ ተግባር ይገባል፡፡ ሁሌም ለስኬታማ ጉዞው ስንቅ የሚያደርገው “ይቻላል!” የሚለውን ቃል ነው፡፡

- “የልብ ቀዶ ህክምና?! በፍጹም አይቻልም!”
- “ሰውን ጨረቃ ላይ ማስቀመጥ?! ተው እንጂ! በፍጹም አይቻልም!”
- “ከአንድ የእግር ኳስ ሜዳ በላይ ቁመት ያለው ህንፃ መገንባትና የመሬት መንቀጥቀጥን እንዲቋቋም ማድረግ?! በፍጹም አይቻልም!”

አስተውሉ! እነዚህ ሁሉ ተችለዋል፡፡ “አይቻልም” ሲሉ የነበሩትም በሀፍረት አንገታቸውን ደፍተዋል፡፡

እናንተ የዚህ ዘመን ባለአደራዎች፤ ራሳችሁን ከክፉ አስተሳሰብ አርቁ! በቀና አስተሳሰብ አንጹ! ስኬታማ ለመሆን ስንቃችሁ “ይቻላል!” የሚለው ቃል ይሁን፡፡

*(ምንጭ፡- በሮበርት ኤች. ሹለር ተጽፎ በማኅሌት ጥላሁን ከተተረጎመው “አመለካከትን በመለወጥ ሕይወትን መለወጥ የሚስችሉ ታላላቅ መንገዶች” ከሚለው መፅሐፍ ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ (48-50)፡፡)*

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን 'እውነት' ስህተት የሆኑትን ደግሞ 'ሐሰት' በማለት መልሱ።

1. ደንታ ቢስ የሆኑ ሰዎች የ "ይቻላል!" መርህ ተከታዮች ናቸው።
2. የጽሑፉ አቅራቢ በዚህ ምድር ላይ የማይቻል ነገር የለም የሚል አቋም አላቸው።
3. የሚቻሉ ነገሮችን "አይቻልም!" ሲሉ የነበሩ ሁሉ ትንቢታቸው ሰምሮላቸዋል።
4. እስካለንበት ዘመን ድረስ የሰውን ልጅ ጨረቃ ላይ ማሳረፍ አልተቻለም።
5. የስኬታማ ህይወት ተቋዳሾች ዓለምን በብሩህ መልኩ የሚቀበሉ ናቸው።

፪. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ላይ በመፈለግ ጻፉ።

| | |
|---|---|
| 1. ተቆራኘ | 6. መፍትሔ |
| 2. ተስፋ | 7. ስንቅ |
| 3. ስኬት | 8. ማነፅ |
| 4. ሰበከ | 9. ቀና |
| 5. ተጨናገፈ | 10. ጥልቅ |

፫. የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ክፍል ውስጥ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩባቸው፤ በመቀጠልም በጋራ ተወያዩበት።

1. በምንባቡ ከቀረቡት አስተሳሰቦች መካከል በህይወታችን ልንከተለው የሚገባው አስተሳሰብ የትኛውን ነው? ለምን? አብራርታችሁ ተናገሩ።
2. "አዲስ ታሪክ ለመሥራት ይነቃቃል" የተባለው ትውልድ የትኛውን አስተሳሰብ የሚከተለው ነው? ለምንስ ስኬታማ ይሆናል ተባለ?
3. ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ህይወታቸውን በምን ዓይነት መንገድ ማስተካከልና መምራት እንዳለባቸው ያላችሁን ሀሳብ ተናገሩ።

## ክፍል ሁለት:- መናገር

፩. በቡድን ሆናችሁ “ቀና አመለካከት” በሚል ርዕስ አጭር ጽሑፍ አዘጋጁና በክፍሉ ፊት በምትወክሉት አቅራቢ አማካይነት አቅርቡ።

፪. በቡድን በመሆን ቀና አመለካከት ያለውን ማህበራዊ ጠቀሜታ በተመለከተ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍሉ አጋሩ።

፫. በአካባቢያችሁ ከሚደረጉ የአዋቂ ሰዎች ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ያገኟችኋቸውን ፍሬ ሐሳቦች በማስታወሻ ይዛችሁ አቅርቡ።

## ክፍል ሦስት:- መጻፍ

***ታማሪዎች!*** **ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጉና ቀና አመለካከት ያላቸውንና የሌላቸውን ሰዎች በማነጻጸር ከሁለት ገጽ ባልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::**

### አመዛዛኝ ድርሰት

የድርሰት ዓይነቶችን በተመለከተ የቋንቋ ሊቃውንት አንድ ዓይነት አመለካከት የላቸውም። አንዳንዶች ስድስት፣ ሌሎች አራት፣ ሌሎች ደግሞ ሦስት ናቸው ይላሉ። በዚህ ምዕራፍ የምናየው በሁሉም ምድብ ውስጥ የማይጠፋውን አመዛዛኝ ድርሰትን ነው።

አመዛዛኝ ድርሰት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚጽፍ፣ አንባቢውን /አድማጩን/ የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሐሰትነት ለማሳመን የሚጥር፤ ደራሲው /ጸሐፊው/ ለአንድ ወገን ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሊጽፍ የሚችልበት፣ ወይም ለሁለቱም አከራካሪ ሐሳቦች የቆመ በመምሰል ጉዳዩን በመደገፍና በመቃወም አቅርቦ በመጨረሻም ማስረጃው ያደላበትን አጠናክሮ በመተቸት አንዱን በማጠናከር ወደ አንድ ውሳኔ የሚደርስበትና ለማሳመን የሚጥርበት የድርሰት ዓይነት ነው።

**የአመዛዛኝ ድርሰት ምሳሌ:-**

ብዙ የሥነ-ትምህርት ተመራማሪዎች የመማር ማስተማር ዘዴ ትምህርት "ሳይንስ" ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ "አርት" ነው ይሉታል። "አርት" ነው የሚሉት ተመራማሪዎች የመማር ማስተማር ዘዴ ምንም ህግ የለውም ይላሉ። "የተማረ ያስተምር" እንደሚሉት ዓይነት ነው።

ጥሩ አስተማሪነት የሚመነጨው ከሰውየው ችሎታ እንጂ ከሚያገኘው ሥልጠና አይደለም ይሉናል። ለአስተማሪ የሚያስፈልገው የሚስተ ምረውን የትምህርት ዓይነት ጠንቅቆ ማወቅ ነው፣ በማለት በአጽንኦት ይከራከራሉ።

"ሳይንስ" ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ህጐች አሉት። አስተማሪው ህጐችን ጠንቅቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በክህሎትና በአመለካከቱም በኩል ያሉትን ህጐች የሚያንጸባርቅ ባህሪይ ማሳየት የሚችል መሆን አለበት ነው የሚሉት። በዚህም መሠረት መምህር የሚሆን ሁሉ በሥነ ትምህርት ሳይንስ የሰለጠነ መሆን አለበት ይላሉ።

ሰውን ካስተማርከው ይማራል፣ የሚል የክርክር መነሻ ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ። ማስተማር ሌላ ጉዳይ ነው፤ መማር ደግሞ የተለየ ነው፤ የሚሉ ሰዎች ደግሞ ሞልተዋል። ታዲያ ማስተማር መማርን እንዲ ያስከትል ከተፈለገ የመማር ማስተማርን ህጐች ጠንቅቆ ማወቅ አያስፈልገንም? መማርን የሚያስከትሉ ነገሮችን ማወቅ ማለት ደግሞ መንስኤና ውጤትን ማወቅ ማለት ነው። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ከስነ-ትምህርት ሳይንስ የሚገኙ ስለሆኑ መምህራን የስነ-ትምህርት ሳይንስ ትምህርትን በሚገባ ማጥናት ይኖርባቸዋል።

*ከመፅሔተ ትምህርት ክቅፅ 1. ቁጥር 1 ላይ የተወሠደ*

## ክፍል አራት:- ሰዋስው

**፩. የሐረጋት ምስረታ ህግጋትን በመመርኮዝ “ምንም የማይቻል ነገር የለም” በሚለው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ሐረጋትን በተሰጠው ሠንጠረዥ ውስጥ በየዓይነታቸው መድቧቸው።**

**ምሳሌ**

| ግሳዊ ሐረግ | ስማዊ ሐረግ | ቅጽላዊ ሐረግ | ተውሳከ ግሣዊ ሐረግ | መስተዋድዳዊ ሐረግ |
|---|---|---|---|---|
| … የማይቻል ነገር የለም።<br>ሀ. _______<br>ለ. _______<br>ሐ. _______<br>መ. _______ | የተማሩ <u>ሰው</u>፣ | ምንም <u>የማይቻል</u>፣ | አሁኑኑ <u>ቶሎ</u>፣ | <u>ከ</u>አእምሮየ <u>ውስጥ</u> |

**፩. ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት ከተሰጧችሁ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ተራ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።**

**ምሳሌ፡-** *በፍጥነት እየነዳ ወደ ሥራ ሲሄድ፣ ከጭነት መኪና ጋር ተጋጭቶ ክፉኛ ቆሰለ። (ውስብስብ ዓረፍተ ነገር)*

**መልስ፡-** የተመሠረቱ ተራ ዓረፍተ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

1. በፍጥነት ነዳ።
2. ወደ ሥራ ሄደ።
3. ከጭነት መኪና ጋር ተጋጨ።
4. ክፉኛ ቆሰለ።

1. *መክሰስህን ቶሎ በልተህ ጥናትህን ጀምር።*
2. *ወደ ፎቅ ከወጣህ በኋላ ወደ ቀኝ ታጠፍና ሁለተኛውን በር አንኳኳ።*
3. *ወንድሟ ወደ ውጭ ሀገር በመሄዱ ከጓደኛዋ ጋር ሆና ምርር ብላ አለቀሰች።*
4. *መምህርህ የቤት ሥራህን ባለመሥራትህ የፈለጉትን ያህል ቢቆጡህ ቂም መያዝ የለብህም።*
5. *መንግሥት የሕዝቡን ችግር በማየት የመፍትሔ ሐሳብ አቅርቧል።*

**፪. ቀጥሎ በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት ከተሰጧችሁ ተራ ዓረፍተ ነገሮች ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።**

**ምሳሌ፡-** **ተራ ዓረፍተ ነገሮች**

1) *መሐመድ ጎበዝ ልጅ ነው።*
2) *ቀልድ ያበዛል።*

**የተመሠረቱት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች**

ሀ) *መሐመድ ጎበዝ ልጅ ቢሆንም፣ ቀልድ ያበዛል።*
ለ) *መሐመድ ጎበዝ ልጅ ነው፤ ቢሆንም ቀልድ ያበዛል።*

1. ሀ. ሐሳቡ አይገባኝም:: ለ. ከማጥናት አልቆጠብም ::
2. ሀ. አዲሱን ኮት አገላበጠው::
   ለ. አዲሱን ኮት አየው::
   ሐ. አዲሱን ኮት ገዛው::
3. ሀ. ፊቱን ታጠበ:: ሐ. መማሪያዎቹን ያዘ::
   ለ. ቁርሱን በላ መ. ወደ ት/ቤት ሄደ::
3. ሀ. በዚህ ክፍል ውስጥ ጥቂት ሰነፎች አሉ::
   ለ. አብዛኞቹ ግን ዓላማቸውን አይስቱም::
4. ሀ. ከበደ መጣ:: ለ. በጣም አስገረመኝ::

**፲. ስለተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ አምስት ተራ እንዲሁም አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ::**

## ክፍል አምስት:- ስነጽሑፍ

**፩. በምሣሌው መሠረት ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋሮች ተስማሚ የሚሆኑትን በሳጥን ከቀረቡት ውስጥ በመምረጥ ባዶ ቦታው ላይ አስፍሩ::**

**ምሳሌ:-**

1. ሺህ ፍልጥ ማሠሪያው ልጥ = <u>ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ::</u>

ሀ. "ባልበላ ጭሬ ላፍስሰው" አለች፣ ዶሮ::
ለ. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ::
ሐ. ሰርገኛች መጡ ብቅል አስጡ::
መ. ችኩል አደንጓሬ ሳይበሉት ሆድ ያማል::
ሠ. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ::

2. ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ = ____________________
3. ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ = ____________________

4. "እኔ ከሞትሁ ሠርዶ አይብቀል" አለች ፣ አህያ = ____________
5. የቸኮለች አፍስሳ ለቀመች = ____________________________

፪. በፍች የሚመሳሰሉ ሁለት ሁለት ምሣሌያዊ አነጋገሮች በመፈለግ በደብተራችሁ ላይ በማስፈር ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ዘይቤ

1. **እንቶኔ ዘይቤ:-** በአጠገብ የሌለን ሰው ወይም ሰው ያልሆነ ነገር በቅርብ እንዳለ፣ እንደሚሰማንና መልስ እንደሚሰጠን አድርገን በመቁጠር መልዕክት የምናስተላልፍበት የዘይቤ ዓይነት ነው።

   **ምሳሌ:-** 1. እናቴ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣
   የሠራልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ።
   2. ተናገር አንተ ሐውልት!

**አስተውሉ:-** በሁለቱም ምሳሌዎች የምናናግራቸው ግዑዛን በሁለተኛ መደብነት እንደተቀመጡ አስተውሉ። ያናገርናቸው "አንተ"፣ "አንቺ" እያልን ነው።

2. **ምፀት ዘይቤ:-** ከምንናገረው ቀጥተኛ ንግግር በተቃራኒው ሐሳባችንን የምናቀርብበት ዘዴ ነው። ይህ ዘይቤ በምክር ስድብን፣ በሙገሣ ማዋረድን፣ በሣቅ ሐዘንን ወዘተ. በጎንዮሽ አነጋገር የምንገልጽበት ዘይቤ ነው።

   **ምሳሌ:-** አጭሩን ሰው ሎጋ ከሲታውን ዱባ፣
   እጅግ ቀርፋፋውን ሰው ‹ጀት›

3. **ግነት ዘይቤ:-** አንድን ነገር ካለው ነባራዊ ይዘት በማጋነን የሚያቀርብ ረቂቁን የሚያገዝፍ እና የሚያጎላ የዘይቤ አይነት ነው።

   **ምሳሌ:-** ዝሆን የሚያህል ቁንጫ ገደልኩ።
   የጨረቃዋ ብርሀን ጤፍ ያስለቅማል።

፫. ከፍ ሲል በተማራችሁት መሠረት በእያንዳንዱ የዘይቤ ዓይነት ሥር ሦስት፣ ሦስት ዓረፍተ ነገሮችን ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።

1. እንቶኔ ዘይቤ:- ሀ. ____________ ለ. ____________ ሐ. ____________
2. ምፀት ዘይቤ:- ሀ. ____________ ለ. ____________ ሐ. ____________
3. ግነት ዘይቤ:- ሀ. ____________ ለ. ____________ ሐ. ____________

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ የቋንቋ አጠቃቀምን፣ ሰዋስውና ስነ ጽሑፍን በሚገባ ያየንበት ምዕራፍ ነው፡፡ በምዕራፉ ውስጥ ሐረጋትን በዓይነታቸው ለይተን በማውጣት ማየት ችለናል፡፡ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ከተራ ዓረፍተ ነገሮች እንዴት እንደምንለይ፣ ከውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተራ ዓረፍተ ነገሮችን እንዴት እንደምንመሰርትና ከተራዎቹ ዓረፍተ ነገሮች ደግሞ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን እንዴት እንደምንመሰርት ተረድተን ተግባራዊም አድርገናል፡፡ ለተሰጡን ምሳሌያዊ አነጋገሮችም ተመሳሳይ የሆኑ ምሣሌያዊ አነጋገሮችን ፈልገናል፡፡ የተሰጡትንም ዘይቤያዊ አነጋገሮች ምንነት ተረድተን ዓረፍተ ነገሮችን በሚገባ መስርተንባቸዋል፡፡ በጥቅሉ የአጻጻፍ ስልታችን ሻል ባለ የቋንቋ አጠቃቀም ለማዳበርና ሰዋስዋዊ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ድርሰት ለመጻፍ ጥረት ያደረግንበት ምዕራፍ ነበር፡፡

## የክለሣ ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ተደባልቀው የተቀመጡት የተለያዩ አምስት ዓይነት ሐረጋት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከፊት ለፊታቸው በሚሰጣችሁ ባዶ ቦታ ላይ ግሣዊ ሐረግ፣ ስማዊ ሐረግ፣ ተውሳከ ግሣዊ ሐረግ፣ መስተዋድዳዊ ሐረግ ወይም ቅጽሳዊ ሐረግ በማለት መልስ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| ጥቁር ድንጋይ __________ | አሁኑኑ በፍጥነት__________ |
| እጅግ በጣም ጥቁር__________ | ከዛፉ ሥር__________ |
| ቆሎ የሚያኝርስ ፍቅር__________ | እስከዳር__________ |
| አበባው አበበ__________ | |

፪. የሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በምን ዓይነት አውድ እንደሚነገሩ ተወያዩባቸው፡፡

1. ሴባ ሳመሉ ዳቦ ይልሳል፡፡__________
2. ሰው ለሰው መድሃኒቱ ነው፡፡__________
3. አባብ ያዬ በልጥ በረየ፡፡__________

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል:: በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ::

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ቀና አመለካከት የቀረበውን ምንባብ ይዘት መግለፅ እችላለሁ:: | | | |
| 2. | ሐረጋትን በዓይነታቸው በመለየት መመደብ ችያለሁ:: | | | |
| 3. | ውስብስብና ተራ ዓረፍተነገሮች እመሰርታለሁ:: | | | |
| 4. | ማስታወሻ የመያዝ ስልትን በመከተል የተለያዩ ንግግሮችን በማዳመጥ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ እይዛለሁ:: | | | |
| 5. | አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ እችላለሁ:: | | | |
| 6. | ለተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍች ያላቸውን ምሳሌያዊ አነጋገሮች እሰጣለሁ:: | | | |
| 7. | የእንቶኔ፣ የምፀትና ግነት ዘይቤዎችን ምንነት ተረድቻለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ (?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ ስድስት

## ግጥም

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች:-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ✓ የግጥም ዓይነቶችን ለይታችሁ ትናገራላችሁ::
- ✓ የቀረበላችሁን ግጥም ዋና መልዕክት ትገልጻላችሁ::
- ✓ የዘይቤ ዓይነቶችን ትለያላችሁ::
- ✓ ስለዘይቤ ዓይነቶች ያገኛችሁትን ቁም ነገር በማስታወሻ ትይዛላችሁ::
- ✓ በግጥም ዓይነቶች ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት መርዘምና ማጠር ባህሪይ ያላቸውን ቃላት ለይታችሁ ታሳያላችሁ::
- ✓ ስንኞች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ትገልጻላችሁ::
- ✓ በበቂ ምዕላድ ላይ የተጨመሩ ቅጥያዎችን ተግባር ትገልጻላችሁ::
- ✓ ቃላዊ ግጥሞችን መርጣችሁ ትጽፋላችሁ፤ ታነባላችሁ::
- ✓ ከግስ ስምና ቅፅል ትመሠርታላችሁ::

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ግጥም ማለት ምን ማለት ነው?
2. የግጥምን ባህሪዎች ታውቃላችሁ? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. ግጥም የሚነበብበት ስልት ከስድ ጽሑፍ የተለየ ነው? ተወያዩበት፡፡

## ግጥም

ስለ ግጥም ምንነት በርካታ ምሁራን የተለያየ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ግጥም በእጅጉ ጥንታዊነት እንዳለው የሚነገርለት የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ የሰው ልጆች ለብዙ ዘመናት የአኗኗር ሁኔታቸውንና ልዩ ልዩ ገጠመኞቻቸውን በማንጎራጎርና በማዜም ሐሳባቸውን በጽሑፍ ከመግለጻቸው በፊት በስነ-ቃል መልክ ይጠቀሙበት እንደነበር በስፋት ይነገራል፡፡ በዚህም መሠረት ግጥም ዕድሜው ከቋንቋ መፈጠር ዕድሜ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ይገመታል፡፡

ይህ የስነ-ጽሑፍ ዘርፍ ዕድሜው ረጅም በመሆኑ እንደየዘመኑ ፍልስፍና፣ ገናን የኪነጥበብ ፈለግ፣ እንደየገጣሚውና እንደየስነጽሑፍ አዋቂው አተያይና የኪነጥበብ ዝንባሌ የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡት ቆይተዋል፤ ከዚህም የተነሳ ሁሉንአቀፍ የሆነ አንድ ወጥ ብያኔ ይህ ነው ብሎ መቀበል ቀላል አይሆንም፡፡

ግጥም አንድን ነገር ወይም ድርጊት አድምቆና አጉልቶ የማሳየት ሀሳብን አክርሮና አግዝፎ የማቅረብ ችሎታ ያለው በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ነገሮችን አምቆ የሚይዝና በሙዚቃዊ ቃናው የስሜት ህዋሳትን በቶሎ የሚነካ፤ ለስሜት ቅርብነት ያለው ኪነጥበብ ነው፡፡ የግጥም ባህሪያትን ስንመለከት የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡

አንደኛ፣ ግጥም በእጅጉ **ቁጥብና እምቅ** ነው፡፡ በጥቂት ቃላት ብዙ ማለት የሚችል የስነጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ግጥም **ምጣኔ** ያለው ነው፡፡ በግጥም ውስጥ የቀለማትን መጠን በሐረግ ውስጥ የምንመጥንበት /የምንለካበት/ ዘዴ ምጣኔ ይባላል፡፡

ከዚህም ሁኔታ እንደምንረዳው ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በሐረግ ውስጥ ሲሆን መለኪያው ደግሞ ቀለም መሆኑን ነው። ታዲያ "ቀለም ማለት ምንድነው?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ቀለም ማለት፡-

ሀ. ተናባቢና አናባቢ ድምጾች አንድ ላይ ሲመጡ የሚፈጥሩት የቋንቋ መዋቅር ማለት ነው።

**ምሳሌ፡-** "ና" የሚለው በድምጻዊ አጻጻፍ ሲጻፍ /ንኣ/ የሚሉትን ድምጾች ይወክላል።

ለ. አናባቢ ድምጽ ብቻውን ሲመጣ የሚፈጥረው የቋንቋ መዋቅር ነው።

**ምሳሌ፡-** እ /እ/ ኧ /ኧ/ ኡ /ኡ/...

ይህን ከተረዳን የግጥም ሐረግ እንዴት በቀለም እንደሚመጠን ደግሞ እንመልከት።

**ምሳሌ፡-** አንበሳ ነው ጀግና ቁጣው አስበርጋጊ፣ ፮ + ፮ = ፲፪

የነፃነት አርማ የድል ፋና ወጊ። ፮ + ፮ = ፲፪

በዚህ መሠረት በየሐረጉ ስድስት፣ስድስት ቀለም መኖሩን ማስተዋል ተገቢ ነው። በሐረግ ስድስት ቀለሞችን የሚይዝ ግጥም የወል ሐረግ /ግጥም/ ተብሎ ይጠራል። ሲጠቃለል ሐረግ ማለት የመጀመሪያዋን ድምጽ ማሰማት ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ **ከፊል እረፍት እስከ ምናደርግበት** ጊዜ ድረስ ያሉ የቀለማት ስብስብ ማለት ነው።

ሦስተኛ፣ **ግጥም ምት** አለው። ምቱ የሚመነጨውም ከምጣኔው ነው። ከፍ ሲል እንዳየነው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን የማለቱ ሁኔታ ነው ምቱን የሚፈጥረው። ይህን ለመረዳት አንድ አባት የስድስት ዓመት ህፃን ልጁን ይዞ ወደ ሱቅ ሲራመድ ያለውን የሁለቱን ርምጃ ልዩነት ማስተዋል ይበጃል።

የአባት ርምጃ ሰፋ ሰፋ ያለ፤ የልጁ ደግሞ ጠበብ ጠበብ ያለ በመሆኑ ምታቸው አንድ አይሆንም። ከዚሁ አንጻር ሐረግ በሚይዘው የቀለም ብዛት መጠን ምቱ ይለያያል፤ ዓይነቱም እንዲሁ።

**ምሳሌ:-** "ቡሄ በሉ" የምንልበት ጊዜና "ካላጨበጨቡ" የምንልበት ጊዜ ይለያያል፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው ሐረግ አራት ሁለተኛው ስድስት ቀለም በመያዛቸው የተነሳ ነው፡፡ <u>ብኡ</u> <u>ህኤ</u> <u>ብኧ</u> <u>ልኡ</u> = ፬ ቀለሞች
ክኣ-ልኣ-ጭኻ-ብኧ-ጭኧ-ብኧ=፮ ቀለም

አራተኛ፣ **ግጥም ዜማ** አለው፡፡ ይህ የሚፈጠረው የተስተካከለና የተከረከመ ምጣኔና ምት በሐረጉ ውስጥ በመኖሩ የተነሳ ነው፡፡ ምጣኔ ከተዛባ ምቱ፣ ምቱ ከተዛባ ደግሞ ዜማው የተዛባ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው የግጥም ዓይነቶች የሚወሰኑት በሐረግ ውስጥ በሚኖሩ የቃላት ብዛት ነው፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ተመልከቱ፡፡

- **የወል ግጥም:-** በሐረጉ ውስጥ ስድስት ቀለማትን የሚይዝ የግጥም ዓይነት ነው፡፡

**ምሳሌ:-** አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ / የጎረቤታችን፤ ፮ + ፮ = ፲፪
እናትሽ ተቆጡ / አትምጪ ቤታችን፡፡ ፮ + ፮ = ፲፪

- **ሰንጎ መገን ግጥም:-** በሐረጉ ውስጥ አምስት ቀለሞችን አካቶ የሚይዝ ግጥም ነው፡፡

**ምሳሌ:-** ፈሪ ጨነቀው / ተርበደበደ፤ ፭ + ፭ = ፲
ጥይት ዘነበ / እሳት ወረደ፡፡ ፭ + ፭ = ፲

- **ቡሄ በሉ/ የህፃናት /ሆያሆዬ/ ግጥም:-** በየሀረጉ ከአንድ - አራት ቀለማትን የሚይዝ የግጥም ዓይነት ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በአቀንቃኙና በተቀባይ መካከል በአብዛኛው በቅብብሎሽ ስለሚከወን ነው፡፡

**ምሳሌ:-** አቀንቃኙ:- " ሆያ ሆዬ" ሲል:-
ተቀባይ "ሆ" ወይም "ሆዬ" ይላል፡፡ ይኸውም "ሆያ ሆዬ" በሚለው አራት ቀለማት፣ "ሆ" በሚለው ደግሞ አንድ ቀለም፣ እንዲሁም "ሆዬ" በሚለው ውስጥ ደግሞ ሁለት ቀለማት ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ከአንድ እስከ አራት ቀለማት በሐረጉ ውስጥ ይከሰታል ማለት ነው፡፡

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ቀጥለው የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. የግጥምን ዕድሜ በትክክል ይህን ያህል ነው ብሎ መናገር ይቻላል::
2. ግጥም ለደስታ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ስሜቶችም መግለጫ ነው::
3. ስድ /ዝርው/ ጽሑፍ እና ግጥም ስሜትን ለማስተላለፍ እኩል ናቸው::
4. ቀለም ማለት ተናባቢ ድምጽ ብቻውን ሲመጣ የሚፈጥረው መዋቅር ማለት ነው::
5. ምት ማለት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን መጥራት ማለት ነው::

**፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::**

1. የግጥም ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ቁጥብ አይደለም
   - ለ. ምት አለው
   - ሐ. ዜማ አለው
   - መ. ምጣኔ አለው
2. ቁጥብነት ሲባል የ______ ቁጥብነት ማለት ነው::
   - ሀ. የሐሳብ
   - ለ. የጽንሰ ሐሳብ
   - ሐ. የቃላት
   - መ. ሁሉም
3. የሰንኙ መገን ግጥም በሐረግ ስንት ቀለም አለው?
   - ሀ. ፬
   - ለ. ፫
   - ሐ. ፮
   - መ. ፯
4. ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በ _____ውስጥ ነው
   - ሀ. ስንኝ
   - ለ. ቀለም
   - ሐ. ሐረግ
   - መ. ቤት
5. ለአዕምሮ የሚጥም ባለ ስልት የቋንቋ አደራደር ______ ይባላል::
   - ሀ. ስነ ግጥም
   - ለ. ስንኝ
   - ሐ. ሐረግ
   - መ. ቀለም

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፩. በምዕራፍ አራት ስለ "ቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር" በተማራችሁት መሠረት ለቅስቀሳ አላማ የሚሆኑ ግጥሞችን ከተለያዩ መጻሕፍት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች በመውሰድ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡
፪. ከመጻሕፍት ከጋዜጣ ከመጽሔቶች...ያገኛችሁትን ግጥም በሚገባ አንብባችሁ ዋናውን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራርታችሁ ግለጹ፡፡
፫. መምህራችሁ በቡድን ከከፈሏችሁ በኋላ በየቡድናችሁ በመሆን ከዚህ በሚከተሉት በአንዱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቃላዊ ግጥሞችን አሰባስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

*ሀ. የልመና ቃላዊ ግጥሞች*
*ለ. የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች*
*ሐ. በክብረ በዓል ላይ የሚባሉ ቃላዊ ግጥሞች*
*መ. በለቅሶ ላይ የሚባሉ ቃላዊ ግጥሞች/ሙሾ/*
*ሠ. ሌሎች በአናንተ አካባቢ የሚነገሩ የሥራ ቃላዊ ግጥሞች፡- ለምሳሌ የመኸር፤ የመዝሪያ፣ የማረሻ ጊዜያትን የተመለከቱ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡*

## ክፍል ሶስት፣ ሰዋስው

፩. ቀጥለው በተሰጡት ምሳሌዎች መሠረት ቅጥያ ምዕላዶችን በበቂ ምዕላዶች ላይ እየጨመራችሁ አገልግሎታቸውን አብራሩ፡፡

| | ነፃ ምዕላድ | + ጥገኛ ምዕላድ | = ቃል | የቅጥያ አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | እህት | - ህ | = እህትህ | የአንተ እህት (ባለገንዘብነትን አመልካች) |
| 2. | | | = ሳምሽ | |
| 3. | | | = ወንድሙ | |
| 4. | | | = አባቷ | |
| 5. | | | = ወሬዎች | |
| 6. | | | = ስንቄ | |

**፪. ቀጥለው በቃል ደረጃ የተሰጡትን ምዕላዶች ነፃ ምዕላድ ጥገኛ ምዕላድ በማለት ከፋፍሉ:: የጥገኛ ምዕላዶቹን አገልግሎትም ግለጹ::**

| | ቃል | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ | የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | መርከበኛ | መርከብ | -ኧኛ | ቅጽል መስሪች |
| 2. | ሆዳም | | | |
| 3. | ወተታም | | | |
| 4. | ተራራማ | | | |
| 5. | ጎጠኛ | | | |
| 6. | ቂልነት | | | |

## በቃላት ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾች

በአማርኛ የቃላት ሥርዐት ውስጥ አንዳንድ ድምጾች በቃላት ውስጥ ሲጠብቁና ሲላሉ የትርጉም ለውጥ ያሳያሉ:: ይሁን እንጂ፣ በማንኛውም ቃል ውስጥ የሚገኙ ድምጾች በመጥበቅና በመላላት የተለያዩ ትርጉም ይሰጣሉ ማለት ግን አይደለም:: የትርጉም ለውጥ ያስከትላሉ የተባሉትን በተለያዩ ዐውዶች አስገብቶ ማየትም ለግንዛቤ ይጠቅማል::

**ምሳሌ:-** አበበ <u>ሰባ</u> ብር ሰጠኝ:: → (ላልቶ ሲነበብ) በቁጥር ፸ ብር

የአየለ በሬ <u>ሰባ</u>:: → (ጠብቆ ሲነበብ) ሰውነቱ ስብ አከማቸ፤ (ጮማ ሆነ)

**፫. በምሳሌው መሠረት በግጥሙ ውስጥ ካሉ ቃላት ውስጥ ጠብቀውና ሳልተው ሲነበቡ የትርጉም ልዩነት የሚያመጡ ቃላት ለዩ::**

ሆ ይላል ገበሬ፤
ዲብ እያፈረሰ ባሽልማ በሬ፣
በርዬ በርዬ
አንተን የቻለ ሰው፣
ቶሎ ቶሎ ብለህ፣
አንጀቴን አርሰው፤
እረኛህ ያለቅሳል
ምሳው እያነሰው::

*(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነፅሑፍ መሠረታውያን፣ በምሳሌነት ከተጠቀሙት፣ (47)::)*

## በቃላት ውስጥ የሚርዝሙና የሚያጥሩ ድምጾች

ይህ ፅንሰ ሐሳብ ከፍ ሲል ካልነው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ጠብቆ ተነበበ ማለት ተረግጦ ተነበበ ማለት ነው፡፡ ተረግጦ ተነበበ ማለት ደግሞ ድምጽ ረዝሞ ተነበበ ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ሀ. ገና /ግእንኣ/ ስወደፊቱ ማለት ነው፡፡ (ሳልቶ)

ለ. ገና /ግእንንኣ/ ማለት ደግሞ የገና በዓል ማለት ነው፡፡ (ጠብቆ)

ከዚህ የምንረዳው "ገና" በሚለው ውስጥ ተነባቢ ድምጽ /ን/ ተደግሞ እንደተጻፈ ልብ ይሏል፡፡ ሌላው ሳድስ ድምጾች ቀለም የሚሆኑበትም የማይሆኑበትም ጊዜ አለ፡ ይኸውም በቃል መጀመሪያ ላይ ተጽፈው ከተገኙ ሁልጊዜ ቀለም ይሆናሉ፡፡

**ምሣሌ፡-** ፍቅር /ፍእቅር/ በሚለው ውስጥ /ፍ/ ከሚለው ድምፅ ቀጥሎ /እ/ የምትባለዋ አናባቢ ድምጽ ስለመጣች /ፍእ/ ቀለም ሆኗል፡፡ ሌሎች /ቅ/ ና /ር/ ግን ቀለሞች አይደሉም፡፡

በሌላ በኩል ሳድስ ድምጽ በቃል መጨረሻ ሆኖ የሐረግ መጨረሻ ከሆነና ተረግጦ ከተነበበ ቀለም ይሆናል፡፡

**ምሳሌ፡-** በድንገት ተያይተን /ፍቅር ቢይዛት ፯–፯ ቀለሞች

እኤም ተሸነፍኩኝ /ልቤን ሰጧት ፯–፯ ቀለሞች

**አስተውሉ፡-** በዚህ ግጥም ውስጥ በሁለቱም ስንኞች የመነሻ ሐረጎቹ ማለቂያ ሆሄያት ሳድሶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ቀለማት አይደሉም፡፡ ባንፃሩ የሁለቱም ስንኞች መድረሻ ሐረጎች መጨረሻቸው ሳድስ ሲሆኑ ቀለማት ሆነዋል፡፡ ሲጻፉም /ብኢይዝኣትትእ/ እና /ስእጥእህኡኣትትእ/ ነው፡፡ ስለዚህ ረዝመው ተነበው ቀለም ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ድምጾች ተጎርደው የሚቀሩበት መንገድም አለ፡፡

**ምሳሌ፡-** እጅግ ያቀናል መንገዱ፤

እዳር ተቀምጦ ላየው፤

ማፅበል ይጎዳል ሰው፡፡

የተሰመረበት ቃል ሲያጥር /ዕ/ ቀለም አይደለችም፡፡ በመሆኑም "ማበል" ወደሚል ቃል ትርጓሜው ይቀየራል፡፡ ስለሆነም ያሉት ቀለማት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡

፬. ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ውስጥ በማስረዘም የተጻፋትንና ያጠሩትን ስደታችሁ በማውጣት የተከሰተውን የትርጉም ልዩነትም ሆነ የተከናወነውን የቀለም ምጣኔ አስረዱ፡፡

| | |
|---|---|
| ግጥም 1፡- | በበቅሎ ሆኜ ስዞር፤<br>ካንዱ ወደ አንዱ አገር፤<br>በህልሜም አይደል በእውኔ፤<br>ብዙ ጥብቅ አየሁ እኔ፡፡ |
| ግጥም 2፡- | ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏል ሰለሞን፤<br>እጠይቀው ነበር በተገናኘን፤<br>ሞት እሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን? |

፭. ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርቡት ቃላትና ሐረጋት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለተሰደዩ ተግባራት መለማመጃነት በቀረቡላችሁ ግጥሞች ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ አገባባዊ /አውዳዊ/ ፍቻቸውን ለክፍል አቅርቡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ዐዋይ | 5. አደባባይ |
| 2. ጨፌ | 6. አንጀቱን አርሰው |
| 3. ባድማ | 7. ትቢያ |
| 4. ይፋ | |

፮. ቀደም ሲል ከቀረቡት ግጥሞች ውስጥ ለወጡት ቀጣዮቹ ስንኞች በራሳችሁ አባባል ትርጓሜ ስጧቸው፡፡

1. ሰላም ሲልሽ ቆሟል ከደጅሽ ፍጥረቱ ____________________
2. ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ______________________
3. ከስም አደባባይ ______________________________________

4. ሞት እሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን______________________
5. ህይወቱን ኮነንሽው_______________________________________

## ፯. በምዕራፍ አራት ከግስ ስምና ቅጽል እንደሚመሰረት ተምረናል::

በመቀጠል:-

ሀ. ከቀረቡት ግሶች ስምን መስርቱ::

ምሳሌ:-

| ጥገኛ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ | ስም |
|---|---|---|
| ውፍር | -ኧት | ውፍረት |
| ድፍር | -ኧት | ድፍረት |
| ድርስ | -ኧት | ድርሰት |
| 1. ውልድ | ? | ? |
| 2. ክስር | ? | ? |
| 3. ቅርብ | ? | ? |
| 4. ግሽብ | ? | ? |

ለ. ከቀረቡት ግሶች ቅጽሎችን መስርቱ::

| ምሳሌ: | ግስ | ውልድ ቅፅል |
|---|---|---|
| | አጠረ | አጭር |
| | ወፈረ | ወፍራም |
| | ከበረ | ክቡር |
| 1. | ዘረፈ | ? |
| 2. | በላ | ? |
| 3. | ከሳ | ? |
| 4. | ሰከረ | ? |

## ፰. በሚከተሉት ባዶ ቦታዎች ላይ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡትን ግሶች ወደ ቅፅል እየቀየራችሁ ሙሉ::

1. ከገበታው ላይ አንድ________ (ቆረጠ) ዳቦ ወሰድሁ::
2. ከትናንት ወዲያ አንድ__________ (ተለቀ) ሰው ወደ ቤቴ መጥቶ ነበር::

3. እንደእርሱ ያለ __________ (ታተረ) ሠራተኛ አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡
4. ሊሸጣት ወደዝያ የወሰዳትን __________ (ከሳ) ላም የሚገዛው አላገኘም፡፡
5. እንጀራ በ ______________ (ጠበሰ) ስጋ በላሁ፡፡
6. ሙስና ሀገርንና ወገንን__________ (ገደለ) በሽታ ነው፡፡

## ክፍል አራት፣ ስነ-ጽሑፍ

**፩. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ግጥሞች በማዳመጥ ቀደም ሲል በተማራችሁት መሠረት የግጥም ዓይነቶቹን 'የወል'፣ 'የሰንጎ መገን' ወይም 'የቡሄ በሉ' ግጥም በማለት መልስ ስጡ፡፡**

**፪.** ሀ. ስለትምህርት ቤታችሁ ንጽህና ሁኔታ ባለ ስድስት ስንኝ ግጥም ገጥማችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

ለ. በፉከራ ወቅት የሚፎከርበትን የሰንጎ መገን ግጥም ስልት በመጠቀም ባለ አራት ስንኝ ግጥም ገጥማችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

ሐ. በአካባቢያችሁ ልጆች በዜማና በግጥም የሚሳተፉበት ጨዋታ ካለ ግጥሙን ጽፋችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

**፫. ስለዘይቤ ባለፈው ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ቁም ነገሮች በማስታወስ ቀጥለው በተሰጡት ግጥሞች ውስጥ፡-**

ሀ. ከዘይቤ ዓይነቶቹ ውስጥ የትኛውን /እንቶኔ፤ምፀት ወይስ ግነት/ እንደተጠቀምን ግለጹ፡፡

ለ. ዘይቤዎቹ የሚያስተላልፉትን መልዕክት በአጭሩ ጽፋችሁ አስረዱ፡፡

**ግጥም 1.**

ብቅ በይ-
ብቅ በይ ጣይቱ፣
ወጣ በይ-
ወጣ በይ ውቢቱ-
ሰላም ሊልሽ ቆሟል ከደጅሽ ፍጥረቱ፡፡

*(ደበበ ሰይፉ)*

**ግጥም 2.**

ጽጌያቱ ደረቁ፣ ንቦችሽ አለቁ፣ ሰዎችሽ ደቀቁ፣
ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ፡፡
ዐዋይን ሰማሁዋት ስታለቅስ በይፋ፣
ከጎጆሽ ስትወጣ ትቢያዋን አራግፋ፡፡

*(ደበበ ሰይፉ)*

**ግጥም 3.**

ከፍ በል ወደ ላይ፣
ከስልጣኑ ሰማይ፣
ከስም አደባባይ፡፡
በሀብት ከፍ ከፍ፣
በሹመት ከፍ ከፍ፣
ከፍ ከፍ፣
ከፍ ከፍ፣
ከዚያ የወደቅክ እለት፣
አጥንትህ እንዳይተርፍ፡፡

*(ታገል ሰይፉ)*

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ:-

የግጥም ምንነትና ባህሪያቱን ተመልክተናል:: በዚህም ግጥም ቋጥብና እምቅ እንዲሁም ምትና ዜማ እንዳለው ተመልክተናል:: የወል ግጥም፣ ሰንኀ መገን ግጥም እንዲሁም ቡሄ በሉ ግጥምን ባህሪያት አይተናል:: እንቶኔ፣ ምፀት እና ግነት ዘይቤ በግጥም ውስጥ የሚቀርቡበትን መንገድ ተመልክተናል:: የነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ምንነትና ተግባር ተምረናል:: በቃላት ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾች እንዲሁም በቃላት ውስጥ ድምጾች የሚፈጥሩት የፍች ልዩነት ተመልክተናል:: ስንኞች የሚያስተላልፉን መልእክት በራስ አባባል እንዴት መግለጽ እንደሚቻል ተለማምደናል:: የቅስቀሳና የማነቃቂያ ግጥሞችን በመሰብሰብና ክፍል ውስጥ በንግግር በማቅረብ ዓይነታቸውን ለይተናል:: የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞችን በመመርመር ይዘታቸውን ለይተን ተመልክተናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ግጥም ከስድ ንባብ የሚለይባቸውን ባህሪያት ጥቀሱ::
2. በግጥም ውስጥ ቀለም የምንለው ምንድነው?
3. የሰንኀ መገን ግጥም ባለ ስንት ቀለም ግጥም ነው?
4. የወል ግጥም ባለ ስንት ቀለም ግጥም ነው?
5. ጥገኛ ምዕላዶች በነፃ ምዕላዶች ላይ ሲጨመሩ ምን አገልግሎት ይሰጣሉ?
6. ቀጥሎ የቀረበው ግጥም በየትኛው የዘይቤ ዓይነት የቀረበ ነው?

እንደ ሰው ተወልዶ እንደሰው የማይኖር
እንደ ሰው የማይሞት እንደሰው ሲቀበር
አይተሽስ ሰምተሽስ ታውቂያለሽ ወይ ምድር
ፍረጂኝ! መስክሪኝ!ይህን ክፉ በደል::

*(አበራ ለማ፣ ለኤልሰን ማንዴላ 1977)*

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል። በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ግጥም ምንነትና ዓይነቶች ከቀረበው ምንባብ ተረድቻለሁ። | | | |
| 2. | የተለያዩ የግጥም ዓይነቶች እንዳሉ ተረድቻለሁ። | | | |
| 3. | የአንድን ግጥም መልእክት አገልፃለሁ። | | | |
| 4. | የዘይቤ አይነቶችንና አገልግሎት መግለጽ እችላለሁ። | | | |
| 5 | በነፃና ምዕላዶች የተጨመሩ ቅጥያዎችን ተግባር አገልጻለሁ። | | | |
| 6. | የቃላት መጥበቅና መላላት የሚያመጣውን የፍች ልዩነት አገልጻለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ሰባት

## የአረጋውያን ሚና

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ በቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዓረፍተ-ነገር ትሠራላችሁ።
- ✓ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተጠቅማችሁ ስዕላዊ ድርሰት ትጽፋላችሁ።
- ✓ ድርብና ነጠላ ትዕምርተ - ጥቅሶችን በተገቢ ቦታ ትጠቀማላችሁ።
- ✓ አባባሎችን፣ ምሣሌያዊ አነጋገሮችን ሰብስባችሁ ትርጉማቸውን ታብራራላችሁ።
- ✓ ከተለያዩ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ሐሳቦች በግለ ገለጻ ታቀርባላችሁ።
- ✓ የግጥማዊ ስነ-ቃሎችን ሐሳብ ለይታችሁ ትገልጻላችሁ።
- ✓ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ታደርጋላችሁ።

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች፣ አረጋውያን የሚባሉት የማህበረሰብ ክፍሎች በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ይመስላችኋል?
2. አረጋውያን በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ምን ዓይነት የጎላ ተሳትፎ አላቸው?

## "መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን"

"ዕድሜ መስታወት ነው::" ይህ አባባል፣ ሰዎች እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ ከህይወት ያካበቱት ልምድና እውቀት ጥልቅና ሰፊ መሆኑን ለማመልከት የሚነገር ነው::

አረጋውያን ከህይወት ብዙ የተማሩ፣በአያሌ የኑሮ ውጣ ውረዶች ተፈትነው ያለፉ የእድሜ ባለጸጎች ናቸው:: ከህይወት ልምዳቸው ጥቂት በጨለፍን ቁጥርም ሚዛን የሚደፋ ቁም ነገር አናጣም::

አረጋውያን በዕድሜ መግፋት የተነሳ አካላዊ ቅልጥፍናቸው እየደከመ ቢሄድም እንኳ አቅማቸው በፈቀደው መጠን በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው ልናገኛቸው እንችላለን፤ ይሁን እንጂ፣ በዚህ እድሜያቸው በማህበረሰቡ ጎልቶ የሚታየው የጉልበት ተሳትፏቸው ሳይሆን አእምሮአዊ ሀብታቸው ነው:: አረጋውያን ታዳጊዎችን ስነ ምግባር በማስተማርና በመምከር፣ በግለሰብ መካከል ይሁን በቡድን የሚፈጠሩ ግጭቶችን በማርገብና በመሸምገል በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ክስተቶችን ለአዲሱ ትውልድ በመንገር ታሪክን የማስተላለፍና የመመስከር ከፍተኛ ሚና አላቸው::

## ተማሪዎች ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?

በተለይ ተከታዩን ትውልድ ከመምራትና ቀና መስመር ከማስያዝ አኳያ ያላቸውን ድርሻ ስንመለከት፣ “መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን” የሚለውን ብሒል እንድናነሳ ግድ ይለናል፡፡ አረጋውያኑ የመምከርና የማስተማር ሚናቸውን የሚጫወቱት በዘዴና በማዋዛት ሲሆን፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃዎችም እድሜ ጠገብ የስነ-ቃል ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተረት፣ ቅኔ፣ ቃላዊ ግጥም፣ እንካስላንቲያ … በሳል ሀሳብ የሚያስተላልፉ ጥበቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ስነ-ቃሎች ወጣቶች ወደ ጥፋት እንዳይገቡና አስቀድመው እንዲጠነቀቁ ይመክራሉ፡፡ አንዴ የተፈጸመን ጥፋት ማብሰልሰል ዋጋ እንደሌለውም ይናገራሉ፡፡ የይቅርታን ትልቅነት ይሰብካሉ፡፡ ስንፍናን ይኮንናሉ፤ ጉብዝናን ያበረታታሉ፡፡ ንፉግነትንና ስግብግብነትን ይነቅፋሉ፤ ክፋት ምቀኝነትን ያወግዛሉ፡፡

ለምሳሌ የመተባበርን ጠቀሜታ፡- “ጤፍ ከነወንድሟ ጎተራ ትሞላለች፡፡” በማለት ለዛ ባለው ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ "ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል” በሚል አባባል ችኩልነትን ይቃወማሉ፡፡

በቃላዊ ግጥሞቻቸው ጎበዙን፡-

የበሬው ቄስ የበሬው መምህር፤
አቆላላፊ ክምር ለክምር ፣
ሐምሌ ነሐሴ ያልተራበ ሰው፣
ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው፡፡” እያሉ ያሞካሻሉ፡፡

ሰነፉን ደግሞ፡-

“አንድ ወር አይበቃውም አንድ ዓመት ያረሰው
እንኳን ቤተሰቡ ጎተራው ወቀሰው፡፡” በማለት ያንኳስሳሉ፡፡

አረጋውያን እድሜ አዋቂነትን አጎናጽፏቸዋል፡፡ “አንድ አረጋዊ ሲሞት አንድ ቤተ መጻሕፍት እንደተቃጠለ ይቆጠራል” የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ አረጋውያን ሰናይ ተግባራትን ተመልክተው ይመርቃሉ፡፡ እኩይ ተግባራትን ታዝበው ያወግዛሉ፡፡ ማህበረሰቡም ይህንኑ በዕድሜና በልምድ ያላቸውን የመሪነት ብቃት ተቀብሎ ያከብራቸዋል፡፡ “የሚያድግ ልጅ

አይጥላህ፤ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ" የሚለው አባባል ከላይ ካነሳነው የአረጋውያንን ምክርና ቃል ከማክበርና ከመፈጸም ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዜጎች ማህበረሰቡን በመምራትና በመቆጣጠር በኩል ያላቸውን ሚና ትልቅ ግምት በመስጠት ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና ምንድነው?

ለ. ማህበረሰባችን ለአረጋውያኑ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? በማስረጃ በማስደገፍ አብራሩ፡፡

ሐ. ስነ ቃሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

መ. በወጣቶችና በአረጋውያን መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?

ሠ. ከምንባቡ ሐሳብ በመነሳት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አረጋውያንና ያልተማሩ አረጋውያን በማህበረሰቡ ያላቸው ተቀባይነት እንዴት ዓይነት ይመስላችኋል? በእኩል ዐይን ይመለከቷቸዋል? ወይስ ያበላልጧቸዋል? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፉ፡፡

**፪. የሚከተሉት አባባሎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ የሚያስተላልፉትን መልዕክት አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡**

| | |
|---|---|
| ሀ. ሚዛን የሚደፋ | መ. አዕምሮአዊ ሀብት |
| ለ. የእድሜ ባለፀጋ | ሠ. መሸምገል |
| ሐ. የኑሮ ውጣ ውረድ | ረ. ሰናይ ተግባር |

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፩. በአካባቢያችሁ ያሉ አረጋውያን በልዩ ልዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች /በእድር፣ በቀበሌ፣ ስብሰባ፣ በክብረ በዓላት … /ላይ በመገኘት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሲናገሩ ምክር ሲሰጡና ሲወያዩ ያጋጥሟችኋል፡፡ ይህንን በመፈለግና በመጠቀም አረጋውያኑ በንግግራቸው፣ በጭውውታቸው እንዲሁም በውይይታቸው ያስተላለፉትን መልዕክት ተከታትላችሁ ያገኛችሁትን ፍሬ ሐሳብ አሳጥራችሁ ክፍል ውስጥ ንግግር አድርጉ፡፡

፪. በአካባቢያችሁ ያሉ አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን አስተዋፅኦ አስመልክታችሁ ያያችሁትን፣ ያነበባችሁትን ከሰዎች ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ሐሳብ በጽሑፍ ካጠናቀራችሁ በኋላ ክፍል ውስጥ በቃል አቅርቡ፡፡

፫. በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ በቀረበው ምንባብ፡-

- ስነ ምግባር ማስተማር፣ መምከር፣
- ግጭትን ማርገብ፣ ማስታረቅ፣
- ታሪክን ለትውልድ ማስተላለፍ፣ …

ዋና ዋና ተብለው የተጠቀሱ የአረጋውያን ተግባራት ናቸው፡፡ እናንተም በቡድን በመከፋፈል ከሚናዎቹ አንዱን በመምረጥ ንግግር አዘጋጅታችሁ በመረጣችሁት የቡድን መሪያችሁ አማካይነት ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

፬. የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር የሚደረገው፣ ሰዎችን ለአንድ ተግባር ለማነሳሳት፣ ለማግባባት በመጨረሻም በተግባር /በድርጊት/ ለማሳተፍ ነው፡፡ አረጋውያን የአካባቢውን ህዝብ በሥራ ለማሰማራትና ማህበራዊ ችግር ለመፍታት የተለያዩ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግሮችን፣ አባባሎችን ይጠቀማሉ፡፡ ንግግሮቹ በግጥም፣ በምሣሌያዊ አነጋገር … ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች እናንተም አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቀሟቸውን አባባሎች በመረጃነት በመጠቀም በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ላይ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር አዘጋጅታችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ ሰዋስው

### የቃላት ቀጥተኛ ፍች

የቃላት ቀጥተኛ ፍች የምንለው መዝገበ - ቃላት ላይ ሰፍሮ የምናገኘውን የቃሉን ፍች ነው፡፡

የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ቀጥተኛ ፍች በምሳሌነት ተመልከቱ!

- አዛውንት → ሽማግሌ ወይም አሮጊት
- ወፈረ → አካል ጨመረ፤ ደነደነ፤ ሰባ፤ ግዙፍ ሆነ፤ ለደለደ
- ማገጠ → ባለገ፤ ተበላሸ፤ ዋልጌ ሆነ
- ቀጠሮ → አንድ ነገር ለመስራት' ለመገናኘት የሚደረግ የቦታ፣ የጊዜ ውሳኔ

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍች ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በደብተራችሁ አስፍሩና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ትንቢት፡______________ | ረ. መባቻ፡______________ |
| ለ. ፋና፡______________ | ሰ. በለተ፡______________ |
| ሐ. ሁዳድ፡______________ | ሸ. አበጀ፡______________ |
| መ. ኩርባ፡______________ | ቀ. ዘበተ፡______________ |
| ሠ. ህዳሴ ፡______________ | በ. አለመ፡______________ |

፪. ከአረጋውያን ጋር ተያያዥነት ያላቸው አምስት ቃላት ከመዝገበ ቃላት ከነፍቻቸው አምጥታችሁ ክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

፫. ምሳሌውን ከተመለከታችሁ በኋላ ከታች ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች በመስጠት በቃሉ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዓረፍተ-ነገር ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ምሳሌ፡-** ደፈረሰ → ተመሳሳይ ፍች = ተበጠበጠ ፣ ታወከ ፣ ተሸበረ
→ ተቃራኒ ፍች = ጠራ ፣ ተረጋጋ

ሀ. ሠፈር ውስጥ በተነዛው ወሬ የቤተሰቡ ሰላም ታወከ፡፡
ለ. ፖሊሶቹ ፈጥነው በመድረሳቸው ገበያው ተረጋጋ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ተቻ | 3. አፈሰ | 5. ገነባ |
| 2. አገደ | 4. ነፈገ | 6. አደፈ |

፬. ከዚህ በታች የቀረበው አጭር ጽሑፍ ድርብና ነጠላ የጥቅስ ምልክት ይጎድሉታል፡፡ አስቀድማችሁ በተማራችሁት የጥቅሶች አገልግሎት መሠረት የጥቅስ ምልክቶቹን በተገቢ ቦታ በማስገባት አሚልታችሁ ጻፉ፡፡

ዙሪያዋን የከበቧት ሰዎች ስለምን እያወሩ እንደሆነ ቢገባትም እንዳ ልሰማችና እንዳልገባት ለመሆን ሞከረች፡፡ በፈርጥ የተንቆጠቆጠው ነጭ የሙሽራ ልብሷ ሰውነቷን አለቅጥ ወጥሮ አስጨንቋታል፡፡ የዛሬን አያድ ርገውና እናቷ የእኔ ልጅ ወገቧ እኮ ችቦ አይሞላም እያሉ የሚያሞግሱት ሸንቃጣ ቁመናዋ በድብኝት መሳይ ቅርፅ ተተክቷል፡፡ ሁሉ ነገር አስጠላት የጎረቤት መጠቋቆሚያ መሆኗ አበሳጫት፡፡

ተው ይሄ ሥርግ ይቅርብን ብለው እናትሽ ሰው አያደርጉኝም ብሎ ጉድ ያደረገኝ አቶ ደረጀ ነው በማለት በባሏ ክፉኛ ተብሰከሰከች፡፡ ወዲያው አንደኛ ሚዜዋ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብላ ደረጀ ወደ ቤት እየቀረብን ነው ፎቶ ግራፍ አንሺውም ተዘጋጅተሽ ጠብቂኝ ብሏል ብሎ ደውሎ ነበር አለቻት፡፡ ሙሽሪትም በታከተ አንደበት አያቴ ድሮ እዩኝ እዩኝ ለደብቁኝ እያለች ስትተርት አይገባኝም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ይኸው ትርጉሙ ግልጽ ሆነልኝ በማለት ብሶቷን አሰምታ ፊቷን በነጭ መሀረቧ ማባበስ ጀመረች፡፡

## ክፍል አራት፡ ስነጽሑፍ

### ስዕላዊ ድርሰት

ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ምስልና ገጽታ በቃላት አማካይነት ስሎ ለማቅረብ የሚሞክር የድርሰት ዓይነት ነው፡፡ በዚህ የድርሰት ዓይነት ደራሲው የሚጠቀምባቸው ቃላት በሰው አእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

አምሳሉና ደምሴ (1982፡ 130) ስዕላዊ-ድርሰትን ሲገልጹት “ያንድን ነገር ሁናቴ በዓይን እንዳዩት በእጅ እንደዳሰሱት በጆሮ በቅርብ ሆነው እንደሰሙት በጠቅላላው ግዙፍ አድርጎ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው” ይላሉ፡፡

**የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት**

ለጠረጴዛው ጎኗን ሰጥታ እግሮቿን አነባብራ ተቀምጣለች። ክንዷን ጠረጴዛው ላይ አስደግፋ መዳፏ ላይ ጋደም ብላለች፤ አውራ ጣቷ ክብ አገጯ ስር ገብቶ በሌባ ጣቷ ጉንጯን እንደማከክ እያለች ትተክዛለች፤ ሀሳብ የያዘው ወይም የተገረመ ሰው ትመስላለች።

ጥቁር፤ የሚያብለጨልጭ ቀሚሷ የሻማውን መብራት ሲስብ ፤ እንደ አልማዝ የሚያበራው ጉትቻዋ መልሶ ይወረውረዋል። በተለይ የወርቅ ቀለም ካለው ነጠላ ጫማዋ ውስጥ ለብቻው ሾልኮ ወጥቶ የሚታየው አውራ ጣቷ የባለጌ ልጅ ምላስ ይመስል በሰው ላይ ያሾፋል፤ ይቀልዳል። *(በዓሉ ግርማ 1962፣ 37)*

**፩. በአካባቢያችሁ የሚገኘውን የገበያ ስፍራ ሁኔታ ከላይ የተሰጠውን የስዕላዊ ድርሰት ማብራሪያን መሠረት አድርጋችሁ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን ወይም ሐረጋትን በመጠቀም ከሶስት አንቀጽ ያልበለጠ አንድ ስዕላዊ ድርሰት ጽፋችሁ ክፍል ውስጥ አንብቡ።**

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ምሳሌያዊ አነጋገር በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሠረት የሚፈጠር በቁጥብና በምርጥ ቃላት በአጭሩ የሚነገር የተጨመቀ ጥልቅ ሐሳብን የያዘ የስነ-ቃል ዓይነት ነው።

ምሳሌያዊ አነጋገር ለሀሳብ መቋጫ፣ ማጠናከሪያ፣ ማጉሊያና ግልጽ ማድረጊያ ይሆናል። ሰዎች በንግግራቸው ጣልቃ እያስገቡ ምሬታቸውን፣ ምኞታቸውን፣ ሀዘን-ደስታቸውን፣ ስለህይወት ያላቸውን አመለካከት ያንጸባርቁበታል። እምነታቸውን ይገልጹበታል። በተጨማሪ ቅሬታቸውን የሚያሳውቁበት አስነዋሪ ተግባርን የሚነቅፉበት መልካሙን የሚያሞግሱበት እጥር ምጥን ያለ የሀሳብ መግለጫ ነው።

/ዘሪሁን አስፋው፣ 1992፣ 35፡36/

የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡-

* ስግብግብነትን የሚነቅፉ፣
    - "ሆዳም ቢፈተፍት የበላ ይመስለዋል፤"

* የምቀኝነትን መጥፎነት የሚነግሩ፡-
  - “ምቀኛ ጠላቱን ይተክል ወዳጁን ይነቅል፤”
* ላለፈ ነገር መቆጨት ትርጉም እንደሌለው የሚመክሩ፡-
  - “ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም፤”
* ችግር ሳይጠና በጊዜ መፍትሔ መፈለግ ግድ መሆኑን የሚነግሩ፡-
  - “አረምን መንቀል ስር ሳይሰድ ነው”፡፡
* ብቻ መልፋት ውጤታማ እንደማያደርግ የሚነግሩ
  - “አንድ ጣት ቁንጫ አይገድልም፤”

**፪. ቀጥሎ የተሰያዩ ገጠመኞች በትረካ መልክ ይቀርቡላችኋል፡፡ በትረካው የቀረቡትን ዐውዶች በመመርመር ተስማሚ ምሳሌያዊ አነጋገር በመፈለግ ባዶ ቦታውን አሟሉ፡፡**

1. አቶ መፍትሔ ቸር ሰው ናቸው፡፡ ሰው በልቶ የሚጠግብ ጠጥቶ የሚረካ አይመስላቸውም፡፡ ይህንን ቸርነታቸውን ያወቀ ሁሉ ታዲያ ቤታቸውን ሳይረግጥ አይውልም፡፡ ጥግነህ የአቶ መፍትሔ ወዳጅ ሆኖ ቤታቸው ገባ ወጣ ማለት ከጀመረ ወራትን አስቆጥሯል፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀንም በልቡ ሲያውጠነጥነው የከረመውን ሐሳብ በተግባር ፈጸመው፡፡ አቶ መፍትሔ ዘመድ ሞቶባቸው ራቅ ወዳለ አካባቢ መጓዛቸውን አስተውሎ በረት ሙሉ ከብታቸውን እየነዳ ከአገር ጠፋ፡፡ አቶ መፍትሔ ጉዳቸውን ሲሰሙ __________ ብለው ተረቱ፡፡
2. ጥናቱን በጥሩ ሁኔታ ሠርተው ያቀረቡት ስለሺና ጌጤ ቢሆኑም ምስጋናና ክብር ያገኙት ግን አለቃቸው አቶ መኳንንት ናቸው፡፡ ለዚህ አይነቱ አጋጣሚ ________________ የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ተስማሚ ነው፡፡
3. በዘውዴና በባለቤቷ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እየከረረ በመምጣቱ በሽማግሌዎች እየታየ ነው፡፡ ዘውዴ የምትወዳት ጓደኛዋ ትብለጥም ከባለቤቷ ጋር መጋጨቷን ሰምታ ሁለቱን ለማስማማት ላይ ታች ማለት ጀምራለች፡፡ ይህንን የታዘቡ ጎረቤቷ እመት አረጋሽ ______________ብለው ተረቱባት፡፡

4. የአማርኛ መምህሯ የተማሪዎቻቸውን የቤት ሥራ ለመሰብሰብ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከፊት የተቀመጡት ተማሪዎች የቤት ሥራቸውን ለማሳየት ፈጠን ብለው ሲያወጡ ከኋላ የተቀመጡት ልዕልትና መዲና ግን ከሳምንት በፊት የተሰጠውን የቤት ሥራ አሁን ለመሥራት ይንደፋደፉ ጀመር፡፡ ይህንን ያስተዋሉት መምህርትም የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ተናገሩ፡፡
5. ሔኖክ ገንዘብ አያያዝ አታውቅም በሚል ሰበብ ከሁለት ዓመት ጓደኛው ተለያይቶ ሌላ የሴት ጓደኛ ይዟል፡፡ ሔኖክ እንደተመኘው አዲሷ ጓደኛው እንኳን ገንዘቧን በአግባቡ ልትይዝ የእሱንም በሰበብ አስባቡ ታጫርሰው ገባች፡፡ ሔኖክም የቀድሞ ጓደኛውን እያሰበ __________ ብሎ በራሱ ላይ ተረተ፡፡

**፫. ከተከታዮቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሁለቱን በመምረጥ ሲነገሩ የሚችሉበትን ዐውድ ፈጥራችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል፡፡
2. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ፡፡
3. ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል፡፡
4. አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይጸጸቱ፡፡
5. ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም፡፡

## ቃላዊ ግጥሞች /ሽለላና ፉከራ/

ቃላዊ ግጥም አመንጪው (ደራሲው) በትክክል አይታወቅም፡፡ ስለዚህ ባለቤቱ ህዝብ ነው፡፡ በቃል ተደርሶ በቃል ሲከወንና በቃል ሲተላለፍ የኖረ ጥበብ ሲሆን፣ ከዜማ ጋር በዘፈንና በእንጉርጉሮ ይከወናል፡፡

ቃላዊ ግጥሞች በሰርግ፣ በክብረ በዓላት፣ በሙሾ፣ በስራ ቦታ፣ በልጆች ጨዋታ፣ በጦርነት ወቅት … ላይ ይደረደራሉ፤ ይዜማሉ፡፡ ይዘታቸው የፍቅር፣ የጥላቻ፣ የናፍቆት፣ የትዝታ፣ የብሶት፣ የንቀት የሙገሳ … ሊሆን ይችላል፡፡

ሽለላና ፉከራ የሚከወኑበት አጋጣሚና የሚከወኑበት ዓላማ አንድ ሆኖ በአቀራረባቸው ግን የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው የቃላዊ ግጥም ዘርፍ ናቸው፡፡

ብዙውን ጊዜ የሚከወኑት ማህበረሠቡን ለማነሳሳት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ሲፈጠሩ ነው። በሚከወኑበት ጊዜ ከዋኙን እንዲሁም አድማጩን /ተመልካቹን/ በስሜት በመሙላት አካሉና አእምሮው እንዲበረታና በሀሴት እንዲሞላ ከዚያ አልፎ በወኔ እንዲነሳና ለዓላማውም እንዲጸና ያደርጋሉ።

አከዋወናቸውን በተመለከተ ሽለላ በዜማ በባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ /ክራር፣ ማሲንቆ፣ ዋሽንት /ታጅቦ የሚቀርብ ሲሆን ፉከራ ግን በቃል ንባብ መልክ የሚቀርብ ነው።

በሁለቱም ውስጥ ያሉ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ጀግናን፣ደፋርን የሚያወድሱ፣ የሀገርን ፍቅርና ክብር የሚሰብኩ፣ ፈሪና ሰነፍን የሚኮንኑ ናቸው። ሽለላና ፉከራ ወኔ በመቀስቀስ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ስነ ቃሎች ናቸው።

**፬. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ሐሳብ በዋናነት በመመርመር የፍቅር፣ የሙገሳ፣ የጥላቻ፣ የንቀት፣ የነቀፋ፣ የብሶት... እያሳችሁ መልሱ።**

**ምሳሌ፡-** “አንጎራጉራለሁ የደላኝ መስዬ፣
ሌሊቱ እንዲነጋ ቀኑ እንዲመሽ ብዬ።” /ብሶትን የሚገልጽ/

1. ገዳይ በየበሩ በየሽንተረሩ
   ይፈለግ የለም ወይ የአዳኝ ውሻ ዘሩ።
2. የእገሊት ወዳጅ ጭራሽም ልብ የለው፣
   የወንድሙ ሬሳ ወድቆ የከረመው፣
   ልብማ ቢኖረው ደሙን ይመልሳል፣
   በግንባሩ ደፍቶ አንጀቱን ያርሳል።
3. ከሳሽን ጠቆርሽን ይለኛል ባላገር፣
   የሆዴን አውጥቼ ለስንቱ ልናገር።
4. የሳር ውስጥ መንገድ ይመስላል ወገቡ፣
   መቼ ያስታውቃል ራቡ ጥጋቡ።

5. ልብ አልባ ነበር የሴት ወይዘሮ እቃ፣
ወርቅ እንቁ ነበር የሴት ወይዘሮ እቃ፣
አወይ የኔ ነገር ሄደች ልቤን ታጥቃ።

6. በበጋ እንዳያርስ ፀሐይ እየፈራ፣
በሐምሌ እንዳያርስ ዝናብ እየፈራ፣
ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ።

7. እንደገንቦ ጠላ ብትንደቀደቂ፣
እንደ ጓሮ ጎመን ብትንከረፈፊ፣
ወደደኝ ወደድኩት እንግዲህ እረፊ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥቅስ ምልክቶች ነጠላ (‹ ›) እና ድርብ (" ") ተጠቅመን መልመጃዎችን ሠርተናል:: ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ገጽታና ምስል በቃላት አማካይነት ስሉ ለማቅረብ የሚሞከር የድርሰት ዓይነት እንደሆነ ተመልክተናል:: ሸለላና ፉከራ በግጥም የሚቀርቡ ወኔ ቀስቃሽ የስነቃል ዓይነቶች መሆናቸውን አይተናል:: የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ሰጥተናል:: የአያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት እንዲሁም ሀረጋት አገልግሎትን ተገንዝበን በተግባር ተጠቅመንባቸዋል:: የጽሑፍ ንግግርን አዘጋጅተናል:: ለተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች መስጠት ችለናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የነጠላ (‹ ›) እና የድርብ (" ") ጥቅስ ምልክቶችን አገልግሎት በአጭሩ ጻፉ::
2. አንድን ጭውውት ወይም ንግግር አዳምጦ ማስታወሻ ለመያዝ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
3. ስዕላዊ ድርሰት በምን ዓይነት ስልት የሚቀርብ ድርሰት ነው? በአጭሩ አብራርታችሁ ጻፉ::
4. ሸለላና ፉከራ መቼ፣ ለምን ዓላማ ይከወናሉ? አጠር አድርጋችሁ ግለጹ::
5. የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር የሚያደርግ ሰው ንግግሩ ተቀባይነት እንዲኖረው ምን ማድረግ አለበት?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ለቀረቡልኝ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የድርብና ነጠላ ጥቅስ ምልክቶች አገልግሎት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የአያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት አገልግሎት ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የጽሑፍ ንግግር ለማዘጋጀት ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቄአለሁ፡፡ | | | |
| 5. | የስዕላዊ ድርሠት አጻጻፍን በመረዳት እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6. | የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ፍች መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7. | የሽለላ፣ የፉከራ ቃላዊ ግጥሞች ባህሪይ እና አከዋወን ምን እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# ሴቶች በባህል ውስጥ

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች:-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ✓ ሴቶች በባህል ውስጥ ያላቸውን ሚና ለይታችሁ ትናገራላችሁ፤ ትጽፋላችሁ።
- ✓ መመሪያን ተከትላችሁ ትወያያላችሁ፣ ትከራከራላችሁ፤
- ✓ በሴቶች ዙሪያ የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ታቀርባላችሁ፤
- ✓ ለፈሊጣዊ አነጋገር ፍች ትሰጣላችሁ፤
- ✓ ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ታሟላላችሁ፤
- ✓ የቅኔን ህብረ ቃል ለይታችሁ በማውጣት ሰምና ወርቅ ፍች ትሠጣላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ባህል ማለት ምን ማለት ነው?
2. የሴቶችንና የባህልን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ ሴቶችን የሚጎዱ ጎጂ ልማዶች አሉ? ካሉ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
4. ሴቶችን የሚጎዱ ልማዶች ለማስወገድ መፍትሔው ምን ይመስላችኋል?

## "የሴቷ መንገድ"

ባህል ሰፊና ብዙ ጉዳዮችን የሚያካትት ማዕቀፍ ነው፡፡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ገፅታዎችም አሉት፡፡ ባህል አንድ ማህበራዊ ቡድን የሚገለገልባቸው ቁሶችን እንዲሁም ማህበራዊ መተዳደሪያ ደንቦችን ያጠቃልላል፡፡ በዚህም ውስጥ አስተሳሰቦች፣ ጥበቦች፣ እምነቶች፣ ልማዶች ይነሳሉ፡፡ እነዚህ በሰው ልጅ አካባቢያዊ እውቀት ላይ የተመሠረቱ ፈጠራዎች በዘልማድ በማህበረሰቡ እየተተገበሩ ለዘመናት ቆይተው የአኗኗር ዘይቤው ይሆናሉ፡፡

ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሰዎች ለመልካም ብለው የሚተገብሯቸው ልማዳዊ ድርጊቶች አንዳንድ ጊዜ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ሲያመዝን ይታያል፡፡ በተለይ በሴቶች ላይ ሲፈጸሙ የኖሩት አንዳንድ ልማዳዊ ድርጊቶች ሴቶች ለረጅም ዘመናት የጨለማ ህይወትን እንዲገፉ ያስገደዱ ነበሩ፡፡ ለአብነትም ያህል የሴት ልጅ ብልት ትልተላ፣ ጠለፋ፣ የውርስ ጋብቻ፣ ያለ እድሜ ጋብቻ፣ ሴትን ልጅ በማጀት ውስጥ ብቻ ወስኖ ማስቀመጥን... መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ጎጂ ልማዶች ሴቶችን ለከፋ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት እየዳረጉ ዘመናት አስቆጥረዋል፡፡ የሚገርመው ግን ድርጊቶቹ ቀጣይነት እንዲኖራቸውና ለትውልድ እንዲተላለፉ የሴቶቹ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ ሴቶቹ በባህል ስም የሚፈጸሙባቸውን ጎጂ ድርጊቶች በዝምታ ተቀብለውና ጉዳታቸውን በውስጣቸው አምቀው፣

የድርጊቶቹን አስፈላጊነት ለልጆቻቸው እየሰበኩ ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ያላቸውን ክብርና ታማኝነት ያሳያሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒ እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በመቃወም አንገታቸውን ቀና አድርገው ሽንጣቸውን ገትረው የሚሟገቱ ጥቂት ደፋር ሴቶችም አልታጡም፡፡ ወደዚህ አስቸጋሪና ውስብስብ ትግል ገብተው ድልን ከተቀዳጁ ጥቂት ጀግና ሴቶች መካከል የአንዷን ተሞክሮ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**ተማሪዎች ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ? የሚቀጥሉት አንቀጾች በበለጠ በምን ጉዳይ ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?**

ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ “ሴት ልጅ አደባባይ ልትውል አይገባም” በሚባልበት ዘመን ተፈጥረው፣ የባህሉን ጫና በጥረትና በትጋት አልፈው ለስኬት የበቁ ኢትዮጵያዊት ናቸው፡፡ የእኚህ ጠንካራ ሴት መንገድ ምን ይመስል ነበር?

ቦጋለች (የአካባቢዋ ሰዎች እንደሚጠሯት ቦጌ) የተወለደችው ከአዲስ አበባ ፫፻፶፭ ኪ.ሜ በስተደቡብ ምዕራብ የከንባታ ጠንባሮ ዞን ‘ዛቶ’ በተባለች ትንሽ መንደር ነው፡፡ ቦጌ በተወለደችበት ዘመን በዛቶ የትኛዋም ሴት ወደትምህርት ቤት እንድትሄድ አይፈቀድላትም፡፡ ሴት ልጅ ከማጀት ጉዳዮች አልፋ ለትልቅ ቁምነገር ትደርሳለች ተብሎ በማህበረሰቡ አይታሰብም፡፡ ይልቁንም ሴቶችን የሚጫኑ ልዩ ልዩ ጎጂ ልማዶች የሚከወኑበት በተለይ የሴት ልጅ ግርዛት በእጅጉ ተስፋፍቶ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡

የትንሿ ቦጌ መንገድ ግን የተለየ ነበር፡፡ ከቢጤዎቿ ፈጥና የነቃችው ቦጌ ወደ አጎቷ ቤት ጎራ እያለች ፊደል ከቆጠሩ ዘመዶቿ ፊደል ለየች፤ ማንበብና መጻፍ ቻለች፡፡ የቤት ውስጥ ሥራዋን ካጠናቀቀች በኋላ ቤት ውስጥ ለምግብ ማብሰያ በሚቀጣጠለው እንጨት ብርሃን ሥራዬ ብላ ጥናቷን ተያያዘችው፡፡ ትጋቷን የተመለከቱ አባቷ ትምህርት ቤት

እንድትሄድ ፈቀዱላት፡፡ በቀን እስከ 6 ማይል ርቀት በእግሯ እየተጓዘች ትምህርቷን ቀጠለች፡፡ በግምት የዘጠኝ ዓመት ልጅ ስትሆን አራተኛ ክፍልን አጠናቅቃ ወደ አምስተኛ ክፍል ገባች፡፡ ይህም በመንደሯ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአራተኛ ክፍል በላይ የደረሰች ሴት አደረጋት፡፡

በተማረቻት እውቀት ለአባቷና ለመንደሯ ሰዎች ማመልከቻ በመጻፍ በቀናነቷ የተመሰገነችና የታወቀች ሆነች፡፡ ይህም አንድ ማዕረግ አሰጣት፡፡ በከምባታ ባህል አባት ለክብሩ መግለጫ የሚጠራው በመጀመሪያ ወንድ ልጁ ሲሆን እናት የምትጠራው ደግሞ በመጀመሪያ ሴት ልጇ ነበር፡፡ ቦጌ ግን ነገሩን የተገላቢጦሽ እንዲሆን አደረገች፡፡ የአካባቢው ሰው አባቷን በእሷ ስም "የቦጋለች አባት" እያለ መጥራት ጀመረ፡፡

ቦጌ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ ከመጣች በኋላ በአገኘችው የነፃ የትምህርት እድል ወደ እስራኤል ሀገር ተጓዘች፡፡ እስራኤል ሀገር ስትማር ከሚሰጣት የኪስ ገንዘብ በመቆጠብም ወደ ሀገሯ ተመልሳ ለአባቷ በዛቶ መንደር የመጀመሪያ የተባለ የቆርቆሮ ቤት ሠራች፡፡ ቦጌ በአካባቢዋ አሁንም አስደናቂ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ምክንያት ሆነች፡፡ ቤቱን ከሩቅም ከቅርብም ሰዎች እየመጡ ጎበኙት፤ "ሴት ልጅ እድሉን ካገኘች ለካ ቁም ነገር ትሠራለች" ተባለ፡፡ ቦጌ ባይጻፍም "ሴት ልጅ መደቧ ማጀት ነው" የሚለውን ባህላዊ ህግ የሻረች የመጀመሪያዋ የከንባታ ወጣት ሆነች፡፡

ቦጌ በተለያዩ የውጭ ሀገራት በመዘዋወር ትምህርቷን ስትከታተል ቆይታ 'ኢፒዲሚዮሎጂ' በተባለ የትምህርት ዘርፍ የዶክትሬት ዲግሪዋን ተቀበለች፡፡ በውጭ ሀገራት ለ፳ ዓመታት ከቆየች በኋላ በትውልድ አካባቢዋ ያሉትን ሴቶች ለማገዝ፤ በተለይ በሚፈጸምባቸው ባህላዊ ልማድ /ግርዛት/ ሳቢያ በተለያየ ሁኔታ በእጅጉ የሚጎዱ እህቶቿን ለመታደግ፤ "ምናልባትም አንዲት ሴት ልጅ እንኳ ከግርዛት ባድን" በሚል ተስፋ ወደ ኢትዮጵያ ጠቅልላ መጣች፡፡ እንደ ኤ.አ. በ1998

አካባቢ ከታናሽ እህቷ ፍቅርተ ገብሬ ጋር በመሆን “ከንባቲ ሜንቲ ጌዝማ -ቶጼ (ከሜጌ)” የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት አቋቋሙ፡፡ “ሴት ልጅን መገረዝ ቆሻሻ ማስወገድ ነው” ብሎ ፍጹም ከሚያምነው የአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ጋርም ፊት ለፊት መጋፈጥ ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳ ፍቅርተ ገብሬ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየት በአጭሩ መንገድ ላይ ብትቀርም ቦጌ የእህቷን አላማ ጭምር አንግባ ወደትግሉ ገባች፤ ትግሉ ቀላል አልነበረም፡፡ ፊትም በመንደሯ ስመ መልካም የነበረችው ቦጌ በትዕግስትና በዘዴ የአካባቢዋን ማህበረሰብ እሷ ወደምትፈልገው መንገድ ማስገባት ቻለች፡፡ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2008 ዓ.ም ተጠንቶ ይፋ በሆነው የዩኒሴፍ ጥናት በአካባቢው 97% ያህል ግርዛት መቀነሱ ተገልጿል፡፡

በተለያዩ በጎ አድራጊ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚደገፈው ከምባቲ ሜንቲ ጌዝማ - ቶጼ (ከሜጌ) ያገኘውን ድል በከምባታ አካባቢ ብቻ ላለመገደብ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ በእናቶች ጤና እና ስነተዋልዶ፣ በኤች አይቪ እና በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ማህበረሰብን በማሳተፍ በርካታ ሽልማቶችንና ምስጋና አትርፏል፡፡

ቁርጠኝነት፣ የዓላማ ጽናት፣ ለሌሎች በጎ ለማድረግ እውነተኛ ፍላጎት መኖር ይህችን ትንሽ ሥራ ለወገኖቼ ለመሥራት አብቅቶኛል በሚሉት ጠንካራዋ ሴት በተለይ ሴቶችን ከተለያዩ የባህል ተፅዕኖዎች ለማውጣትና ጤናማና ነፃ ማህበረሰብ ለመገንባት፤ እርስ በእርስ የሚከባበር፣ የሚመካከር፣ የሚማማር፣ ሰላማዊ እኩልነትን የሚያስብ ዜጋ መፈጠር አለበት ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው ማህበረሰቡን በማዳመጥና በማስተማር ነው ብለውም ያምናሉ፡፡

የዶ/ር ቦጋለች መንገድ አባጣ ጎባጣ ቢበዛውም በጽናት ይቀጥላል!

*(ምንጭ “ከሜጌ” ቢሮ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ 2003ዓ.ም)*

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ::**

1. ቀደም ባሉት ጊዜያት በከንባታ ሴት ልጅ ወደ ትምህርት ቤት በባህሉ ይፈቀድ ነበር::
2. ዶ/ር ቦጋለች በተወለዱበት ዘመን ሴቶች የቤት ውስጥ ሥራቸውን ከጨረሱ አደባባይ መዋላቸውን የሚቃወም አልነበረም::
3. የዛቶ አካባቢ ሰዎችን እጅግ ያስገረመው የቦጋለች አባት ቆርቆሮ ቤት የተሠራበት ውድ ገንዘብ ሳይሆን የቦጋለች ተግባር ነበር::
4. የቦጌ አካባቢ ሰዎች የቦጌን ሀሳብ ለመከተል ፍጹም ፈቃደኛ አልሆኑም::
5. በዶ/ር ቦጋለች ጥረት በከንባታ አካባቢ የሴት ልጅ ግርዛት በእጅጉ ቀንሷል::

**፪. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ ምንባቡ ውስጥ ባላቸው ዐውድ ፍቻቸውን ግለጹ::**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ትጋት | 5. | ቁርጠኛነት |
| 2. | ቢጤዎቿ | 6. | ስመ-መልካም |
| 3. | ቁም ነገር | 7. | ግብረ ሰናይ |
| 4. | አንግባ | 8. | ሽንጣቸውን ገትረው |

**፫. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ::**

1. በከንባታ ሴት ልጅ ትገረዝ የነበረው ምን በሚል ምክንያት ነው?
2. ትንሿ ቦጌ በአካባቢዋ ማህበረሰብ ዘንድ ሞገስ ያገኘችባቸውን ሁለቱን ዋና ዋና ተግባራት ግለጹ::
3. ዶ/ር ቦጋለች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ምን ተስፋ ሰንቀው ነው?
4. ሰላማዊ እኩልነትን የሚሻ ዜጋ ለማፍራት ዋና መሳሪያው ምንድን ነው?
5. ከዶ/ር ቦጋለች ህይወት ምን ተማራችሁ?

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

**ክርክር፡-** ማለት ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ዳኞችን በመሰየም የሚያደርጉት ሥርዓት ያለው ሙግት ነው፡፡

### 1. የክርክር ዝግጅት

1.1 ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ ምንጮች ሐሳብ ሰብስቡ፡፡

**ምሣሌ፡-** ከባለሙያዎች፣ ከልዩ ልዩ ጽሑፎች…

1.2 በርዕሱ መሠረት ጠይቃችሁ ካገኛችሁትና ካነበባችሁት ውስጥ ለክርክራችሁ ጠቃሚ የሆኑትን ሃሳቦች በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ያዙ፡፡

1.3 ክርክራችሁን ለአድማጮች ከማቅረባችሁ በፊት በጓደኞቻችሁ ፊት ልምምድ አድርጉ፡፡

1.4 ለክርክር ከመቅረባችሁ በፊት ስብዕናችሁን (ንጽህናችሁን አለባበሳችሁን) በሥነ ሥርዓት አሟሉ፡፡

### 2. የክርክር አቀራረብ

2.1. የመከራከሪያ ርዕሳችሁን ለአድማጮች አስተዋውቁ፡፡

2.2. ፍሬ ሃሳቦቻችሁን በቅደም ተከተል አቅርቡ፡፡

2.3. ረጋ ባለ መንፈስ በልበ ሙሉነት አቅርቡ፡፡

2.4. ከክርክራችሁ (ከምትናገሩት) ነገር የማይስማማ እንቅስቃሴ አታድርጉ፡፡

2.5. ተቃዋሚያችሁ የሚሰጠውን ሐሳብ በትክክል <u>በማዳመጥ ማስታወሻ በመያዝ</u> የተቃውሞ <u>ሐሳብ አዘጋጁ</u>፡፡

2.6. በብጣሽ ወረቀት ላይ ማስታወሻ መያዝ ብትችሉም ማንበባችሁና መያዛችሁ እንዳይታወቅ አድርጉ፡፡

2.7. የምታቀርቡት ሐሳብ /ማስረጃ/ በአድማጮቻችሁ ችሎታ ልክ የተመጠነ ይሁን፡፡

2.8. ለክርክር የተሰጣችሁን የጊዜ ገደብ አክብሩ፡፡

2.9. ከርዕሱ ውጪ የሆነ ሐሳብ እንዳታቀርቡ ተጠንቀቁ፡፡

2.10. ክርክራችሁን ስታበቁ አድማጮቻችሁን አመስግኑ፡፡

*ምንጭ፡- (ደበበ ኃ/ጊዮ/ሕንግዳ፣1999፣ 438)*

፩. ከፍ ሲል የቀረበውን የክርክር መመሪያ በመመርኮዝ በየቡድናችሁ ዝግጅት ካደረጋችሁ በኋላ በምትወክሉት ተወካይ አማካኝነት ከሚከተሉት ርዕሶች በአንዱ ላይ ተመካክራችሁ የክርክር ሃሣባችሁን አቅርባችሁ ተወዳደሩ።

| ቡድን "ሀ" | ቡድን "ለ" |
|---|---|
| ለሴቶች የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል | ለሴቶች የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት አያስፈልግም |
| - | - |
| - | - |
| - | - |

፪. በመምህራችሁ አማካይነት በክርክሩ ወቅት የሰማችሁትንም ሆነ ቀረ የምትሉትን ሀሣብ በማቅረብ በሴቶችና ባህል ዙሪያ ጠቅላላ የክፍል ውይይት አድርጉ።

**ምሳሌ:-** 1. ሴቶች የትዳር ጓደኛቸውን ለመምረጥ ቤተሰብ ጣልቃ ቢገባ የሚያገኙት ጥቅም ምንድን ነው?
2. ሴቶች የትዳር ጓደኛቸውን ለመምረጥ ቤተሰብ ጣልቃ ቢገባ ጉዳቱ ምንድን ነው?
3. ምን የመፍትሔ ሀሣብ ማቅረብ ይቻላል? ወዘተ...የሚሉ።

## ክፍል ሶስት፣ መጻፍ

፩. ከሴቶች ጉዳይ ተጠሪ፣ ከሴት ተማሪዎች ክበብ ተጠሪ ወይም ከሌሎች ኃላፊዎች ጋር በመወያየትና ማስታወሻ በመያዝ "ሴቶች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ስላላቸው ሚና" አጠር ያለ ጽሑፍ አዘጋጁና ለክፍሉ በንባብ አሰሙ።

፪. በቡድን በመሆን በተለያዩ ዘመናት በነበሩ ባህላዊ ሥርዓቶች ሴቶች የነበራቸውን ቦታ የሚገልጹ ጽሑፎችን ካነበባችሁ በኋላ ያገኛችሁትን ሃሣብ በማነጻጸር ጽፋችሁ ወይም በንግግር ለክፍሉ አቅርቡ።

፫. ከፍ ሲል በየቡድኑ ከቀረቡት ሃሣቦች ሆነ በማንበብ ካሠባሰባችኋቸው ሀሣቦች በመነሣት የቅስቀሣና ማነቃቂያ ጽሑፍ (በግጥም ይሁን በስድ (ዝርው) አዘጋጁና በቡድን ተጠሪያችሁ አማካይነት ለክፍሉ አቅርቡና ተወያዩበት።

## ክፍል አራት፣ ሰዋሰው

### የሐረግ አመሰራረት

- ከዚህ በፊ በተማራችሁት መሠረት፣ ሐረግ ማለት ትርጉም ያላቸው ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ አምስት የሐረግ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- ስማዊ ሐረግ፣ ቅጽላዊ ሐረግ፣ ግሳዊ ሐረግ፣ ተውሳከ ግሳዊ ሐረግና መስተዋድዳዊ ሐረግ ናቸው፡፡

**ሀ. ስማዊ ሀረግ፡-** የተለያዩ ስሞችን ቀኝ መሪው ያደረገ የሐረግ ዓይነት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** የሐረር <u>ብርቱካን</u>፣
የበቆሎ <u>ገንፎ</u>፣
የጨርቅ <u>ኳስ</u>፣

**ለ. ቅጽላዊ ሀረግ፡-** ቀኝ መሪው ቅጽል የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** በጣም <u>ከባድ</u>፣
በጣም <u>ሰነፍ</u>፣
በጣም <u>መጥፎ</u>

**ሐ. ግሣዊ ሐረግ፡-** ቀኝ መሪውን የተለያዩ ግሦችን መሪ ያደረገ ሀረግ ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ነጋዴ <u>ነው</u>፡፡ ገበያ <u>ሄደች</u>፡፡
አስተማሪ <u>ሆነ</u>፡፡ መኪና <u>ገዛ</u>፡፡

**መ. ተውሣከግሣዊ ሐረግ፡-** ይህ ሐረግ ተውሳከ ግስን ቀኝ መሪ ያደረገ ሃረግ ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ቁልቁለቱን <u>ቶሎ</u>
እንደጦር <u>ፈጥኖ</u>

**ሠ. መስተዋደዳዊ ሐረግ፡-** ይህ የሀረግ ዓይነት ከሌሎች ይለያል፡፡ ምክንያቱም ግራ መሪ እና ግራም ቀኝም መሪ ሆኖ ይከሰታልና፡፡

**ምሣሌ፡-** 1. ግራ መሪ ሲሆን፡- <u>ስለ</u> ትምህርት
<u>እንደ</u> ትልቁ ልጅ
2. ግራም ቀኝም መሪ ሲሆን፡- <u>ከ</u> ወንዙ <u>ማዶ</u>
<u>እስከ</u> ወንዙ <u>ድረስ</u>
<u>እ</u> ወንበሩ <u>ላይ</u>

**፩. ቀጥሎ የተለያዩ የሐረግ ዓይነቶች ቀርበዋል። ፊት ለፊት በተሰጣችሁ ባዶ ቦታ ላይ የሐረግ ዓይነቶችን ስያሜ አስፍሩ።**

1. በፍጥነት እየተዳከመ ሄደ ______________________
2. እንደ ወንድሙ ክፉኛ ______________________
3. ጕበዝ የአማርኛ አስተርጓሚ ______________________
4. እጅግ በጣም ወንጀለኛ ______________________
5. ከእኛ ቤት ጐን ______________________

**፪. በቡድን በመሆን ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች "ሐተታዊ"፣ "ጥያቄያዊ"፣ ወይም "ትዕዛዛዊ" በማለት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።**

1. ካሣ በግ አልገዛም?
2. ጠጅ አምጣ!
3. እንኳን አደረሰህ።
4. ከአልጋው ላይ ተነስ!
5. ልጁ አስተማሪውን አያዳምጥም።

## ክፍል አምስት፣ ስነጽሑፍ

**፩. ቀጥለው ለቀረቡላችሁ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ከመጻሕፍት ፈልጋችሁ ካመጣችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ እየተጠያየቃችሁ ተወያዩበት።**

**ምሳሌ፡-** ሀ) "እናት ናት" ማለት "ሩህ ሩህ ናት" ማለት ነው።
ለ) "የወርቅ ፍልቃቂ" ማለት "በጣም ቆንጆ" ማለት ነው።

| | |
|---|---|
| 1. "ደመ ግቡ" __________ | 5. "አንገተ ሰባራ" __________ |
| 2. "ማቅ መሰለች" __________ | 6. "አመለ ወርቅ" __________ |
| 3. "የጥርስ ስጋ" __________ | 7. "ባህር ወለድ" __________ |
| 4. "ሀብቷ ቀና" __________ | 8. "እንከን የለሽ" __________ |

**፪. ቀጥለው ያልተሟሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይቀርቡላችኋል። በምሳሌው መሠረት በትክክል አሟልታችሁ በመፃፍ በትርጉማቸው ላይ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።**

**ምሳሌ፡-** ቤት ያለሴት ________________ ።

መልስ፡- ከብት ያለበረት

1. ____________________ አይን ያለቅሳል።
2. ሞኝ የዕለቱን ____________________።
3. ሰው ለወዳጁ __________________።
4. የማይተማመን ባልንጀራ _________________።
5. መልካም ሚስት _____________________።

**፫. ቀጥለው በቀረቡላችሁ ግጥሞች ውስጥ ያሉትን ህብረ ቃላት በማውጣት ሰምና ወርቁን ፍች አሳዩ።**

**ምሳሌ 1፡-** መሸ በሩን ዝጉት ከቀረ ልማዴ፣
ተከፍቶ ማደሩን አይወደውም ሆዴ።

**ህብረ ቃል፡-** ተከፍቶ
**ሰም፡-** ሳይዘጋ ክፍት ሆኖ፣
**ወርቅ፡-** አዝኜ፣

**ምሳሌ 2፡-** ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ፣
በሬ ሳላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ።

**ህብረ ቃል፡-** በሬ ሳላይ
**ሰም፡-** የሚያርስ በሬ አላየሁም
**ወርቅ፡-** በአስክሬን ላይ እየተረማመድኩ መጣሁ

1. ያን ማዶ ተራራ ስፈራው ዱሩን፣
   መልካም ገላለጡት ትሄዱ እንደሆን
2. ልዩ ልዩ ምግብ ምንም ቢኖር በዓለም፣
   እንደ ስጋ ከቶ የሚደግፍ የለም።

3. የማናውቀውን ሌብነት
   ልንሰርቅ ገብተን እሠው ቤት፣
   ይቅርብን ጓዴ እንውጣ፣
   የሚጠብቀን መጣ፡፡
4. ፀጉሯን ስታበጥር ዶሮ እየበላባት፣
   እሽ ስትል ጊዜ እንዴት አማረባት፡፡
5. እያነጋገረኝ ቢጠይቀኝ ወሬ፣
   አላቅም ብዬ ነው አለመናገሬ፡፡
6. ላረቂውም ኮራሽ ለውስኪውም ኮራሽ አንች ግድ የለሽም፣
   የወደድሽው ጠላ አልተገኘልሽም፡፡
7. ሚስቴ በየአዓይነቱ ቁርስ ስትሰጠኝ፣
   ቅንጨዋ ናት በጣም የምትስማማኝ፡፡
8. ላሞቹ አልወለዱ ገና ነው ሰዓቱ፣
   ወተት ወተት ይላል ሰው ሁሉ በከንቱ፡፡
9. ማር ቀምሼ አላውቅም እኔ ወንድማችሁ፣
   የሀገሬ ወጣቶች ተማሩ እባካችሁ፡፡
10. በታንኳ በመርከብ ሲገቡ ብታይ
    ኸረ አባይን በግር ትገባለህ ወይ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የዚህ ምዕራፍ አበይት ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ፡፡ አምስት የሐረግ ዓይነቶችን አይተናል፡፡ ከዚህም በመቀጠል ከሐረግ ከፍ ወደ አለ መዋቅር ገብተን ዓረፍተነገሮችን ስልቶቻቸው መሠረት እየለየን ተመልክተናል፡፡ የተወሠኑ የማስታወሻ አያያዝ ስልቶችን ተከትለን በተለያዩ ስብሠባዎች ላይ በመገኘት በማስታወሻችን ላይ ይዘን በመምጣት ለክፍል ጓደኞታችን ዋና ዋና ሐሳቦችን እንዳካፈልን እናስታውሳለን፡፡ መረጃ አፈላለግንም ተገንዝበን ለክፍል ጓደኞታችን በፅሁፍ/በንግግር መልክ ያገኘነውን ሐሳብ አካፍለናል፡፡ መመሪያን ተከትለንም ውይይትና ክርክር አድርገናል፡፡ ጅምር ምሣሌያዊ አነጋገሮችን በትክክል አሟልተን ጽፈናል፡፡ ለፈሊጣዊ አነጋገሮችም ተገቢ ፍች ሠጥተናል፡፡ የቅኔን ህብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅ መለየታችን አይዘነጋም፡፡ ባጠቃላይ ሴቶች በባህል ውስጥ ስላላቸው ሚና ተረድተናል፡፡ ካነበብነውና ከምናዳምጠው እንዴት ማስታወሻ መያዝ እንዳለብን ተምረናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. <u>እንደፈሪ</u> ለምን ትርበደበዳለህ? የተሠመረበት ሐረግ ዓይነቱ ________ ነው፡፡
   - ሀ. ቅፅላዊ ሐረግ
   - ለ. ስማዊ ሐረግ
   - ሐ. ተውሣከ ግሣዊ ሐረግ
   - መ. ግሣዊ ሐረግ
   - ሠ. መስተዋደዳዊ ሐረግ
2. በክርክር የማያስፈልገው የቱ ነው?
   - ሀ. ማስታወሻ መያዝ
   - ለ. ከአድማጮች ችሎታ በላይ የሆነ ሐሳብ ማቅረብ
   - ሐ. ከአድማጮች ችሎታ በታች የሆነ ሐሳብ ማቅረብ
   - መ. "ለ" እና "ሐ"
3. "አይንና ናጫ" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሳሳይ የሚሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. አይብና ጐመን
   - ለ. እጅና ጓንት
   - ሐ. ሆድና ጀርባ
   - መ. "ሀ" እና "ሐ"
4. "ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ" የሚለውን ምሣሌያዊ አነጋገር ፍች በአጭሩ ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ፡፡
5. በአካባቢያችሁ ስለሴቶች የሚነገሩ አሉታዊ አመለካከቶችን የሚያንጸባርቁ አባባሎችን በማስታወስ ክፍል ውስጥ ትችት ስጡ፡፡
6. የሚከተለውን ቅኔ ህብረቃል፣ ሰም፣ ወርቅ ለይታችሁ አሳዩ፡፡
   
   ባገርቤት ገበያ ከመንከራተት፣
   ከተማ ይሻላል ልብስ ለመግዛት፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ሴቶች በባህል ውስጥ ለሚኖራቸው ሚና ባነበብኩት ምንባብ መሠረት እገልጻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የተለያዩ የሐረግ ዓይነቶችን አመሠራረት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የተለያዩ የዓረፍተ ነገር ስልቶችን ተመርኩዤ አረፍተነገሮች እመሠርታለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የቃላት አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺያቸውን እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ውይይት ሲካሄድ መከታተል ያለብኝን ሥርዓት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 6. | ለተለያዩ ፈሊጦች ምሣሌያዊ አነጋሮች ፍቺያቸውን እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 7. | በሴቶች ዙሪያ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ማድረግ እችላለለሁ፡፡ | | | |
| 8. | ለቀላል ቅኔ የሰምና ወርቅ ፍቻቸውን እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 9. | ካነበብኩትም ሆነ ካዳመጥኩት እንዴት ማስታወሻ መያዝ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ (?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ሱስ

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ በተለያዩ የአረፍተ ነገር ስልቶች ዓረፍተ ነገሮች ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን አቀናጅታችሁ ቃል ትመሠርታላችሁ፡፡
- ✓ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ግጥም ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ህብረ ቃላቸውን በመለየት ቅኔዎችን ትፈታላችሁ፡፡
- ✓ መመሪያዎችን በመከተል የተለያዩ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ፡፡
- ✓ ሥርዓተ ነጥብ /ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ/ ትለያላችሁ፡፡

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ሱስ ምንድን ነው?
2. ሰዎች ወደተለያዩ ሱሶች የሚገቡት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
3. በአካባቢያችሁ ሰዎች በብዛት የተጠመዱት በምን ዓይነት ሱስ ነው? ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?
4. የሱስን አስከፊ ገጽታ አጠር አድርጋችሁ ተናገሩ፡፡

## "የጉስሴው ሰካራም"

“በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው?” ብለው ከገፈርሳ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች “ተበጀ! ሰካራሙ ተበጀ! ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ነው!” ብለው ይነግሯቸዋል፡፡

የህይወቱ ታሪክ ፍጹም ገድል ነው፡፡ ጢም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው፤ የራሱን ጠጉር ውሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም፡፡ ማለዳ አይናገርም፤ በጠርሙስ የሞላውን ከጠጣ በኋላ ማታ ሲራገም ወይም ሲሳደብ፣ ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምጹ ከፈረንጅ ውሻ ድምጽ ይወፍራል፡፡ ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ጋር ሁሉ ማታ ይስቃል፡፡ የሰላምታው ዓይነት እንደወታደር ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው፡፡ ከሰላታው ጋር ድምጽ ትሰማላችሁ ከአፉ የሚወጣውን አንድ ቃል ግን መለየት አትችሉም፡፡

**ተማሪዎች ከላይ ካነበባችሁት አንቀጽ ተበጀ ምን ዓይነት ሰው ነው? ማሕበረሰቡስ ስለእሱ ያለው አመለካከት ምን ዓይነት ይመስላችኋል?**

ከሚያሰክር ሁሉ ለመታረም ብዙ ጊዜ አስቦ ነበር፡፡ ሰክሮ ያደረበት ሌሊት አልፎ ብርሃን በሆነ ጊዜ “ከእንግዲህ መጠጥ አልቀምስም” እያለ በየቀኑ ምሏል፡፡ በነጋታው የበለጠ ጠጥቶ የባሰ ሰክሯል፡፡ ለመስከር ይጠጣል፤ ደስ ያለው እንዲመስለው ይጠጣል፤ ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል፡፡

ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ሥር መልኩን አይተው ያላወቁ ባልቴቶች እንኳ በፍንጃል ቡናን ፉት እያሉ የሌላውን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ እያላከኩ ይሳሳቁበት ነበር።

“ይህን መስከርህን ካልተውህ ላንተ ንስሐ አባት አልሆንህም” ብለው የመጀመሪያ ንስሐ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከእርግማት ጋር አስወግደውታል። ሠራተኞቹም ለርሱ ተቀጥሮ መሥራትን ከውርደት ቆጥረውት እየነቀፉት ሄደዋል። “መጠጥ ካልተውህ አናገባህም” ብለው በየጊዜው ለጋብቻ ጠይቋቸው የነበሩ በቁመናው አሰናብተውታል። በሰንበቴም፣ በማህበርም ማህበርተኛ ለመሆን የጠየቃቸው ነፍሱን ሳይቀር ንቀዋታል።

ብዙ ጊዜ ሰክሮ ኦቶሞቢል ሄዶበታል። ሰክሮ በነጋታው ሲነቃ እራሱን እስር ቤት ውስጥ አግኝቶታል። በጉለሌ መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የውሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ የጉለሌ ህዝብ አውጥቶታል። ሰክሮ የጎርፍ ውሃ ከወሰደው በኋላ ብዙ ጊዜ የእሳት አደጋ ደርሶለታል። ሰክሮ ከቤቱ መድረስ እያቃተው ከወደቀበት ባቡር መንገድ ሳይነሳ፣ ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ጎርፍ ሲሄድበት አድሯል።

ሰዎች መልካም የሰማዕትነት ሥራውን ሁሉ ርካሽ አድርገው ይቆጥሩበታል። በግብረገብ መሠረት አደረግሁት የሚለውን ሁሉ በስካር እንዳደረገው ያናንቁበታል። “በጎ ሥራህን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አለበስከው፤ አንተ ሰው ሰው ሁን ሚስት አግባ ልጆች ይኑሩህ” ይሉና ይዘልፉት ነበር።

ይህ ሁሉ ውርደትና ርክሰት ነው እንጂ ክብር ከቶ አይደለም። ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው። ሰዎች ይሸሹታል፤ ፍጹም ወዳጅነቱንና ዝምድናውን አይሹም። እናም ኑሮው በጨለማ እንደተከበበ ይሆናል። የሰካራሙ ተበጀም እጣ ይኸው ነበር።

*(ተመስገን ገብሬ፣ የጉለሌው ሰካራም፣ 1941፣ 1-8 ለማስተማሪያ እንዲያመች ተሸሽሎ የቀረበ)*

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ትክክል የሆኑትን ‘እውነት’ ስህተት የሆኑትን ‘ሀሰት’ በማለት መልሱ፡፡**

1. ተበጀ የተባለው ሰው በአካባቢው የሚታወቀው ችፍግ ባለ ጢሙና በጎፈሬ ፀጉሩ ነው፡፡
2. ተበጀ ምንም አንኳን በመጠጥ ሱስ የተጠመደ ቢሆንም በማህበራዊ ህይወቱ የተሳካለት ነበር፡፡
3. ተበጀ ድምጹ የሚሰማውና ለአንጧጓሮ የሚነሳሳው መጠጥ  ከጠጣ በኋላ ነው፡፡
4. የመጠጥ ሱሰኛው ተበጀ ሱሱን ለማቆም ብዙ ጊዜ ሞክሮ ነበር፡፡
5. ተበጀ ትዳር መስርቶ የሚኖር ሰው ነው፡፡
6. ተበጀ የቀበሌው እድር አባል የሆነው መጠጥ ለመተው ቃል-ስለገባ ነው፡፡

**፪. ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. “የተበጀ የህይወት ታሪክ ፍጹም ገድል ነው” ሲል ____ ማለቱ ነው፡፡
   - ሀ. አስቂኝ
   - ለ. አስገራሚ
   - ሐ. አስደንጋጭ
   - መ. አስፈሪ
2. የጉለሌ ባልቴቶች የቡና ማጣፈጫ ወሬ የተበጀ_______ነው፡፡
   - ሀ. አረመኔነት
   - ለ. ቅጥያጣ ድፍረት
   - ሐ. ሰካራምነት
   - መ. ዶሮ ነጋዴነት
3. ተበጀ በመጠጥ ሱሰኛነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ________ ነበር፡፡
   - ሀ. የተደነቀ
   - ለ. የተረሳ
   - ሐ. የተወደሰ
   - መ. የተገለለ
4. ተበጀ በመጠጥ ሱሰኛነቱ የተነሳ፣
   - ሀ. ሰው ደብድቦ ታስሮ ነበር፤
   - ለ. ስራ ለመቀጠር አስቦ አልተሳካለትም፤
   - ሐ. የዶሮ ንግድ ከስሮበታል፤
   - መ. ከእድርና ሰንበቴ ተባሯል፤

5. ከላይ የቀረበው ምንባብ የሚያስተላልፈው መልእክት
   ሀ. የመጠጥ ሱስን አስከፊነት
   ለ. የመጠጥን አዝናኝነት
   ሐ. የመጠጥ ሱስን አዋራጅነት
   መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

፫. በምንባቡ መሠረት በ"ሀ" አምድ ለተሰጡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳያቸውን በ "ለ" ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አቅራራ | ሀ. ተዋረደ |
| 2. ከበረ | ለ. ከፍ አለ |
| 3. ነቀፈ | ሐ. አረንቋ ውስጥ ገባ |
| 4. እርባና ቢስ | መ. ዘለፈ |
| 5. ረከሰ | ሠ. ፋይዳ የለሽ |
| 6. አናናቀ | ረ. ዘፈነ፣ ሸለለ |
| | ሰ. አጥላላ |
| | ሸ. አካረረ |

፬. በ"ሀ" አምድ ለተሰጡት ቃላት ተቃራኒ የሚሆኑ ቃላትን ከ "ለ" አምድ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ሸነቆረ | ሀ. አነወረ |
| 2. ነውጥ | ለ. ቆነጠረ |
| 3. ድጉስ | ሐ. አጫ |
| 4. አመሰገነ | መ. ሰላም |
| 5. ጥላት | ረ. ደፈነ |
| 6. ጉራማይሌ | ሰ. ያልተሸፈነ |
| | ሸ. አንድ ወጥ |

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፩. በቡድን ሆናችሁ ሉሰኛ የሆኑ ሰዎች ከሉሳቸው መላቀቅ እንዲችሉ መከናወን ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አጫጭር ነጥቦችን አዘጋጁና በተወካዮቻችሁ አማካይነት ሐሳባችሁን እያቀረባችሁ በጋራ ተወያዩ። አንድ የጋራ መፍትሄ ሀሳብ ላይም ድረሱ።

፪. ሉስን ማቆም ይቻላል ወይስ አይቻልም በሚል ርዕስ ተከራከሩ።

## ክፍል ሶስት፣ ሰዋስው

፩. ምዕራፍ አራት ውስጥ ስለ ዓረፍተነገር ስልቶች መማራችሁ ይታወሣል። በመሆኑም ቀጥሎ በሚሰጧችሁ ምሳሌዎች መሠረት፣ የተሰጀዩ የዓርፍተነገር ስልቶችን ጥንድ ሆናችሁ እየመሰረታችሁ በየተራ በንባብ አሰሙ።

ሀ. ሐተታዊ ዓረፍተነገር ፦ (አወንታዊ፣ አሉታዊ ዐ.ነገር)

**ምሳሌ:-** 1. ጉበዝ ተማሪ በርትቶ ያጠናል። (አዎንታዊ)

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________

**ምሳሌ:-** 2. ወርቁ ትናንት ደብተር አልገዛም። (አሉታዊ)

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________

ለ. ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር:-

**ምሳሌ:-** ራትህን ብላና አጥና!

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________

**ሐ. ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር:-**

**ምሣሌ:-** ለምን ሁል ጊዜ ትረብሻለህ?

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________

**፪. ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቅጥያ ምዕላዶች እየመረጣችሁ ለነፃ ምዕላዶች (ቃላት) ተስማሚ የሚሆኑትን በመቀጠል ቃላትን መስርቱ::**

**ምሣሌ:-**

1. ልጅ (ነፃ ምዕላድ) + - ኦች (ብዛት አመልካች ጥገኛ ምዕላድ)
   ልጆች (ከነፃና ጥገኛ ምእላድ የተመሰረተ ቃል)
2. ሜዳ + ኣማ = ሜዳማ

| | | |
|---|---|---|
| | -ኣት | |
| -ኢያ | -እና | -ኤ |
| -ኧኛ | -አማ | -ና |
| -ማ | -አዊ | -ኦሽ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | መጥረግ | ሠ. | ሰማይ |
| ለ. | ግብ | ረ. | ድንጋይ |
| ሐ. | ጦስ | ሰ. | ድርቅ |
| መ. | ዘመድ | ሸ. | ቅብብል |

## ክፍል አራት:- ስነጽሑፍ

፩. "ሱስ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ጉዳት አለው::" የሚለውን ዓረፍተነገር መንደርደሪያ አድርጋችሁና ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅሶችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ:: የጻፋችሁትን አንቀጽ ለጓደኞቻችሁ በማሳየት በሚሰጧችሁ አስተያየት እንደገና አሻሽላችሁ ጻፉ::

፩. በቡድን በመወያየት፣ ከዚህ ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሶስት ስለአንቀጽ ቅርጽ የተማራችሁትን መሠረት በማድረግም በየአንቀጾቻችሁ ቅርጽ ላይ ተነጋገሩ፡፡

፪. ስለ ሱስ አጭር ግጥም አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ፡፡

**፬. ቀጥለው በቀርቡላችሁ ቅኔዎች ውስጥ ያሉትን ህብረ ቃላት በማውጣት ሰምና ወርቁን ለይታችሁ አሳዩ፡፡**

1. ሽክላ በሩቅ ሲያዩት ብረት ይመስላል፣
   ለመረመረው ሰው ገል አፈር ኖሯል፡፡

   **ህብረቃል፡-** ______________________

   **ሰም፡-** ______________________

   **ወርቅ፡-** ______________________

2. ጠምጄ ነበር ልዘራ ዳጉሳ፣
   ለካስ እረስቼው ዘር የለኝም እሳ፡፡

   **ህብረቃል፡-** ______________________

   **ሰም፡-** ______________________

   **ወርቅ፡-** ______________________

3. ጠጅ ሞልቶ ካኖሩት እንዳይጐድል አውቃለሁ፣
   ሰውን ጠጣው መሬት እንዴት እሆናለሁ፡፡

   **ህብረቃል፡-** ______________________

   **ሰም፡-** ______________________

   **ወርቅ፡-** ______________________

4. ጤና በማጣቷ አዝኜ ስኖር፣
   ደግሞ ባልጋ ሄደች ወይ ዓለማፈር፡፡

   **ህብረቃል፡-** ______________________

   **ሰም፡-** ______________________

   **ወርቅ፡-** ______________________

5. ሥጋ እበላ ብዬ የቆረጥኩትን፣
   ላሳያችሁ መጣሁ እኤማ ጣቴን።

**ህብረቃል፡-** ______________________

**ሰም፡-** ______________________

**ወርቅ፡-**______________________

**ፎ. ቀጥለው የተለያዩ መመሪያዎች ይቀርቡላችኋል። በመመሪያዎቹ መሠረት ጥያቄዎቹን ሥሩ።**

**መመሪያ አንድ፡- በየተራ ቁጥሩ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል በፍችው ልዩ የሆነውን ምረጡ።**

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሀ. | መተረ | ለ. | ሰፋ | ሐ. | ዘመዘመ | መ. | ቀመቀመ |
| 2. | ሀ. | ሒስ | ለ. | ትችት | ሐ. | ነቀፋ | መ. | ዘለፋ |
| 3. | ሀ. | ረብ | ለ. | ፋይዳ | ሐ. | ጥቅም | መ. | እርካታ |
| 4. | ሀ. | ሳበ | ለ. | ዘረጋ | ሐ. | ለጠጠ | መ. | ዘመመ |
| 5. | ሀ. | ሽለላ | ለ. | ፉከራ | ሐ. | ሙሾ | መ. | ቀረርቶ |

**መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ቃላት በ "ሀ" ውስጥ እማሬያዊ ፍቻያቸውን፤ በ "ለ" ደግሞ ፍካሬያዊ ፍቻቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ። የጻፋችኋቸውን ዓረፍተነገሮች ለጓደኛችሁ አሳዩና በሚሰጣችሁ አስተያየት መሰረት አሻሽሉ።**

**ምሣሌ፡-** ጨልሌ፡- ሀ) ጣሪያው ላይ ያረፈውን ጨልሌ በድንጋይ አባረርኩት። /የወፍ ዘር/ እማሬያዊ ፍች፤
ለ) ደላላው ጨልሌ ነው። /ብልጥ/ ፍካሬያዊ ፍች፤

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ቆቅ | ሀ. | ______________ | ለ. | ______________ |
| 2. | እባብ | ሀ. | ______________ | ለ. | ______________ |
| 3. | አኞ | ሀ. | ______________ | ለ. | ______________ |
| 4. | ወንፊት | ሀ. | ______________ | ለ. | ______________ |
| 5. | ገለባ | ሀ. | ______________ | ለ. | ______________ |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ስልትን በመጠቀም፣ ስለሱስ አሉታዊ ጐን በሚገባ ተገንዝበናል፤ ከሱስ መራቅ የሚያስችል እውቀትም ገብይተናል:: የድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ አጠቀቃቀም የሚያስገነዝብ ትምህርትም ቀርቧል:: ቃላት እማሬያዊ - ጥሬ፣ ቀጥተኛ ፍች እንዲሁም ፍካሬያዊ-ውስጠ ወይራ፣ ሚስጥራዊ ፍች እንዳላቸው፤ ይህም ትርጉማቸው በተለያየ አውድ ሲገባ እንደሚፈጠር ተምረናል:: ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች ተቀናጅተው ቃል ሲመሠርቱ እንደሚችሉ በተግባር አይተናል::

የክርክር መመሪያዎችን በመከተል፣ በሱስ ጥቅምና ጉዳት ላይም ተወያይተናል:: በመንደርደሪያ ዓረፍተነገሮች መነሻነትም አንቀፅ በመጻፍ ቅርጽንም አሳይተናል:: የቅኔን ህብረቃል፣ ስምና ወርቅ ፍች እንዴት መለየት እንደምንችል ተረድተናል:: በተሰጠ ርእስ ግጥም መፃፍ ተለማምደናል::

## የክለሣ ጥያቄዎች

1. ሱስ በጥቅሉ <u>ፋይዳ ቢስ</u> ነው:: የተሰመረበት ሐረግ ፍች:-
   - ሀ. ጠቃሚ
   - ሐ. ጥቅም የለሽ
   - ለ. ጉዳት የለሽ
   - መ. አሳሳቢ
2. "የቤት ሥራህን ለምን ሠርተህ አትተኛም?" ይህን ዓረፍተነገር ወደ ሐተታዊ (አዎንታዊ፣ አሉታዊ) ዓረፍተነገሮች ስንቀይረው __________ ይሆናል::
   - ሀ. አዎንታዊ ዓረፍተነገር:-

     ________________________________________
   - ለ. አሉታዊ ዓረፍተነገር:-

     ________________________________________
3. "ኢትዮጵያዊነትሽን" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጥያ ምዕላዶች ብዛት __________ነው::
   ሀ. 1    ለ. 2    ሐ. 3    መ. 4
4. ከአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች ሦስቱን ጥቀሱ::
5. በአንድ አንቀጽ ውስጥ የመንደርደሪያ ዓረፍተነገር መኖር ዓላማ ምንድን ነው?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ሱስን በተመለከተ የቀረበውን ምንባብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | ለቀረቡልኝ ቃላት ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 3. | በዓረፍተነገር ስልቶች ተጠቅሜ የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን እመሠርታለሁ፡፡ | | | |
| 4. | በመንደርደሪያ ዓረፍተነገር ተጠቅሜ አንቀፅ እፅፋለሁ፡፡ | | | |
| 5. | የአንድን አንቀጽ ቅርጽ ከመንደርደሪያ ዓረፍተነገር አቀማመጥ አኳያ መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6. | ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 7. | መመሪያን ተግባራዊ አደርጋለሁ፡፡ | | | |
| 8. | የሚሰጠኝን ቃል በነፃና በጥገኛ ምእላድ እተነትናለሁ፡፡ | | | |
| 9. | ለተለያዩ ቅኔዎች ሰምና ወርቅ ፍቻቸውን እሰጣለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አስር

# ሥራና ምርት

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ ከግስ የተለያዩ ስሞችንና ቅጽሎችን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ✓ ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ከጽሑፍ ውስጥ ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- ✓ የንግድ ሥራ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ በሠንጠረዥ የቀረበን መረጃ ወደ ዝርው ጽሑፍ ትቀይራላችሁ፡፡
- ✓ በዝርው የቀረበውን መረጃ በሠንጠረዥ ታቀርባላችሁ፡፡
- ✓ ለገለጻዎች ዘይቤያዊ ስያሜ ትሰጣላችሁ፡፡

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ሥራና ምርት ያላቸው ግንኙነት ምንድነው?
2. ጠንክሮ መሥራት ለራስ ፣ ለሀገርና ለወገን ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?

## "የሠራ ያገኛል!"

ኢትዮጵያ በርካታ ህፃናትና ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፣ አካባቢዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፖሊሲ አውጪዎችና ፖለቲከኞች ሥራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸው፡፡ ልጆች ትልልቅ ርዕይና ዓላማ እንዲይዙ በቂ ችሎታና ሙያ እንዲኖራቸው ከሁሉም በላይ ወላጆች ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በሁሉም መስፈርቶች እያደገ የሚሄድ ቤተሰብ ኃላፊ የሆኑ ወላጆች ያሏቸው ልጆች፣ ውስጣቸውን እየመረመሩ የቤተሰባቸውን እንቅስቃሴ ወደተሻለ ህይወት የሚቀይሩና ለልጆቻቸው ምሳሌ መሆን የሚችሉ ወላጆች ያሏቸው ልጆች ከወላጆቻቸው የበለጠ ባለ ራዕይ ይሆናሉ፡፡ ህይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ፣ በሂደት የእነሱ ህይወት ከእለት ወደ እለት ለውጥ እያመጣ ሲሄድ፣ በየቤተሰቡ ያለ አንድ ሁለት ሰው የራሴ የሚለው ሥራ ሲፈጥር ተነሳሽነት ያድጋል፤ “ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው!”

አሁን አሁን እንደሚታየው ወላጆች በጣም ውስን የሆነ ህልምና ራዕይ አላቸው፡፡ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ሁሉ ከቤተሰብ አባላትና ከልጆች መኖር አለመኖር ጋር የሚያያይዙ አሉ፡፡ በመሠረቱ ህፃናት ወላጆቻቸውን አስገድደው የተወለዱ አይደሉም፤ ህፃናትን የምንወልዳቸው እኛ ነን፤ በየትኞቹም ኃላፊነቶች በአብዛኛው ተጠያቂዎቹ እኛ ወላጆች ነን፡፡ ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የምንንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፋል፡፡ ኢትዮጵያ የምታድገው እያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ነው፡፡

**ተማሪዎች! ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?**

የኢትዮጵያ ትልቁ ሀብት ወጣቱ ነው፡፡ ወጣቱ አስተሳሰቡ ብሩህ ነው፤ ትኩስ ጉልበት አለው፤ ከፍተኛ የመፍጠር ችሎታ አለው፤ ፈጣን ነው፤ አንድ ጊዜ የጀመረውን ነገር ደጋግሞ በመሥራት ለማሸነፍ ሰፊ የእድሜ ገፀ-በረከት ያለው የህብረተሰባችን ክፍል ነው፡፡ ከማንም የተሻለ መኖር የሚፈልገው ወጣቱ ነው፡፡ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ብዙ መሥራት ያለበትም ወጣቱ ነው፡፡
በጥቂቶች የኢኮኖሚ ነፃ መውጣት ብዙ ሰው ጥሩ ኑሮ መኖር አይችልም፡፡ የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለፀጋ አይሆንም፤ አትሆንም፡፡ ስለዚህ ሥራ ፈጣሪ ለመሆን የበለጠ እድል ላለው ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የሥራ ፍላጎትና ተነሳሽነትን እናስተምረው፡፡

*(ወሮታው በዛብህ፣ ኢንተርፕሬነርሽፕ፣1998፣109፣ ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ፡፡)*

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ከምንባቡ የወጡ ዓረፍተነገሮች በመመርመር ትክክል የሆነውን “እውነት” ስህተት የሆነውን “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ወጣቶች የሥራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ወላጆች ብቻ ናቸው፡፡
2. ሀገር የሚያድገው እያንዳንዱ ቤተሰብ በኢኮኖሚ ሲሻሻል ነው፡፡
3. የሀገርን እድገት በተመለከተ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡
4. ወላጆች ለልጆቻቸው ማውረስ የሚገባቸው ቀና አስተሳሰብንና ታታሪነትን ነው፡፡
5. ወጣቶች በአገር ግንባታ ዘርፍ ሚና የላቸውም፡፡

**፪. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ፍቻቸውን ጻፉ፡፡**

ሀ. የአስተሳሰብ ድህነት፡- ____________________

ለ. ውስን ህልምና ርዕይ፡- ____________________

ሐ. ለልጆች ምሳሌ መሆን፡- ____________________

መ. የእድሜ ገጸ-በረከት፡- ____________________

ሠ. ልምድ ያካበተ፡- __________

**፫. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ሥራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸው የተባሉትን አካላት በዝርዝር ጥቀሱ፡፡

ለ. ወጣቶች ሀገር ለመገንባት ቀዳሚ የህብረተሰቡ ክፍሎች ናቸው የተባለበትን ምክንያት በዝርዝር አስረዱ፡፡

ሐ. ቀና አስተሳሰብ ያላቸውን ልጆች የማፍራት የወላጆች ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህንን ሐሳብ ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት አስተያየት ስጡ፡፡

መ. "ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው" ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል፡፡

ሠ. የምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት (ጭብጥ) ምንድን ነው?

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፩. ጥንድ ጥንድ በመሆን በአካባቢያችሁ ወደሚገኙ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ የህብረት ሥራ ማህበራት በመሄድ ስለ ሥራ እንቅስቃሴያቸውና ተሞክሮአቸው ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በማጠናቀር በተወካያችሁ አማካይነት ለክፍሉ በንባብ አሰሙ፡፡

፪. ሥራና ምርትን አስመልክቶ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር አዘጋጅታችሁ አቅርቡ፡፡ (ለምሳሌ ኢትዮጵያ መገንባት በጀመረችው በህዳሴው ግድብ ዙሪያ ሐሳቦችን አሰባስባችሁ ንግግር ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡)

## ክፍል ሶስት፣ መጻፍ

፩. ከዚህ በታች የሚቀርቡላችሁን አያያዥ ቃላት በመጠቀም "ሥራና ምርትን በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጻፉ::

| | | |
|---|---|---|
| ስለዚህ | ይሁን እንጂ | ነገር ግን |
| በመሆኑም | ወይም | ለምሳሌ |
| እና | ባንጻሩ | ደግሞ |

፪. በሠንጠረዡ የቀረበላችሁን መረጃ መሠረት በማድረግ ርዕስ ሰጥታችሁ፣ አንድ አጭር ጽሑፍ ጻፉ::

| ገበሬው እርሻ ለማረስ ያነሳሱት ምክንያቶች | ያከናወናቸው ተግባራት በቅደም ተከተል | ያመረተው ምርት | ያመረተውን ምርት እንዴት ተጠቀመበት? |
|---|---|---|---|
| • ራሱንና ቤተሰቡን (3 ልጆቹን) በበቂ ሁኔታ ለመመገብ<br>• ልብስ ለመግዛት<br>• የፋብሪካ ውጤቶች (እንደ ዘይት፣ ጨው፣ ሣሙና ...... ያሉትን) ለመግዛት ለመጠቀም<br>• ልጆቹን ት/ቤት ሰ'ዶ ለማስተማር<br>• ሌሎች ፍላጐቶችን ለማሟላት | • የእርሻ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት (ጅራፍ፣ ሞፈር፣ ክርፍ፣ ወገል፣ ቀንበር፣ ማረሻ፣ ድግር፣ ምራን......)<br>• ሦስት እያስተጋገዘ የሚጠምዳቸው በሬዎች መግዛት<br>• ስመቆጥቆጫና ስመጥረብ የሚያገለግል መጥረቢያ (ምሣር) መግዛትና እጀታ ማዘጋጀት<br>• የበሬዎች ማደሪያና የሥራ ዕቃዎች ማዘጋጀት | • ሦስት ጐታ ጤፍ<br>• ሁለት ጐታ ዳጉሣ<br>• አንድ ጉስጉሻ በርበሬ<br>• አንድ ይዘቱ 60ሜ³ የሆነ ጐተራ ሙሉ በቆሎ ወዘተ... | • ልጆቹን፣ ሚስቱንና ራሱን በሚገባ መገበ<br>• ለት/ቤት የሚሆኑ መሳሪያዎቻቸውን ለልጆቹ አሟላ<br>• ቆርቆሮ ቤት ሠራ |
| | • ጤፍ፣ ዳጉሣ፣ በቆሎ (ማሽላ)፣ አተር፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ ወዘተ... ወቅታቸውን ጠብቆ መዝራትና ማረም:: ወዘተ. | | • ስመንንዛና ለማንንዘ የሚሆኑ አንድ በቅሎና አንድ አህያ ገዛ ወዘተ... |

**፫. ቀጥሉ በጽሑፍ የቀረበላችሁን ምንባብ በሚገባ በማንበብ ከጽሑፉ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ጉዳዮችን በመለየት አስቀምጡ፡፡**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት በዓባይ ወንዝ ላይ የህዳሴ ግድብን ሊገነባ ቆርጦ ተነስቷል፡፡ ለዚህ ተግባር እውን መሆንም የሀገሪቱን ተወላጆች ትብብር በመጠየቅ “ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ” የሚለውን ብሂል ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአደረጉት የምረቃ ላይ ንግግር ግድቡን በመገንባት በሀገሪቱ ላይ የሚታየውን የኃይል እጥረት ለመቅረፍ፣ እንደሚያስችል ተናግረዋል፡፡ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ፣ ልማትን በአመርታዊ ሁኔታ ለማፍጠን ፣ የራስን ልማት ከርዳታ ነፃ በሆነና ራስን ችሎ በመሥራት ታሪክ ለማስመዝገብና በጥቅሉ ተፈጥሯዊ ሃብታችን በመጠቀም የኢትዮጵያን ህዝብ ድህነት ለመቅረፍ ሲባል እንደሚከናወን አስረድተዋል፡፡ ይህን ለማድረግም ብዙ ምክክሮች እንደተደረጉ አክለው አስረድተዋል፡፡ህዝቡም “ቦንድ” በመግዛት ራሱን ጠቅሞ ሀገሪቱን እንዲጠቅም ጥሪ ቀርቦለት ለተግባራዊነቱ በመረባረብ ላይ ይገኛል፡፡ ርብርቡ ቦንድ በመግዛት ላይ ብቻ ሳይሆን መዋጮ በማሰባሰብ፣ ቦንድንም ያለ ወለድ በመግዛት፣ የሚፈለግበትንም በመለገስና በመነሳሳት ላይ ያተኮረ ርብርብ ነው፡፡

ግድቡ የሚሠራው ፵፮ ኪ.ሜ ያህል ርዝመት ዓባይን በመገደብ ሲሆን የሚያቆረው ውሃ መጠንም የጣና ሐይቅ ከሚይዘው ሰላሳ አንድ ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የውሃ መጠን በእጥፍ እንደሚበልጥ ማለትም ፷፫ ቢሊዮን ሜትር ኩብ እንደሚሆን ከመገናኛ ብዙሃን የሚወጡ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚመነጭ ታውቋል፡፡ ውሃውም ወደ ቤንሻንጉልና ጉምዝ ለም መሬቶች እየፈሰሰ ለልማት እንደሚውል ይታመናል፡፡ በጥቅሉ የዓሣ ምርታችን ከፍ እንደሚል ፣ የመስኖ ውሃን በመጠቀም ድህነትን ታሪክ እንደምናደርግ፤ ለበለጠ የዕድገት “ትራንስፎር ሜሽን”ም እንደሚያተጋንና ብሩህ ድባብን ያሳየን ክንውን ነው ብሎ መናገር ያስችላል፡፡

| የኢትዮጵያን መንግስት የህዳሴ ግድብ እንዲገነባ ያነሳሱት ምክንያቶች | በቅደም ተከተል ህዝቡን ለማነሳሳት ያከናወናቸው ተግባራት | ግድቡ ሲያልቅ የሚገኘው ውጤት | የተገኘው ውጤት ለምን ተግባር ይውሳል? |
|---|---|---|---|
| | | | |

## የንግድ ሥራ ደብዳቤ

የሥራ ደብዳቤዎች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም የድርጅት ወይም የመ/ቤት የሥራ ደብዳቤ እና የግል የሥራ ደብዳቤ የሚባሉት ናቸው፡፡

የንግድ ስራ ደብዳቤ ከድርጅት ወይም ከመ/ቤት የሥራ ደብዳቤ የሚመደብ ሲሆን አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የንግድ ሥራን (ሽያጭን፣ ግዢን ወይም ልውውጥን) አስመልክቶ ለሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚጽፈው ደብዳቤ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ደብዳቤ የእቃዎችን ዋጋ ለመጠየቅ፣ ለዋጋ መጠየቂያ ደብዳቤ ምላሽ ለመስጠት ስሞታ ካለ ለመሰንዘር፣ ለቀረበው የግዢ ጥያቄ ፈጣንና አርኪ ምላሽ ከተገኘ ምስጋና ለማቅረብ ወዘተ የሚጻፍ ነው፡፡

ቁጥር፡-______________

ቀን፡-______________

**የራስጌ ማህተም**

ለ ______________________________

(ከተማ፤)_______________________

ጉዳዩ፡- ______________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

______________________________::

የግርጌ ማህተም

ከሰላምታ ጋር!

ፊርማ __________

ሙሉ ስም (ኃላፊነት)

ግልባጭ፡- ____________

፬. ቀደም ሲል የቀረበውን የንግድ ሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ መመሪያን እና የንግድ ሥራ ደብዳቤ ናሙና በመከተል በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይና አድራሻ አንድ የንግድ ሥራ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

፭. ስርዓቱን ጠብቃችሁ መጻፍ አለመጻፋችሁን በአጠገባችሁ ከሚቀመጡ ሌሎች ተማሪዎች ጋር በማስተያየት ተወያዩበት፡፡

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

፩. ቀጥሎ በሚቀርበው አንቀጽ ውስጥ ተራና ውስብስብ ዓረፍተነገሮች ተካተው ቀርበዋል፡፡ አንቀጹን ካነበባችሁ በኋላ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ተራና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ በሠንጠረዥ ውስጥ ጻፉ፡፡

አንድ ጅብና አንድ አንበሳ ነበሩ፡፡ ጅቡ አንዲት እርጉዝ ጊደር ነበረችው፡፡ አንበሳውም አንድ ወይፈን ነበረው፡፡ አንበሳው ወይፈኑን የሚጠብቅለት ያጣል፡፡ አንድ ቀን አያጅቦን፣ "አያጅቦ ወይፈኔን ለምን አትጠብቅልኝም?" ብሎ ጠየቀው፡፡ አያጅቦም "ይኸማ በጣም ጥሩ ሐሣብ ነው፡፡ ጊደሬም ከአንተ ወይፈን ጋር ስትውል እሱን የመሰለ ጥሩ ጥጃ ትወልድ ልኛለች"፡፡ ይለዋል፡፡ ከዚያ ተራ በተራ ለመጠበቅ ይስማማሉ፡፡ ከዚያም አያ አንበሶ "አያ ጅቦ እንግዲህ ነገ አንተ ስትጠብቅ ዋል፡፡ እኔ አደን አድኜ ራታችንን ይዤ እመጣለሁ"። ብሎት ይሄዳል፡፡ አያ ጅቦም ጊደሯንና ወይፈኑን ጥሩ ሳርና ውሃ ወዳለበት እየወሰደ ሲያግጣቸውና ውሃ ሲያጠጣቸው ዋለ፡፡ በተጨማሪም ለጊደሩ ለስላሳ ሳር አጨደላት፡፡ ባፍ ባፏም ሲሰጣት ዋለ፡፡

| ተራ ዓረፍተገር | ውስብስብ ዓረፍተነገር |
|---|---|
| አንድ ጅብና አንበሳ <u>ነበሩ</u>፡፡ | አንበሳው ወይፈኑን <u>የሚጠብቅለት ያጣል</u>፡፡ |
| | |

፪. የራሳችሁን አምስት ተራ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች መስርቱና ክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

፫. ከዚህ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ከግስ የተሰያዩ ስም መሰል ቃላትንና ቅፅሎችን መመስረት እንደሚቻል ተምራችኋል፡፡ ምሳሌውን በመከተል መልመጃውን ሥሩ፡፡

| ግስ | ከግስ የተመሠረተ ስም መሰል ቃል | ከግስ የተመሠረተ ቅጽል |
|---|---|---|
| ምሳሌ 1. ቀጠፈ | መቅጠፍ | ቀጣፊ |
| 2. ሰነፈ | መስነፍ | ሰነፍ |
| ሀ. ሰከረ | ______ | ______ |
| ለ. ዘለለ | ______ | ______ |
| ሐ. ቀለለ | ______ | ______ |
| መ. በላ | ______ | ______ |
| ሠ. ከሳ | ______ | ______ |
| ረ. በዛ | ______ | ______ |

## ክፍል አምስት፡ ስነጽሑፍ

፩. የሚከተሉትን የተጓደሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በትክክል አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ሥራ ያጣ መነኩሴ ______________________ ፡፡

ለ. አፍ ሥራ ሲፈታ ________________________ ፡፡

ሐ. ___________________________ ይሞታል በሰኔ፡፡

መ. ስራ ያጣ ገበሬ ___________________፡፡

ሠ. ሥራ ለሠሪው ____________________________ ፡፡

፪. ሥራን የሚያበረታቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ጥንድ ሆናችሁ ሰብስቡና መልእክታቸውን አብራሩ፡፡

**፫. በ"ሀ" አምድ ለቀረቡት የዘይቤ ዓይነቶች ከ "ለ" አባባሎች እየመረጣችሁ አዛምዱ::**

**ምሳሌ** 1. እንቶኔ = ቀ

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. እንቶኔ ___ቀ___.<br>______.<br>______. | ሀ. ያችን ወፍራሟን ልጅ "ቀጮ" ብሎ ጠራት::<br>ለ. ዓባይ አሁንስ ሆድህ ምናለ?<br>ሐ. "ለሰው ሞት አነሰው" አለች ቀበሮ::<br>መ. የሰማይ ስባሪ የሚያክል ዳቦ በላሁ:: |
| 2. ምፀት ______.<br>______.<br>______. | ሠ. ከቀጠሮው ሁለት ሰዓት አርፍዶ ሲመጣ አንተ'ኮ "ጀት" ነህ አለው::<br>ረ. ሰውየው ተራራ አክሏል::<br>ሰ. ምላሷ አርባ ክንድ ስለሆነ ሁሉም ይሸሻታል:: |
| 3. ግነት ______.<br>______.<br>______. | ሸ. "አየሽ አንቺ እናት ዓለም! ቃል የእምነት እዳ እንጂ የእናት የአባት እኮ አይደለም" አለ ቴዎድሮስ::<br>ቀ. ፀሐይቱ ምነው ፊትሽ ጠቆረ? |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ ነጥቦች በአብዛኛው በአለፉት ምዕራፎች ላይ የአያችኋቸውን ሲያካትቱ በጥቂቱ ደግሞ አዳዲሶችም አሉ፡፡ ለምሣሌ የዓረፍተነገር ዓይነቶችን አመሠራረት፣ ከውይይት መልዕክት አዳምጦና በማስታወሻ መዝግቦ ለክፍል ጓደኛ የማቅረብ ልምምድ፣ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግርና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉት ርዕሰ-ጉዳዮች በቀደሙት ምዕራፎች የተዳሰሱ ሲሆን ከሠንጠረዥ፣ ከፎቶግራፍና ከካርድ ላይ መረጃዎችን አንብቦ መረዳት እንደሚቻል በዚህ ምዕራፍ ተምረናል፡፡ በጥቂቱም ቢሆን የሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ ስልትንም ቀስመናል፡፡ የንግድ ሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ ከሌሎች የደብዳቤ አጻጻፍ ስልቶች እንደሚለይም ተገንዝበናል፡፡ ከዘይቤ አነጋገሮች የጥቂቶቹን (እንቶኔ፣ ምፀትና ግነት) ዘይቤዎችን አተረጓጐም በውል አይተናል፡፡

## የክለሣ ጥያቄዎች

1. "ቶሳ ወደ ት/ቤት ከመሄዱ በፊት ዝግጅት አድርጓል"፡፡ የሚለው ዓረፍተነገር ዓይነት ______________ ነው፡፡
2. ገፈፈ ብለን ገፈፋ ብንል፡-
   ሀ. ገመተ ብለን ______________ እንላለን፡፡
   ለ. በላ ብለን ______________ እንላለን፡፡
   ሐ. ዘገነነ ብለን ______________ እንላለን፡፡
   መ. አሰሰ ብለን ______________ እንላለን፡፡
3. ለህዳሴው ግድብ ቦንድ እንድንገዛ ጥሪ ተደርጐልናል፡፡ ________ ቦንድ መግዛት አለብን፡፡
   ሀ. ይሁንም እንጂ
   ለ. ስለዚያ
   ሐ. በመሆኑም
   መ. በአንፃሩ
4. ከሰዎች ጠይቃችሁም ይሁን መጻሕፍት አንብባችሁ በንግድ ሥራ ውስጥ አንድ ድርጅት እንዲቀጥራችሁ የቅጥር ማመልከቻ ደብዳቤ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡
5. ከተማራችኋቸው ሌላ የእንቶኔ ዘይቤ ምሳሌ የሚሆኑ፣ ለምፀት ዘይቤ ምሳሌ የሚሆኑ እና የግነት ዘይቤ ምሳሌ የሚሆኑ ሦስት፤ ዓረፍተ ነገሮች ወይም ግጥሞች ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አስር የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል። በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅጽን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የዓረፍተነገሮች ዓይነቶችን ለይቻለሁ። | | | |
| 2. | ከግስ ስምንና ቅጽልን እመሠርታለሁ። | | | |
| 3. | አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን በተገቢው ቦታ ተጠቅሜ አንቀጾችን እጽፋለሁ። | | | |
| 4. | የአንድን ውይይት አዳምጬ የውይይቱን መልእክት እገልጻለሁ። | | | |
| 5. | የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር በሥራና በምርት ዙሪያ አደርጋለሁ። | | | |
| 6. | በሠንጠረዥ፣ በፎቶግራፍ፣ በካርታ አማካይነት የቀረበን መረጃ በጽሑፍ አቀርባለሁ። | | | |
| 7. | የንግድ ሥራ ደብዳቤ በአጻጻፍ ቅርጹ መሠረት እጽፋለሁ። | | | |
| 8. | አንቶኔ፣ ምፀትና ግነት ዘይቤዎችን ለይቼ መግለጽ እችላለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

## ሙዳየ ቃላት

| ቃል | ፍች |
|---|---|
| ሂስ | በደካማ ጎን ላይ የሚያተኩር አስተያየትና ነቀፋ:: |
| ህቡዕ | ድብቅ፣ ስውር፣ ሚስጥራዊ:: |
| ሊቅ | በትምህርት የበሰለ የተራቀቀ፣ ምሁር፣ አዋቂ:: |
| መላምት | በማስረጃ ያልተረጋገጠ ንድፈ ሀሳብ፣ የግምት አባባል:: |
| ማቅ | ከጥቁር በግ ፀጉር ተፈትሎ የሚሠራ እንደ ብርድ ልብስ ያለ ልብስ:: |
| ማጀት | ብዙ ጊዜ በአነስተኛ ጎጆ ቤቶች ውስጥ በመከታ የተከለለ የእቃ ማስቀመጫ ጓዳ:: |
| ምጸት | በቀጥታ የቀረበውን ሀሳብ ትርጉም ተቃራኒ የሚያሳይ የንግግር ስልት:: |
| ራእይ | በእንቅልፍ ወይም በተመስጦ ጊዜ የሚታይ ህሊናዊ ትርኢት፣ ህልም:: |
| ሰማእት | ለእምነቱ፣ ለሃይማኖቱ መስዋእት የሆነ ሰው:: |
| ስኬት | የአላማ ወይም የድርጊት ክንዋኔ በጥሩ ሁኔታ እንደታቀደው መፈፀም:: |
| ስውር | ሽሽግ፣ ድብቅ፣ የማይታይ:: |
| ቅሪት አካል | ጥንት ሕይወት የነበራቸው አሁን ግን ደርቀው በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ ጠጣር ነገሮች:: |
| ባድማ | ጠፍ፣ ወና፣ ባዶ ቦታ:: |
| ብሩህ | የበራ፣ የፈካ፣ ንጹህ፣ የጠራ:: |
| ትቢያ | ደቃቅ አፈር፣ አቧራ:: |
| ነውጥ | ሁከት፣ ብጥብጥ፣ ሽብር/ርደት፣ ንቅናቄ/:: |
| አረንቋ | ረግረግ፣ ማጥ:: |
| አረጋዊ | ሽማግሌ፣ አዛውንት:: |
| አቆራኘ | አንዱን ከሌላው ጋር አጣምሮ አሠረ:: |
| አቻ | እኩያ፣ በእኩል ደረጃ የሚገኝ:: |
| አነፀ | ጠረበ፣ ላገ፣ ሰራ፣ ገነባ:: |
| አንደበት | ለመናገር የሚያስችል የሰውነት ክፍል፣ ልሳን:: |

| | |
|---|---|
| ሹደት | በድግግሞሽ የሚካሔድ የአንድ ድርጊት ክንዋኔ ሂደት፣ ዙረት:: |
| እውን | እውነት፣ እርግጥ:: |
| ኮበለለ | የነበረበትን ቦታ ትቶ ወደ ሌላ ቦታ ተደብቆ ወይም ተሸሽጎ ሔደ ወይም ጠፋ:: |
| ዘለፋ | ነቀፋ፣ ስድብ፣ ቁጣ:: |
| ይፋ | ገሃድ፣ ግልፅ:: |
| ዲብ | ከፍታው አነስተኛ የሆነ የአፈር ጉብታ:: |
| ድብኝት | ከጭቃ የተሠራ የእህል ማስቀመጫ ጎታ፣ ጉስጉሻ:: |
| ገሃድ | ስውር ያልሆነ፣ ግልፅ ወይም ይፋ:: |
| ጉራማይሌ | የተለያዩ ቋንቋዎች በመደባለቅ የሚቀርብ፣ ድብልቅ ንግግር ወይም ጽሑፍ:: |
| ጦስ | ሰበብ፣ ምክንያት:: |
| ጨፌ | ለምለም ሳር የሚበቅልበት ውሃማ መሬት:: |
| ፀዳል | ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ:: |
| ፀጋ | አምላካዊ ስጦታ፣ ሃብት፣ ረድኤት:: |
| ፅናት | ያለማወላወል በአንድ አቋም ላይ መርጋት:: |
| ፈርጥ | ከተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች የሚሠራና በቀለበት፣ በዘውድ ላይ የሚደረግ የሚያብለጨልጭ ጌጥ:: |
| ፋይዳ | ጥቅም፣ እርባና:: |

## ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሀሞተ ቢስ | ፈሪ |
| ሀረግ መዘዘ | ዘሩን ቆጠረ |
| ሆድና ጀርባ | ፈጽሞ አለመግባባት |
| ልቡ ቆመ | አንድ ነገር ለማድረግ ቸኰለ፣ ጓጓ |
| ሠርግና ምላሽ | ታላቅ ደስታ |
| ሰባራ ስንጥር | ማንኛውም እቃ |
| የሰው ነጭ | ብዙ ህዝብ |
| ስሙን ተክለ | ታዋቂ ሆነ |
| ቀጭን ጌታ | ሀብታም |
| ቅቤ አንጓች | አወደድ ባይ አስመሳይ |
| ብቅል አውራጅ | ረጅም |
| እንባ ጠባቂ | ተቆርቋሪ |
| እንብርት የለሽ | በልቶ የማይጠግብ፣ ሆዳም |
| እጅ አጠረው | ገንዘብ አለቀበት፣ ቸገረው |
| ውስጡን ለቄስ | የተደበቀ መጥፎ ተግባር |
| የአዞ እንባ | የውሸት ሀዘን |
| የውሻ አፍንጫ | በጣም ቀዝቃዛ |
| ገመና ከታች | ምስጢር ደባቂ |
| ጎህ ቀደደ | ፀሀይ ወጣ፣ ሌሊቱ ነጋ |
| ፈሳጭ ቆራጭ | አምባገነን |

# ዋቢ መጻሕፍት


## ሀ. ረጃጅም ልቦለዶች

ሀዲስ አለማየሁ (1960) ፍቅር እስከ መቃብር፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሲሳይ ንጉሱ (1978) ሰመመን፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

## ለ. አጫጭር ልቦለዶች

አንጋፋና ወጣት ደራስያን (1998) ወንዞች እስኪሞሉ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለድ ታሪኮች፡፡ አዲስ አበባ፣ ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር፡፡

አዳም ረታ(1981) ማህሌት፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

## ሐ. ወጎች

መስፍን ኃ/ማርያም (1976) የቡና ቤት ሥዕሎችና ሌሎችም ወጎች፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፡፡

የሻው ተሰማ (1997) የጥቁር አፈር ትሩፋት፡፡ አዲስ አበባ፣ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡

## መ. ግጥሞች

በውቀቱ ስዩም (2001)፡፡ ስብስብ ግጥሞች፡፡ አዲስ አበባ፣

ደበበ ሰይፉ (1980)፡፡ የብርሃን ፍቅር፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ፈቃደ አዛዘ (1985) ጩኸት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

## ሠ. አጋዥ መጻሕፍት

ማረው አለሙ (1995) በሳል ድርሰት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባዩ ይማም(2002) አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ(1999) የአማርኛ ሥነ ግጥም፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች

ታሪኩ ፋንታዬ (2001) **አማርኛ ሁሉ ለሁሉ (ከመሰስተኛ ኮሌጅ)**፣ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

አለም እሸቱ (1992) **መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ** ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ (1975) **የአማርኛ ፈሊጦች፡፡** አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ዘሪሁን አስፋው (1992) **የስነፅሑፍ መሠረታውያን**፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል (2001)፡፡ **ኣማርኛ መዝገበ ቃላት**፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፡፡

ደምሴ ማናህሎትና አምሳሉ አክሊሉ(1982) ጥሩ ያማርኛ ድርሠት እንደት ያስ ነው?፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ደረጀ ገብሬ (1996) **ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ**፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ(    )፡፡

ጌታሁን አማረ (1990) **ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ** ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡